ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ- አማርኛ ትህምርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# ስነ ምግባራዊ ሂሰ በተመረጡ አጫጭር ልቦለዶች ዉሰጥ ማሳያነት

የቀረበ ጥናት

ለኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፉና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት

ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ ጌታቸዉ አየነዉ

መጋቢት
2015 ዓ.ም

ጅማ -ኢትዮጵያ

# ስነ ምግባራዊ ሂስ በተመረጡ አጫጭር ልቦለዶች ዉስጥ ማሳያነት

የኢትዮጵያ ስነ-ጹሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት

የቀረበ ጥናት

በ

ጌታቸዉ አየነዉ

አማካሪዎች


| | |
|---|---|
| ዋና አማካሪ | ዶ/ር ማንያለዉ አባተ |
| ረዳት አማካሪ | ዶ/ር ምህረት ሳዳሞ |

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጹሑፍ -አማርኛ ትህምርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


መጋቢት 2015 ዓ.ም

ጅማ -ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ- አማርኛ ትህምርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# ስነ ምግባራዊ ሂሰ በተመረጡ አጫጭር ልቦለዶች ዉስጥ

# ማሳያነት የቀረበ ጥናት

ለኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ

ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ጌታቸዉ አየነዉ

መጋቢት 2015 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም -------------------------------------ፊርማ-------------------ቀን---------------------

የዉስጥ ፈታኝ ስም-------------------------------ፊርማ---------------------ቀን-------------------

የዉጭ ፈታኝ ስም--------------------------------ፊርማ---------------------ቀን-------------------

## ምስጋና

ከሁሉም በፊት በመኖሬ ይችን ቀን አይቻለሁና መኖር የሚቻል የስኬት ሁሉ ምንጭ የሆነዉ የድንግል ማሪያም ልጅ ልዑል እግዝአብሔር ይመስገን፡፡ከዚህ በታች የዘረዘርኳችሁ ሰዎች በተለያየ መንገድ ለዚህ ጥናት መሳካት የየራሳችዉን ድርሻ ያበረከቱ ናቸዉ፡፡በነበረን ጊዜያት ሁሉ ቅንነትና የተገባ አስተያይት ለሰጣችሁኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ማንያለዉ አባተና ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ  እንዲሁም ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ጊዜያችዉን ሰዉታችዉ ላደረጋችሁልኝ የተገባ አስተያይትና ቅንነት ባለፍኳቸዉ አስቸጋሪ ጎዳናዎች ታበረቱኝ ስለነበረ በፍጹም ቅንነት እዉቀታችዉን ስላካፈላችሁኝ ይህ ይገባችኋል፡፡መተኪያ የሌላችሁ ቤተሰቦቸ በእናንተ ላይ አቅም አግኝቻለሁና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

ሥነ-ምግባራዊ ሂስ" በተመረጡ አጫጭር  ልቦለዶች ውስጥ በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ጥናት በአምስቱ የሱለይ አደም ድርሰቶች ውስጥ የስነ-ምግባር ሂስን መመርመር ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ስነ ጹሑፍ በዘመን መንፈስ ዉስጥ የራሱን ጭብጥ እየያዘ እራሱንም በተለያዬ የአጻጻፍ ስልቶች እያሳደገ የማህበረሰቡን ተጨባጭ ህይወትና ኑሮ መልሶ ለማህበረሰቡ ያቀርባል፡፡በጊዜ ሂደትም የስነ ጹሑፍ ሂስ  ጭብጥን መሰረት በማድረግ  ማጠንጠኛ ከሆኑት መካከል ስነ ምግባራዊ ሂስ  አንዱ ሁኖ የሚጠቀስ ነዉ፡፡ ለዚህም የሂስ ዓይነት በጥናቱ ዉስጥ የሞራልን ንድፈ ሀሳብ መነሻ አድርጎ የዲኦንቶሎጂን ንድፈ ሀሳብ በዋናነት፣ ቴሊኦሎጅ እና ቨርቹ ኤቲክስ የሚባሉትን ዘረፎችም እንደ አስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ እኩይና ሰናይ ድርጊት፣ ግብረገባዊነት፣ ማህበራዊ እሴቶች፣ የሰዉ ባህሪና ፀባይ፣ጎሊናና ሀቀኝነትን ማጉደል እና የክብር መውረድ የሚሉትን ጽንሰ ሀሳቦች እንደ አንድ የስነ-ምግባራዊ ሂስ ከሚዳስሳቸዉ ጉዳዮች ማሳያ በመውሰድ እንዴት፣ የት፣ መቼ፣ በምን፣ ለምን እና በነማን መገለጫነት እንደቀረበ ለማሳየት ሞክሬያለው፡፡

በዚህም በልቦለዶቹ ውስጥ የሰው ልጅ ሲያዳብረው የመጣን ደንበኛውን የስነ-ምግባራዊ እሴት እንደ ኋላ ቀር፣ ከንቱና ቀላፊ አድረገው የሚመለከቱ ገጸ ባህሪያት ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ አፈንግጠዉ በመዉጣት እኩይ የሚባሉ ድርጊቶችን እንደሚፈጸም አመላክቻለሁ፡፡ በስሜት መዘውርነት  ድርጊት መፈጸማቸው ደግሞ "በእኩይ ባህሪ በመታነጽ ከሰዉነት የወጣ አረመኔያዊ ጭካኔ በተሞላበት ከኅሊና ዉጭ እና በሌላዉ ስቃይ የሚደሰቱና በተግባሩም የሚሰተፉ ገጸ ባህሪያት እንዳሉ ታይቷል፡፡

በአንድ ጎራ ወጣት ትውልዶች ከነባሩ የስነ-ምግባር እሴት እንውጣ በሚል ሲሞግቱ፣ በሌላኛው ጎራ የወጣቶችን ከማንነት መውጣት ለመታደግ ሲጥር፣ በልቦለዶቹ ፈጠው የሚታዩትን ክሱቶችና ሁነቶች ከሚፈጽሙት ገጸ ባህሪያት በግልባጩ የመፍትሄ ጥበብን የሚያዘጋጁ ገጸ ባህሪያት ያሉ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ ትልቅ አክብሮትና እምነት የተጣለባቸው የእምነት አባቶች በላይ በአብሮነት ለመኖር፣ ሀይማኖትም ይሁን ሌሎች የግል ጉዳዮች ሳይገድቦቸዉ፣ አንዱ ለአንዱ በመተሳሰብና በመተዛዘን፣ ያላቸዉን በማካፈልም ይሁን በመረዳዳት፣ ኢትዮጵያዊ ስነ ምግባርን በመጠበቅ ደረጃ ላቅ ያለ ሚና ሲወጡ ተስተውሏል፡፡ በዚህም ተግባር ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣  ከህጻናት እስከ አዛውንት አድነናቆትን ሲቻሩና ሲሞገሱ በተቃራኒዉ እኩይ ድርጊትን ሲተገብሩ በማህበረሰቡ ሲወገዙና ሲንቋሸሹ ያሰያል፡፡

ብዙዎቹ ገጸ ባህሪያት ትናንት በተሸመነ የዛሬ ማንነት፣ ዛሬም ለነገ ለቀጣይ ትዉልድ ቅብብሎሽ እርሹ በሚይዝበት መልኩ፣ በማህበረሰቡ ተወደዉና በምሳሌነት እየተጠቀሱ ቆመው ህይወትን ሲገፉ ተስተውለዋል፡፡ ለሁሉም የስነ ምግባራዊ ሂስ ማሳያ የሆነውን የአጭር ልቦለድ መድብል  ያለምንም ግርዶሽ ሱለይ አደም በጥበብ ወዝ አሳይቷል፡፡

## ማዉጫ


ምስጋና ..... IV

አጠቃሎ..... VI

ምዕራፍ አንድ ..... 1

1. መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2 የጥናቱ ዓነሳሽ ምክንያት..... 4

1.3 የጥናቱ ዓላማ..... 5

1.3.1 ዝርዝር ዓላማዎች ..... 5

1.4.1 የጥናቱ ዓብይ ጥያቄዎች ..... 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሚታ ..... 5

1.6 የጥናቱ ወሰን ..... 6

ምእራፍ ሁለት፡- ክለሳ ልሳን ..... 7

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ..... 7

2.1.1. ስነ-ምግባራዊ ሂስ..... 7

2.1.2 የስነ-ምግባር እሴቶች ..... 23

2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ..... 28

ምዕራፍ ሶስት..... 32

3 የጥናቱ ዘዴ..... 33

3.1 የናሙና አመራርጥ ..... 33

3.1.1 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች..... 34

3.1.2 የአተናትን ስልት ..... 34

ምዕራፍ  አራት..... 35

4 የመረጃ ትንተና ..... 35

4.1 የልቦለዱ ጭምቅ ታሪክ በአልፎ  ያላለፈ  አጭር ልቦለድ ..... 35

4.1.1 ስነ ምግባር በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ....................................................36

4.1.1.8 ምርቃት በባህል የመልካም ስነ ምግባር መገንቢያነት ....................................................42

4.2 በዘመናይ ማርዬ የቀረበዉ አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ....................................................44

4.2.1 ዘመናይ ማርዬ ከስነ ምግባር ሂስ አንጻር ....................................................44

4.2.2 የሰባዊነት መንጠፍ በዘመናይ ማርዬ አጭር ልቦለድ ዉስጥ ....................................................46

4.3 ልጅን አደራ አጭር ልቦለደ ጭምቅ ታሪክ ....................................................46

4.4 ጀሮዬን ጣፈጠኝ አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ....................................................48

4.5 የአንድ ነፍስ ጩኸት አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ....................................................50

ምዕረፍ አምስት ....................................................53

5 ማጠቃልያና አስተያይት ....................................................53

5.1 ማጠቃልያ ....................................................53

5.2 አስተያይት ....................................................54

ዋቢ መጽሐፍት ....................................................55

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ስር በጥናቱ ዙሪያ ተያየዥ የሆኑ ጉዳዮች የተዳሰሱበት ሲሆን፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ዋና እና ንዑሳን ጥያቄዎች፣ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎች እና የጥናቱ ወሰን ቀርበውበታል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ስነ-ጽሑፍ የህይወት በርካታ ጉዳዮችን ይነቅሳል፡፡ ተፈጥሮ፣ ባህል፣ የሰው ልጅ ባህሪና ተግባር በስነ-ጽሑፍ የሚገለጹ የህይወት ፈርጆች ናቸው፡፡ የባህል ውጤት የሆነው ስነ-ጽሑፍም መልሶ ባህልን በመግለጽ በኩል ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስነ-ጽሑፍ በሁሉ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ ሁሉን ነገር ለመግለጽም የላቀ ብቃት አለው፡፡ ስለሰው ልጅ ሕይወት ደግሞ በተለየ ዓይን ይመለከታል፡፡ ማህበራዊ ህይወትን ከሚኖሩ ፍጡራን መካከል የሰው ልጅ ይጠቀሳል፡፡ በአብሮነት ህይወቱ ውስጥም የሚፈጥራቸው በርካታ ልዩ ልዩ ማህበራዊ እሴቶች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ራሱን ከተፈጥሮ እና ከራሱ ባህሪ ጋር ያለውን ዋህድነት እና መቃቃር ለመመርመር፣ በአብሮነት ሂደቱ ውስጥ ሲያዳብራቸው የመጣን ውስጣዊና ውጫዊ ጠባያቱን ለመለካት የሚያስችለውና የግሉ የሕይወት መመሪያ አድርጎ የሚጠቀምበት ስነ-ምግባር ነው፡፡ ስለ ስነ-ምግባር ሂስ ምንነትና አስፈላጊነት የፍልስፍና ሰዎች የተለያየ አቋም አላቸው፡፡

ዘሪሁን (1992፣361) የሂስ አይነቶች እንደ ስነ-ጹሑፍ ስራዉ ዘመን የተለያዩ ናቸዉ፡፡በአብዛኛዉ እስከ አሁን የታዩት የሂያሲያን አላማዎች የራስን ሥራ ለምን እንደተጻፈ ማረጋገጥ ወይም ስራዉን ወይም የተሰራበትን መርህ ሊረዱት ለማይችሉት ለማብራራት ምናባዊ ኪነ ጥበብ በእሴት ላይ ጥያቄ የማንሳት አዝማሚያ የሚታይበት ዓለም መሆኑን ለማረጋገጥ …የሥነ ጹሑፍ ሂስ አይነቶች አመዳድብ ከእነዚህ ዓላማዎች አንዱን ወይም የተወሰኑትን አጥብቆ በመያዝ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ በየጊዜዉ ከተሰጡት ሥነ-ጹሑፋዊ ሂስ ዓይነቶች አምስቱ ማለትም ሥነ-ምግባራዊ ትንታኔ ስነ-ልቦና ስነ ማህበረሰባዊ ቅርጻዊ ስር መሰረታዊ በመባል የሚታወቁት በብዙ አዋቂዎች ዘንድ በተደጋጋሚ የሚጠሩ ሆነዉ እናገኛቸዋለን፡፡

ሥነ-ምግባራዊ ሂስ የቆየና ረጅም ታሪክ ያለዉ የሂስ ዓይነትና ከፕልቶ ጀምሮ ብዙ ሂያሲያን ሲደገፉትና ሲሰሩበት የኖሩ፣ዋነኛ ትኩረቱ አንድን የሥነ ጹሑፍ ስራ በሚይዘዉ ጉዳይ ወይም ሊስተላልፍ በተነሳዉ ቁም ነገር ላይ እንደሆነና ድርሰቱ በተጻፈበት ወቅት በዘመኑ በታወቁ የሥነ ምግባር መርሆች ላይ በመመርኮዝ ስራዉ ሰዊዊነትን ምን ያህል እንዳሳዬ እንደሚመዝን ይገልጻሉ፡፡

እንዲሁም ፕልቶ ‹‹የሰዉ ልጅ በስነ ጹሑፍ በማምጣት ከሃይማኖታዊ ሃሳብ ሊወጣ ይችላል የሚል ሃሳብ አለዉ››፡፡

Nietzsche's critique is an evaluative agenda: he thinks Morality is over all a bad thing and that it constitutes the dangers of all dangers, because it is not life en-hancing, but rather thwarts the possibility of achieving the most advanced forms of life 'the highest power and splendour of the human type (Douglas, Smith, 6)

Smith እንደሚገልጸው ኒቼ "ስነ-ምግባር በሁሉም ነገሩ መጥፎ ገጽታን" ይይዛል ብሎ የሚያስብ ነው፡፡ ምክንያቱም "ህይወትን የሚያሻሽል ነገር የለውም" ብሎ ያምናል፡፡ እንዲያውም የሰውን ልጅ ከላቀ የህይወት መልክ፣ ከፍ ወዳለ ችሎታና ግርማ ሞገስነት ደረጃ የሚደረስባቸውን አማራጮች ወይም እድሎች የከለከለ ነው፡፡ ስነ-ምግባር ግለሰቦችን ከራሱ፣ ደንብ፣ እሴት፣ ሀሳቦችና ግዴታዎች ጋር ተመሳስለው እንዲኼዱ እንጂ፣ "ጥሩ" የሚለው ነገሩ ከግለሰቦች ባህሪ ጋር የሚስማማ መሆን አለመሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም በማለት የስነምግባርን ረብ የለሽነት ይገልጻል፡፡ እንደ ሆቢስ ያሉት ደግሞ ጠቃሚነቱን ያስረዳሉ፡፡ "morality is simply a declaration of rules and beliefs that are considered absolute guides for human behaviour." Hobbes, (1994:11)

እንደ ሆቢስ ስነ-ምግባር በሰው ህይወት ውስጥ ባህሪን ለመግራት የተደነገገ የህጎች እና የእምነቶች ፍጹም መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ (ህግ፣ ድንጋጌና መመሪያ የሚሉት ቃላት በዚህ አገባብ የማህበረሰቡን ቃላዊ ስምምነቶች የሚመለከቱ ናቸው) ህጉም ድርጊቶችን መልካም እና እኩይ በማለት የሚያስቀምጥ ነው፡፡ መልካም የሆኑትን ስነ-ምግባራዊ በሚል ሲፈርጅ እኩይ ባህሪንና ድርጊትን ደግሞ ኢ-ስነ-ምግባራዊ ብሎ ያስቀምጣል፡፡

የሰው ልጅ ቀጣይ ለሚተኩት የአብራኩ ክፋዮችም እንዲማሩበት ያደርጋል፡፡ ይህም የሰው ልጅ በማህበራዊ ህይወቱ ጸንቶ እንዲዘልቅ እርስ በእርስ እንዳይጎዳዳ የሚያለዝብበት ስርዓት ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይኸው ስርዓት ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ ውስጥ የሚገለጹ ሀሳቦችን ለመገምገምና የጽሑፉን ደረጃ ለመስጠት የስነ-ምግባር ውሳኔ ያስፈልጋዋል፡፡ ኤተንም ይህን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

Eaton "moral judgments are a common feature of interpreting, appreciating and evaluating literary works" (A.W.eaton:433) በማለት ስነ-ጽሑፍን ለማድነቅ ለመተርጎም እና ለመገምገም ለሁሉም ማንጸሪያው ስነ-ምግባር እንደሆነ ያስረዳናል፡፡ አንድ ጽሑፍ በስነምግባር ልኬት ሲመዘን ከመስፈርቱ ወለል በታች ተንሸራትቶ ሲገኝ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን አለመዳሰሱ መርዶ ነው፡፡ ስነ-ምግባራዊ ዉድቀተ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የስነ-ምግባር ልኬቶች ተጥሰው ሲገኙ እና ይህንኑ ለመግለጽ የሚሰጥ ስያሜ እንደሆነም Njoku ያስረዳል፡፡

"...moral decadence is the process of behaving in a way that shows low moral standards. It means gross reduction in the moral values in a particular society. Thus, moral decadence appears to be a fall in the moral standard of the society.

It seems to be deterioration or a collapse in upholding our societal values, beliefs, norms and ethical standards." (Njoku, 2016 pp. 187)

እንደ ንጆኩ አገላለጽ የስነ-ምግባር ዉድቀት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መልካም ስነ-ምግባርን ከመልቀቅ ወይም ከመጣል የሚመጣ ነው፡፡ ዝቅተኛ የስነ-ምግባር ደረጃዎችን በሚያሳይ መንገድ የመመራት ሂደትም አንዱ ማሳያው ነው፡፡ በተወሰነ ማህበረሰብ ውስጥ አጠቃላይ የእሴቶቹን መቀጨጭ የሚያሳይ ተግባርና ሀሳብ ሲሆን፣ ማህበረሰቡ በእምነት ከያዘው እሴቱ፣ ደንቡ፣ እምነቱና ስነ-ምግባሩ በሚፋታበት ጊዜ መገለጫው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ይኸው ድርጊትና ተግባር ገሀዳዊ አለም በአስተማስሎ በሚቀርብበት የስነ-ጽሑፍ ፈርጅ በሆኑት ልቦለዶችም ውስጥ ይንጸባረቃል፡፡ ልብ ወለድ በደራሲው ስሜትና የምናብ ልቅነት በመታገዝ ስለሚጻፍበትና ስለተጻፈለት ማህበረሰብ ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚያሳያቸውን አዳዲስ ለውጦች በተለያዩ መንገዶች ያንጸባርቃል፡፡ በአማርኛ ስነ-ጽሑፍ የስነምግባር ከሚዳሰሱት ልቦለዶች መካከል የሱለይ አደም አጭር ልቦለድ መድብሎች የፈጠራ ስራዎች አመላካች ናቸው፡፡ ስነ-ጽሑፍ በትችት አይን ሲቃኝ ትኩረት ከሚደረግባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ስነ-ምግባር እንደሆነ የሚከተለው ጽሑፍ ያትታል፡፡

"Writes Hyman modern criticism has emphasized the autonomy of the poem and the novel from their moral purposes" (Karim, 2012:186)

እንደ ካሪም ገለጻ ዘመናዊ የስነ-ጽሑፍ ሀያሲዎች ግጥሞችና ልቦለዶቹን በሚመረምሩበት ጊዜ ትኩረታቸው ግጥሞችና ልቦለዶቹ ከያዙት ስነ-ምግባራዊ ዓላማ አንጻር እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ከተጠቀሱት የስነ-ጽሑፍ ዘርፎች መካከል ደግሞ የአማርኛ ግጥሞችና ልቦለዶች የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣ ስነ-ምግባርን ለመተቸት ምቹ የሆኑ የስነ-ጽሑፍ ዘርፎች ናቸው፡፡ ስነ-ጽሑፍ ዓላማው ማስደሰት ነው፡፡ ይህንንም ጉልህ አላማ የሚፈጽመው ሁሉን አቀፍ የህይወት ሂስ በማቅረብ ነው የሚሉት ደግሞ ዮሐንስ አድማሱ ናቸው፡፡(ዮሐንስ ፣መነን መጽሔት፤ግንቦት 1961ዓ.ም፣1)

የዮሐንስ አገላለጽ በቀጥታ ስነ-ጽሑፍ ሁለንተናዊ ይዘት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ህይወት ይሰምር ዘንድ የሚመራበትን የስነ-ምግባር ደንቦች የሚያካትት መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡ በዚህም የአማርኛ ስነ-ጽሑፍ ስነ-ምግባርን ጉዳዩ አድርጎ የሚጻፍ መሆኑንን በነ ህሩይ ወልደ ስላሴ ወዳጄ ልቤ (1915) እና በነሃዲስ አለማየሁ፣ ፍቅር እስከ መቃብር (1958)፣ ወንጀለኛው ዳኛ (1974) እና የልምጃት (1981) ያሉት ልቦለዶች ስነምግባርን በዘመኑ የፈተሹ ልቦለዶች መሆናቸው ተወስቷል፡፡

በተመሳሳይ የሱለይ አደም አጫጭር ልቦለዶች በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን የስነ ምግባር ጉዳዮች የሚመለከቱና የሚፈትሹ ናቸው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ስነ-ምግባራዊ ሂስ በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር መርሆችን መሰረት በማድረግ ከግል ገጠመኝ ከማህበረሰቡ ጋር ስኖርና ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዬ ጋር በማገናዘብ ስነ ምግባራዊ ሂስ በአንድ የስነ ጽሑፍ ስራ ላይ የሚደረግ ምዘና እንደመሆኑና ባለንበት ዘመን የድጅታልና የፊልም እንዱስትሪዉ በበዛበት ጊዜ በስነ ጽሑፉ ስራዎች ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች በአጭር ልቦለድ ድርሰት ላይ መቅረባቸዉ ለተደራሲያን ያላቸዉን ሚና ለማወቅና ለማሳወቅ፡፡

ሁለተኛዉ አነሳሽ ምክንያቴ፡-ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዉ የሚያስተላልፈዉ ቁም ነገር ድርሰቱ የቀረበበት ዘመንና ስነ-ምግባርን የማንጸባረቅ አቅሙና በሰዎች ላይ ሊያሳድር የሚችለዉ ተጽዕኖ በድርሰት ስረዉ እንዴት እንደቀረበ የመፈተሽ ልዩ ፍላጎት ስላደረብኝ ጥናቱን ለማከናወን አነሳስቶኛል፡፡

ሶስተኛዉ፡- የስነ ምግባር መጎደሎች፣የስብዕና መንጠፍ በዘመናችን እየተስፋፋ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ይህ ጉዳይ ደግሞ በተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች ዉስጥ እንደተቀነቀነ ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡(ለምሳሌ፡-መአዛ ብሩ፣2005)፡፡ ይህ ጉዳይ ከግብረ ገባዊነት መጥፋት ጋር ተያይዞ የሚከሰት ነዉ፡፡የተለያዩ መጽሐፍት ሥነ-ምግባር(ግብረ ገብ) የዘመኑ አሳሳቢ ጉዳይ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ስለዚህ በስነ ምግባር ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለማድርግ ሲወሰን የሰለይ አደም ስራ ለጥናት ከተመረጠ በኋላ በግብረ ገብነት በልጽጎ የተገኙ በመሆኑ ከመድብሉ ዉስጥ አልፎ ያላለፈ፣ዘመናይ ማርዬ፣የአንድ ነፍስ ጩኸት፣ልጀን አደራና ጀሮዬን ጣፊጠኝ የሚሉት ለጥናቱ ሊመረጡ ቸለዋል፡፡

አራተኛዉ የማጥናት ግፊቴ፣ በርካታ የአማርኛ ልቦለዶች በተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች የተፈተሹ ቢኖሩም፣ የስነ-ምግባር ፍልስፍናን መሰረት አድርገው ስነ-ምግባርን ብቻ ጉዳያቸው ያደረጉ ጥናቶች ስለመኖራቸው በእኔ የጥናት ዳሰሳ ለማግኘት ባለመቻሌ ነው፡፡

"ስነ-ምግባራዊ ዝቅጠት በኢያሪኮ 777፣ 888 እና ኤጭ... ልቦለዶች ውስጥ" ፣የሰባዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦቻቸው፣ በየህሊና ባርነት ልቦለድ ውስጥ "፣" የተፈጥሮና የባህል ግጭትና እርቅ በአዳም ረታ ህማማትና በገና ውስጥ " ፣ " ባይተዋርነት በሰባተኛው መልአክ ፣ ትኩሳትና ሌቱም አይነጋልኝ" የሚሉት የእንዳለ ገበየሁ፣ የወንድወሰን ሽመልስ፣ የሰላማዊት በየነ እና የስነ-ኽይወት ገዛኽኝ እንደቅደም ተከተላቸው የስነ-ምግባር ጉዳይዮችን በእግረ-መንገድ የዳሰሱ ጥናቶች ቢሆኑም፣ ከብዙ የስነ ምግባር ጉዳዮች ዉስጥ አንዱን በታላሚነት መርጠዉ በማዉጣት ይዳስሳሉ እንጅ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን ብቻ በመምረጥ የመረመሩ አይደሉም፡፡ ሌሎች ምሁራንም ቢሆኑ ተደራሲያን ፣ የሱለይ አደምን አጫጭር ልቦለዶች በገረፍታ ከማንበብና ፣ አስተያየት ከመስጠት የዘለለ የልቦለዶቹን ውስጣዊ ምንነት በጥናት በመደገፍ ያቀረቡበት መንገድ የለም፡፡ ይኽ ጥናትም ይህን ውስን ክፍተት ይሞላል በሚል፣ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሀሳብን በመታገዝ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን ለመመርመር አመች ይሆናሉ በተባሉት አምስት የ"ሱለይ" ስራዎች፣ ላይ ተመስርቶ፣ "ስነ-ምግባራዊ ሂስ ጉዳዮች ቢጠኑ የዘመኑን የስነ-ምግባር ሁነት ሊያሳይ ይችላል ከሚል ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፡-ለጥናቱ በተመረጡ አምስት አጫጭር ልቦለዶች ዉስጥ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን መመርመር ነዉ፡፡

### 1.3.1 ዝርዝር ዓላማዎች

1 የስነ ጹሑፍ ስራዉ ምን ያህል ሥነ ምግባራዊ እሴቶችን እንደሚያንጸባርቅ መፈተሽ፣

2 ለስነ ምግባር ዉድቀት የሚዳርጉ ሁነቶችንና ተግባራትን መለየት፣

3 በልቦለዶች ዉስጥ የስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች የቀረቡበትን መንገድና የሚያስተላልፉትን ይዘት ማብራራት፣

4 ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች በገጸ ባህሪያት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽኖ መግለጽ፣

5 ገጸ ባህሪያት ወደ እኩይና መልካም ምግባር የሚወጡበትንና የሚወርዱበትን መንገደ እንዳለ ማረጋገጥ፣

## 1.4 በጥናቱ የሚመለሱ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

### 1.4.1 የጥናቱ ዓብይ ጥያቄዎች

በተመረጡ አጭር ልቦለዶች ዉስጥ የስነ ምግባራዊ ሂስ ማሳያዎች እንዴት ተመርጠዋል?

### 1.4.2 የጥናቱ ንዑሳን ጥያቄዎች

1 በልቦለዶች ዉስጥ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች እንዲት ቀርበዋ ?

2 በልቦለዶች ዉስጥ ገጸ ባህሪያት ለሥነ ምግባራዊ መልካምነትም ይሁን እኩይነት ያስገባቸዉ ምክንያት ምንድን ነዉ?

3 የስነ ምግባር እኩይነት በገጸ ባህሪያት ላይ ያሳደረዉ ተጽኖ ምንድን ነዉ?

4 ገጸ ባህሪያት ከገቡበት የማህበራዊና ባህላዊ የስነ ምግባር ጥሰትና ብልሹነት መዉጣት ይችላሉን?

5 የስነ ጹሑፍ ስራዉ ምን ያህል ስነ ምግባራዊ እሴቶችን አንጸባርቋል?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሚታ

ጥናቱ በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ የስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን የቀረበበትን መንገድ መመርመር የሚል አቢይ ዓላማ የሚይዝ እንደ መሆኑ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የዳበሩ ማህበረ፣ ባህላዊ እሴቶች ያሉበትን ደረጃ በማመላከት በኩል የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ እኔም ይህን ጥናት ለማጥናት በስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ንባብ ስለ አደረኩ የዳበረ እውቀት እንዳገኝ አስችሎኛል፡፡ እንዲሁም የስነ ጹሑፍ ስራዎች በስነ-ምግባር ቀረጻ ላይ አወንታዊም

ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ በመጠቆም ስራዎቻቸው ይበልጥ ይመረመሩ ዘንድ መጠቆሚያ በመሆንም ያነሳሳል፡፡

የሰዎች የባህሪ እድገትና የልምድ ብስለት በስነ ምግባር እዉቀት ጭምር መታነጽ እንዲችል ስነ ምግባር በኢትዮጵያ ማህበራዊና ባህላዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች አኳያ ተጫማሪ ትኩረታዊ ጥናትና ምርምር እንደሚያስፈልግ ይሰጠቁማል፡፡

ስነ ጹሑፍ በሰዉ ልጆች ላይ ተጽዕኖ አሳዳሪ እንደመሆኑ መጠን በዚህ አጭር ልቦለድ ስራ ዉስጥ የተነሳዉ ማህበራዊ ጉዳይ የሆነዉ ስነ ምግባራዊ ትንታኔ መደረጉ ለሌሎችም ስነ ጹሑዊ ስራዎች ትንተና መነሻ በመሆን በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለሚሰሩት እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ስነ ጹሑፋዊ ስራዎች በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ እንደመሆኑ መጠን ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ ሁሉንም ይዳስሳል ማለት አይደለም፡፡ በዚህ መሰረትም ደራሲዉ በመድብሉ ዉስጥ ሃያ (20) የተለያዩ አጫጭር ልቦለዶች ቢኖሩትም በዚህ ጥናትና ምርምር አገልግሎት ላይ የዋሉት ለስራዉ አመች በሆነዉ የሰለይ አደም አጭር ልቦለድ መድብል ዉስጥ አልፎ ያላለፈ፣ዘመናይ ማርዬ፣የአንድ ነፍስ ጩኸት ልጆን አደራና ጀሮዬን ጣፈጠኝ የተሰኙት አምስቱ ብቻ ናቸዉ፡፡ ስነ ጹሑፋዊ ሂሶች እርስ በዕርስ ተያያዥነት ቢኖራቸዉም በድርሰቱ ዉስጥ ጎልቶ እንዲወጣ ወይም እንዲታይ ደራሲዉ ሊያሥተላልፍ የፈለገዉ ጉዳይ መሰረት በማድረግ አንዱን እንደ ዋናነት በማድረግ ሂስ ማካሄድ ይቻላል፡፡

በዚህም መሰረት ይህ ጥናት መሰረት ያደርገዉ በተመረጡት አጭር ልቦለድ መድብሎች ዉስጥ ስነ ምግባራዊ ገዳዮችን ነቅሶ በማዉጣታና አብይ ገጸ ባህሪያቶች የሚያካናዉኖቸዉን ድርጊት በማጤን ጭብጣቸዉን ትንታኔ ማድረግ ላይ ነዉ፡፡

በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትም ከሀገር ወስጥም ይሁን ከዉጭ የተገኙ ስራዎች ቢኖሩም የተመረጡት ስረዎች ከስነ ምግባር ጉዳዬች ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያላቸዉ ብቻ ናቸዉ፡፡ ለምን ቢሉ በጉዳዩ ዙሪያ በርካታ የተሰሩ ስራዎች ሰላሉ መምረጥ አስፈላጊ ስለሆነ ይህ ጥናትም ከስነ ምግባር ጉዳዮች ዉጭ የጥናቱ አካል አድርጎ አይመለከትም፡፡

ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን በሀሳብ፣በተግባርም፣በስፋትና በጥልቀት ያስነብባሉ ብሎ ባመነባቸዉ መገለጫዎች ላይ ብቻ ትኩረቱን አድርጎል፡፡

ከንድፈ ሀሳብ አንጻርም፣ የሞራል ንድፈ ሀሳብን የተጠቀመ ሲሆን፣ በዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሀሳብ የተቀነበበ ነው:: እንዳስፈላጊነቱ የቨርቹ ኤቲክስንና ቴሊኦሎጂካል ሥነ-ምግባርንም ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ እንደ pojman ገለጻ የዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሀሳብ ስነ-ምግባርን፣ ማህበረሰቡ የሕይወት መመሪያ አድርጎ፣ ከሚጠቀምባቸው ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ህጎች አንጻር ይመረምራል፡፡ ህጎችን ከማክበር አለማክበር፣ ግዴታን ከመወጣት አለመወጣት አኳያ እየመዘነ ሰናይ እና እኩይ፣ ተገቢነት ያለውና ተገቢነት የሌለው፣ በማለት ይፈርጃል (pojman, 2005)፡፡ ይኸም ለንድፈ ሀሳቡ መመረጥ ምክንያት ሆኗል፡፡

# ምእራፍ ሁለት፡- ክለሳ ልሳን

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የስነ-ምግባር ጽንሰ ሀሳቦችና እሱን ለመመርመር የሚያስችሉ ንድፈ ሀሳቦች፣ የስነ ምግባራዊ ሂስ ምንነት እንዲሁም የተዛማጅ ጽሑፎች የተዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡

### 2.1.1. ስነ-ምግባራዊ ሂስ

ስለ ስነ-ምግባር ምንነት ከመግለጼ በፊት ግን ጽንሰ ሀሳቡን አስመልክቶ ግልጽ ሊሆን ይገባል ያልኩትን ነገር ለመግለጽ እሞክራለው፡፡ ይኸውም በእንግሊዘኛ moral, morality and ethics በአማርኛ ግብረ-ገብ/ ስነ-ምግባር፣ ግብረ-ገባዊ/ ስነ-ምግባራዊ እና ስነ-ምግባር/ ግብረ-ገብ እንደቅደም ተከተላቸው እየተባሉ የሚጠሩት ቃላት ብዙ ጊዜ የፍልስፍና እና የስነ-ልቦና ሊቃውንትን ያስማማ ወጥ ትርጓሜ ይዘው አናገኛቸውም፡፡ አንድ አንዶች ቃላትን በተመሳሰይ ፍች በአማራጭነት ሲጠቀሙ ሌሎቹ ደግሞ የተለያየ ትርጉም አስይዘው ሲገለገሉባቸው ይስታዋላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ቃላትን በተገቢው መልኩ ለመጠቀም የምሁራንን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ያላቸውን ተመሳስሎሽ እና ልዩነት ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ ፈርጆ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የKelechን እና ሌሎችን ሀሳብ በመውሰድ በጥናቱ ውስጥ የሚኖራቸው ትርጉም በሚከተለው መልኩ ተቀምጧል፡፡

…morals and morality, which are understandably interchangeable with ethics because of their common etymological origin, is derived from the Latin word ‘mos’ (plural mores) which means ‘custom’ or ‘habit’ which is the equivalent of the Greek word ‘ethos’ which also means ‘custom’ or ‘habit’. The two terms morality and ethics are roughly interchangeable in/contemporary usage though some scholars try to demarcate them. For McClendon; “when a distinction is made “morals” nowadays refers to actual human conduct viewed with regards to right and wrong, good and evil, “ethics” refers to a theoretical overview of morality, a theory or system or code. In this sense, our morality is the concrete human reality that we live out from day to day, while ethics is an academic view gainedby taking a step back and analyzing or theorizing about (any) morality” (Kelechi,2018:42)

ከከልቺ ገለጻ የምንረዳው “ሞራሊቲ” ወይም “ሞራል” የሚሉት ቃላት ስነ-ምግባር ከሚለው ቃል ጋር በተለዋዋጭነት መጠቀም እንደሚቻል ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሁለቱም ቃላት መሰረተ ግንዳቸው ወይም ስነ-አመጣጥ መሰረታቸው በትርጉም አንድ ከሆነው እና “ሞስ” ከሚለው የላቲን ቃል የተገኙ በመሆናቸው እና ትርጓሜያቸውም ባህል፣ ልምድ የሚል በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዘመናዊ ሊቃውንት ለሁለቱ ማለትም ለሞራል እና ስነ-ምግባር በተወሰነም ቢሆን፣ McClendon፣ ድንበር ለማበጀት ሙከራ ያደረገ ሊቅ ነው፡፡ በዚህም፣

ሞራልን ትክክለኛ የሰዎች ባህሪ ሲሆን፣ ባህሪያቸውም ከትክክልና ስህተት፣ ከመልካም እና ከመጥፎ አንጻር የሚታይ ነው፡፡ ስነ-ምግባር ደግሞ ንድፈ ሀሳባዊ ምልከታ ሲሆን፣ ስለ ስነ-ምግባር የሚመረምር ዘዴ ወይም ስልት ነው በማለት ይገልጻል፡፡

በሌላ በኩል Fagothey የተባሉት ምሁር ከመሰረታዊ የቃላት ስነ-አመጣጥ ባህሪያቸው በመነሳት የሁለቱን ቃላት ትርጉም በተመሳሳይነት ያሥቀምጣሉ፡፡ “ethics (ethos) and morals (mos) study human customs some of which are mere conventions, such as table manners, mode of dress, forms of speech and expression of courtesy which vary from place to place and at different times”በ (Kelechi, 2018:42 ውስጥ የተጠቀሰ)፡፡ በማለት ለሁለቱም ቃላት በእኩል የአገላለጽ ክብደት፣ ስለሰው ልጅ ባህሪ፣ የአለባበስ፣ የአነጋገር እና ጨዋነትን በተመለከተ የሚያጠኑ እንደሆኑና፣ በጊዜ ሂደትም ትርጓሜያቸው ከቦታቦታ ሊለያይ እንደሚችል በማስረዳት፣ ቃላትን በተለዋወጭነት መጠቀም እንደሚቻል ያሳያሉ፡፡ እንደ Fagothey አገላለጽ  ሀሳቡ ሁለቱም በተለያየ መንገድ የማጥናትና የመጠናት ባህሪ ያላቸው ሳይሆን፣ ስለሰው ልጅ የሚያጠኑ ወይም የሚመረምሩ የሚል እንድምታን የያዙ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ Huri “ሞራሊቲ” የሚለው ቃል ከግሪክ የሚመዘዝ እና፣/Ethika በላቲን moralia) ከሚሉት ጥሬ ቃል የሚገኝ ሲሆን፣ ትርጉሙም ስነ-ምግባር ማለት ነው፡: የስነ-ምግባር ስነ-አመጣጥ /ethimological root/ ethos በላቲን mos ትርጉሙም ባህሪ፣ ባህል ወይም የአተገባበር ዘዴ፣ ተግባር የሚል ትርጉም ይይዛል፡፡ ስነ ምግባር ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች ያሉት እና ብዙ ጊዜ መርህ፣ መልካምነት፣ ደንብ እና ምግባር ከሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች ጋር የሚተሳሰርበት ባህሪ እንዳለው ይገልጻል፡፡ (Huri ፣2011፣30)

ከላይ የሁለቱ ቃላት ትርጉም በልዩነት የተቀመጠበት አግባብ ቢኖርም፣ የስነ-ምግባር እና የሞራል ፍች በሌላ ማንጸሪያ ስናየው ከሰው ልጅ የማጥናት እና የመጠናት ባህሪ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ስለሰው ልጅ ባህሪ የሚያጠናው ሰው ነው፡፡ አጥኚውን እንደ ስነምግባር/ሞራልን እንደሚመረምር/ ብንወስደው ተጠኚውን ደግሞ እንደ ግብረ-ገብነት/ ተመርማሪ/ ብንውሰደው በሁለቱ መካከል የሚኖረው የጊዜ ልዩነት ብቻ ይሆናል፡፡ (አጥኚና ተጠኚ የሚሆኑበት ጊዜ)፡፡ ተጠኚ የነበረው አጥኚውን ሊያጠና በሚችልበት ጊዜ የአጥኚውንመሰረታዊ ባህሪያት መላበሱ የማይቀር ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም የጋራ መነሻ መሰረትያላቸው ናቸውና፡፡ በዚህም ሁለቱም መሰረታዊ የባህሪ ተመሳሳይነት ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡ ሞራልንና ስነ-ምግባርን ስንወስድም ሁለቱም የሚሰሩት በሰው ልጅ ባህሪያት ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የሁለቱ ቃላት መሰረተ ትርጓሜም አንድ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በዚህ ጥናት ውስጥ  ሞራል በሚል የሚገኘው ቃል ስነ-ምግባር ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ፍች እንዲይዝ በማድረግ ግልጋሎት ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

ስነ-ምግባር ምንድን ነው? የሚለውን ሀሳብ ስንመለከት፣ በአንድ በኩል የድርጊትን እና የባህሪን ትክክልና ስህተትነት፣ ተገቢነትና ኢ-ተገቢነት መለየት የሚችልና በጉዳዮች ላይ ለመፍረድ የሚያስችሉ እሴቶችን የሚያዘጋጅ እና እነዚህ ውሳኔዎች እንዲለመዱ፣

እንዲያድጉና እንዲበለጽጉ የሚያግዝ ሲሆን፣ ውሳኔዎችና እሴቶች በተጣሱ ጊዜም ለጸጸት የሚዳርግ ህሊናዊ ባህሪ ነው፡፡ ስነ-ምግባራዊ መርሆች እለታዊ ህይወትን ማስሂጃ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መርሆች ከህግ የተካከለ ጸባይ እንዳለቸው Pojmaይገልጸል፡፡

“Morality is also closely related to law; and some people equate the two practices. Many laws are instituted in order to promote well-being, resolve conflicts of interest, and promote social harmony, just as morality does,…”(Pojman, 2005: 3) እንደፖጅማን ገለጻ ህግ ማህበራዊ ፍላጎትን በተገቢው መንገድ እንደሚያስተናግድ አጥፊን አርሞ ወደ እርቅ መመለስ እንደሚያስችል ሁሉ፣ ስነ-ምግባርም ተመሳሳይ ሂደትን ያደርጋል፡፡ በሁለቱ መካከል የሚኖረው ልዩነት ህግ በአስገዳጅነት የተደነገጉ ህጎችን ተፈጻሚ ሲያደርግ ስነ-ምግባር አእምሮ ላይ ተጽእኖ ፈጥሮ የሚሰራ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም የህግ “አድርግ አታድረግ” ድንጋጌዎች ከስነ-ምግባር መርሆች ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው እንደሆነ ለመረዳት ያስችለናል፡፡

Anderson የተባለው ምሁርም ስነ-ምግባርን የሰው ልጅ ጠባያት እና ተግባራት በጥቅል የሚገኙበትና የሚተረጎሙበት፣ የድርጊቶች ተገቢነትም እንደየማህበረሰቡ የአኗኗር መንገድ እና ባህል አንጻር የሚወሰንበት ወይም ብይን የሚያገኝበት ስርዓት ነው በማለት ይገልጸዋል (Anderson, 2013:165)

እንደ Hobbes አባባል ደግሞ ስነ-ምግባር የሰዎችን ባህሪ ለመግራት የተደነገገ የህጎች እና የእምነቶች ፍጹም መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ መመሪያውም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ የማህበረሰብ አባልም ሆነ ከማህበረሰቡ አባል ውጭ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን ማህበረሰቡ ከተለያዩ እይታዎች ተነስቶ የደነገጋቸውን እሴቶች ለማረም ወይም ለማስተካከል የሚፈቀድለት አይሆንም፡፡ ይህ ስነ-ምግባራዊ ደንብ የማህረሰቡ አባላት ያለፉትም፣ ያሉትም ሆኑ ወደፊት የሚመጡት ትውልዶች ያገኙትን የማህበረሰብ ደንብ እንዳለ የሚቀበሉ እንጅ ለማስተካካል ሙከራ የሚያደረጉበት እድል የላቸውም፡፡

በህገ ደንቡ የማይስማማ ወይም ከህገ ደንቡ ውጭ ተግባር የሚሰራ የማህበረሰብ አባል ካለም እንደ ሰይጣናዊ፣ ስህተተኛ እና አላዋቂ የሚቆጠር ይሆናል (Hobbes 1994:11)፡፡ Huriም ስነምግባርን ከዘመናዊ እሳቤ አንጻር ወስዶ፣ ውስብስብ ጉዳይ የሆነ የኀይማኖት፣ የባህልና የፍልስፍና ውህድ ነው በማለት ይገልጸዋል፡፡ ስነ-ምግባር ኀይማኖትን፣ ባህልን እና ፍልስፍናን መሰረት አድርጎ የሰው ልጅ ድርጊቶችን ስህተትና ትክክል መሆናቸውን የሚመረምርበት እና ፍርድ የሚሰጥበት ጽንሰ ሀሳብ ነው በማለት የሆቢን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ (Huri 1981:27)

በድሉ ዋቅጅራም የ/Manual Vilaasquez, et al/ን ሀሳብ በመውሰድ ስነ-ምግባርን በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፡፡

ስነ-ምግባር በሁለት ነገሮች ጥምረት የሚገለጽ ነው፡፡ በመጀመሪያ ስነ-ምግባር በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ የትክክለኛነትና የስህተት (right and wrong) ልኬት (standard) ነው፡፡

ይህ ልኬት ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና እንደ ሌለባቸው የውሃ ልክ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ዜጎች መብታቸው የት ድረስ እንደሆነ የሚያሳይ፣ ምን ግዴታ እንደተጣለባቸው፣ ለማህበረሰቡ እንዲያበረክቱ የሚጠበቅባቸው ምን እንደሆነ ይገልጻል፡፡

Valadimr Propp (1949/ Theory and history of folklore ህዝባዊ ታሪኮችን መሰረት በማድረግ ታሪኮች ሊነገሩ የሚችሉበትን የታሪኮችን ስነምግባር አጥንቷል፡፡ በዚህም ተረኮች ሊነገሩ የሚችሉት የዘመኑን ስነ ምግባር መሰረት በማድረግ እንደሆነና በታሪኮች ዉስጥም ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች መዳሰሳቸዉን ከይዘት አንጻር ይዳስሳል፡፡

Roman Ja kobsn(1969) language in literature የስነልቦና ባለሙያ ሲሆን የቋንቋ ምርምሩን አጠናክሮ በመቀጠል በዚያ ውስጥ የሰወችን ስነምግባር ምን አይነት እንደሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል ፡፡ በተለይም ስነ ምግባር ለሰዎች ስለ ሰዎች ባህላዊና ማህበራዊ ሁነቶች የሚዳስስ መሆኑን ይገለጻል፡፡

ስነምግባራዊ ሂስ የሁነቶችና ቅደም ተከተል የታሪክ፣ የእምነት፣ የባህል፣ ለኪነ-ጥበብ ውጤቶች ላይ የሚኖረው አስፈላጊነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም ወይም የጥናቱ ትልቅ አስተዋጽ አድርጎል ማለት ነዉ፡፡

ሚዛናዊነትን (fairness) ወይም ተለይተው የታወቁ ሰባዊ ጸጋዎችን (Virtue) ምሰሶው ያደረገ ነው፡፡ (በድሉ፣ 2011)

ከዚህ ሀሳብ መውሰድ የምንችለው የስነ-ምግባር ጉዳይ ሁለት ነገሮችን በትይዩ በአንድ ጊዜ ወስዶ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን እና የሌላቸውን እየለካ ደረጃ የሚሰጥ/የሚፈርጅ መስፈሪያ መሳሪያ ሆኖ ማገልገል እንደሚችል ነው፡፡

ስነ-ምግባር የሰዎችን ባህሪ የሚወክል ሲሆን፣ ስነ-ምግባራዊ ተግባራዊ ድርጊቶችን ይወክላል፡፡ በሌላ በኩል "ኤቲክስ" የሚለው ንድፈ ሀሳብ ሲሆን፣ ስልታዊ እና የሰዎችን ባህሪ ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ የሚመረመርበት ቃል ነው፡፡ (Churchill, 1982)

እንደ Rennie እሴቶች ከእምነቶችና አመለካከቶች ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸው በመሆናቸው፣ የሰው ልጆችን ባህሪ የሚገሩ ወይም የሚመሩ ናቸው፡፡ (Rennie,1982) እንዲሁም ስነምግባር፣ እሴት እና "ኤቲክስ" የሚሉት ቃላት ከባህላዊ፣ መንፈሳዊ እና ባህል ጋር በጠንካራ ሁኔታ እንደሚያያዙ (United Nations Educational Scientific and Cultural Organization, 1991).ይገልጻል፡፡

### 2.1.1.1 የስነ-ምግባር ፍልስፍና

*ስነ ምግባርን የዘርፉ ምሁራን እንደ ፍልስፍና መስካቸዉ የተለያየ ትርጋሚንና ፍችን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡በዚህም ጥቂቶችን እንደሚከተለዉ ለመቃኘት እሞክራለዉ፡፡*

ፍልስፍና የተለያዩ ርእዮት ያሉት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአይነት ደረጃ ግን በቁጥር ለማስቀመጥ ቢያስቸግርም፣ ሚለር በስድስት ይከፍላቸዋል፡፡ “Not all lists of philosophy would agree, but most of them would almost certainly include six: metaphysics, epistemology, value - theory, ethics, aesthetics, and logic” (Miller, 1984:5) ከላይ ከተጠቀሱት የፍልስፍና አይነቶች የእኔ የጥናት “መታገኒያ” ሆኖ የሚያገለግለው የስነ-ምግባር ፍልስፍና ነው፡፡

Moral philosophy refers to the systematic endeavor to understand moral concepts and theories. It under takes to analayze concept and terms, such as right, wrong, permissible, ought, good and evil in their moral contexts. Moral philosophy seeks to establish principles of right behavior that may serve as action guides for individuals and groups. It investigats

which are paramount to a worth-while life or society. It builds and scrutinizes argmenets in ethical theories. (pojman, 2005:2)

እንደ ፖጅማን አገላለጽ የስነ-ምግባር ፍልስፍና ስነ-ምግባርን ለመመርመር የሚያስችሉንን ንድፈ ሀሳባዊ እና ጽንሰ ሀሳባዊ ዘዴዎችን ለማዘጋጀት የሚሞክር ነው፡፡ የሚወስዳቸው ጽንሰ ሀሳባዊ ወይም ቃሎች ማለትም፣ ትክክልና ስህተት፣ የሚፈቀድና የማይፈቀድ፣መሆን ያለበትና የሌለበት፣ መልካም እና መጥፎ የሚሉ ቃላትን ከየራሳቸው አውድ በመነሳት/ከተመሰረቱበት ማህበረሰብ አተያይ/ እየወሰደ ይመረምራል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ማህበረሰብ የሚገነባበት እሴት የተለያየ በመሆኑ ነው፡፡ ስነ-ምግባራዊ ፍልስፍና ግለሰቦች እና ቡድኖች ድርጊታቸውን የሚመሩበት ትክክለኛ/እንደየማህበረሰቡ ባህል ይወሰናል/ መርህ መመስረት ይፈልጋል፡፡

ይህም ድርጊቶች ወደመጥፎ አቅጣጫ እንዳይሄዱና ቅርጽ ለማስያዝ ከማሰብ የሰዎች አተያይ ይመነጫል፡፡ የሰዎችን ወይም ማህበረሰቦችን የሰላ ህይወት መኖር አለመኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡ በስነ-ምግባር ዙሪያ የሚደረጉ የተቃርኖ ሀሳቦችን በቅርበት ይመረምራል፡፡ የስነምግባር ፍልስፍና ስነ-ምግባራዊ አውድ የሚፈጠርበት የፍልስፍና አይነት ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥም በርካታ የስምምነት መስመሮችን በመዘርጋት እንዴት ተግበራዊ እንደሚሆኑ ይመረምራል፡፡

*(ስል የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ መጽሄት በቅጽ ሁለት በቁጥር ሁለት ላይ የሰነ-ምግባርን ፍልስፍና በ ሶስት በመክፈል ያብራርል፡፡*

*ስነ ምግባር ኤቲኮስ ወይም ኤቶስ ከሚለዉ ከግሪክ ቃል የመነጨ ሲሆን ባህሪ ወይም ጠባይ ማለት ነዉ፡፡ይህም ትኩረቱ በተለይ ለሰዎች ስለ ሰዎች የሆነ የፍልስፍና ጥናት አንዱ ዘርፍ ሲሆን ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡*

*አንደኛ የቢሆን ስነ ምግባር (normative ethicse) ምግባራችንንና ተግባራችንን ምን መሆን ይገባወዋል፣ምን ማድርግ ይገባኛል እንዲሁም ምን አይነት ባህሪ ሊኖረኝ ይገባል የሚሉ እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ መሻት በጎ ምግባርን እንድናንጽ መልካም ተግባሮችን እንድናከናዉን ያሳዉቀናል፡፡*

*ሁለተኛ ልዕለ ስነ ምግባር ሁለገብና ከፍተኛ ስነ ምግባራዊ ጥያቄዎችን እንድናነሳና ትንታኔ እንድናደርግ ይጠቅመናል፡፡ስነ ምግባር ከየት መነጨ ለዉሳኔዎቻችን በእርግጥ የየገላችን ምርጫዎች አሉን ስነ ምግባራዊ ይዘት በማህበራዊና በባህላዊ አስተሳሰብ ላይ ተመስርተዉ የታነጹ ናቸዉን ስነ ምግባራችን ከገል ጥቅም ጋር የተያያዙ ናቸዉን በግሌ ጥቅም ላይ ተመስርተዋልን እና የመሳሰሉትን ሁለንተናዊ ጥያቄዎች አንስትን በልቦናችን እንድንመረምር ይረዳናል፡፡*

*ሶስተኛዉ ገቢራዊ ስነ ምግባር በተቀዳሚ ግብረ ገባ ጉዳዮችና በግብረ ገባዊ አጣብቂኞች ላይ በግልና በሙያዊ ሂወት የሚቀላቀሉና መፍትሄ የሚያስፈልጋቸዉ ችግሮች ላይ እንድናተኩርና መልስም እንድንልግሳቸዉ አቅጣጫ ያሲዙናል፡፡ በማለት ያብራራል፡፡*

*በዚህም ስነ ምግባር ትኩረቱ በሰዎች ላይ ተመስርቶ ስለ ሰዎች ባህሪና ጠባይ፣ማህበራዊ ና ባህላዊ ሂወት የመሳሰሉትን ሁለንተናዊ ጥያቂዎች በልቦናችን እንድንመረምር ስነ ምግባራዊ ይዘትን የሚያላብሰን እንደሆነ ያብራራል፡፡*

### 2.1.1.2. የሥነ-ምግባር ንድፈ-ሀሳቦች

#### 2.1.1.2.1.የዲኦንቶሎጂካል (ሁለንተናዊያን) ንድፈ-ሀሳብ

የዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች፣ ትክክል ወይም ስህተት የሚባሉት ድሪጊቶች ከውጤት ጋር ተዛምዶሽ የላቸውም ብለው የሚሞግቱ ናቸው፡፡ የድርጊት ውጤት ከድርጊቱ መልካምነት ወይም መጥፎነት ጋር ግንኙነት የለውም ብለው ያምናሉ፡፡ የድርጊት ወይም ጠባይ ስነ-ምግባር የሚለካው የራስን ግዴታ በአግባቡ ከመወጣት አለመወጣት ጋር ተያይዞ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው፡፡

እንደግዴታ የሚወስዱትም ቃል ኪዳንን መጠበቅ፣ እውነት መናገር፣ የሰው ንብረትን አለመፈለግ፣ በሌሎች ላይ ጉዳት አለማድረስ፣ እኩይ ድርጊት አለመፈጸም በምትኩ መልካም ነገሮችን ማድረግ የሚሉትን ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህን ግዴታዎች ለሰው ልጆች በሙሉ አስፈላጊዎች በመሆናቸው ሁሉም ሊጠብቃቸው ይገባል የሚል እምነት አላቸው፡፡

በዚህም የንድፈ ሀሰቡ አራማጆች ሁለንተናውያን እየተባሉ እንዲጠሩ አስተችሎቸዋል፡፡ ጠና የኢማኑኤል ካንትን ሀሳብ በመውሰድ እንደሚገልጹትም፡-

“ድርጊት የሚፈጸመው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው የራስን ፍላጎት ማርካት ሲሆን፣ ሁለተኛው የራስን ግዴታ መወጣት ነው፡፡ ያንድ ድርጊት ግብረ-ገባዊ እሴት የሚለካው ድርጊቱ ለአድራጊው በሚያስገኘው ውጤት ወይም በአድራጊው ተፈጥሮና ማህበራዊ ደግነት ሳይሆን፣ አድራጊው ራሱን ለግብረ ገብነት ህግጋት ለማስገዛት ባለው ሙሉ ፍቃድ ነው፡፡ በጎ ፈቃድ ከምንም ቅድመ ሁኔታ ነጻ የሆነ ነው፡፡ ጠና፣ (2009፣ 147)

በዚህ አረዳድ እኩይ እና በጎ ተግባራት መለካት የሚችሉት የመጨረሻ ግብንና የሚገኝን ጥቅም ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ከልብ በመነጨ ስነ-ምግባር መልካም ነገሮችን ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው፡፡ መልካም ነገር ወይም ትክክለኛ ስራ ምን ማለት ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ለዚህም Pojman መልስ አለው፡፡ እንደ ፖጅማን አገላለጽ የአንድ ድርጊት ትክክለኛነትና ስህተትነት ሊወሰን የሚችለው ስራው በሚያስገኘው የመጨረሻ ውጤት አይደለም፡፡ ውጤቱ ጥሩም ይሁን አይሁን የድርጊቶችን ሁኔታ ሊወስንልን አይችልም፡፡

“The end never justifies the means. For example, there is something right about truth telling and promise keeping, even when such actions may bring about some harm; and there is something wrong about lying and promise breaking, even when such actions may bring about good consequences. Acting unjustly is wrong even if it will maximize expected utility. (Pojman, 2005:137-138)

እንደፖጅማን እሳቤ በማህበረሰቡ ውስጥ እውነትነት ያላቸው፣ እውነት መናገር፣ ቃልን መጠበቅ የሚሉ እሴቶችን በጽናት ይዞ መቀጠል እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ ቃልን በመጠበቅ፣

እውነትን በመናገር ችግር የሚያመጣ ሆኖ ቢገኝ እንኳን ችግሩን ለማለፍ ተብሎ በመዋሸት፣ ቃልን ባለመጠበቅ ከችግሩ ለመውጣት የሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ተገቢነት እንደሌለው ያስረዳል፡፡ "የምትሞትን ነፍስ ዋሽተህ አድናት" የሚለው የአበው ብሂልም በዚህ ንድፈ ሀሳብ ተገቢነት የለውም፡፡ በመዋሸት፣ ቃልን በማጠፍ የሚገኘው ውጤት የቱንም ያህል፣ መልካም ቢሆን፣ ምን አልባትም ግኝቱ የእርካታ ጫፍ ላይ የሚያደርስም ቢሆን፣ ድርጊቱ እንደስህተት እንጅ እንደትክክል ሊቆጠር አለመቻሉን እንረዳለን፡፡ የአንድን ነገር ድርጊት ስህተትና ትክክል የሚለውን ለመለካት የመነሻ እሴቶቹ "መጣስ አለመጣስ" እንጅ እሴቶቹ ተጥሰው የሚገኘው መልካም ውጤት አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.1.2.2 የቴሊኦሎጂካል ንድፈ ሀሳብ

ይህ ንድፈ ሀሳብ አላማ መር ንድፈ ሀሳብ ወይም ውጤት ተኮር ንድፈ ሀሳብ እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህም አንድ ድርጊት ከስነ-ምግባር አንጻር በመጥፎ ወይም በመልካም ሊፈረጅ የሚችለው ድርጊቱ የተፈለገውን ግብ መምታት አለመምታቱን በመመልከት ነው የሚል ሀሳብ የሚያራምድ በመሆኑ ነው፡፡ ማንኛውም ድርጊት የታለመውን ግብ የሚመታ ከሆነ መልክም፣ ተገቢነት ያለው ሲባል፣ በተቃራኒው ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ተገቢነት የሌለው፣ እኩይ ተብሎ ሊጠራ ይችላል የሚል እምነት ያላቸው ናቸው፡፡ በቴሊኦሎሎጂካል ንድፈ ሀሳብ ድርጊቶችን ለመፈረጅ ትልቅ መስፈርት ተድርጎ የሚወሰደው በየትኛውም መንገድ ታልፎ ከሚመጣው ውጤት ላይ ነው፡፡ "... teleological systems see the ultimate criterion of morality in some non moral value that results from acts,... For example, a teleologist would judge whether lying was morally right or wrong by the consequences it produced..." (Pojman, 2005:110)

እንደ ፖጅማን ገለጻ የቴሊኦሎጂካል ንድፈ ሀሳብ ኢ-ስነ-ምግባራዊ በሆኑ እሴቶች ውስጥ ታልፎም ሳይቀር፣ ግብን የሚመታ ድርጊት ሁሉ በስነ-ምግባር እይታ ትክክል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የውሸትን ተግባር ከሚያስገኘው ውጤት አንጻር ተመልክተነው ስህተት ወይም ትክክል ልንለው እንችላለን፡፡ በመዋሸታችን የምናገኘው ውጤት ጥሩ ከሆነ መዋሸት በግብረ-ገብ ወይም በስነምግባር አይን ትክክል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ውጤቱ በተቃራኒው ከሆነ ደግሞ ስህተት ተድርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ አረዳድ ማንኛውም ነገር ፍጹም እውነት ፈጹምም ስህተት ወይም ፍጹም ጠቃሚ ወይም የማይጠቅም አድርጎ መውሰድ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ወይም የመነሻ ቅድመ ሁኔታዎችን እንደ ዲኦንቶሎጂካል ንድፈ ሀሳብ አይመለከትም ማለት ነው፡፡

### 2.1.1.2.3 ቨርቹ ኤቲክስ (መልካም ስነ-ምግባር)

ቨርቹ ኤቲክስ እንደ ዲኦንቶሎጂካል ግዴታ ተኮር ወይም እንደ ቴሊኦሎጂ ድርጊት ተኮር ባህሪ ያለው አይደለም፡፡ ሁሉም ነገር ከጥሩ ባህሪ የሚመጣ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ጥሩ ባህሪ ያለው ሰው ሁልጊዜም መልካም ነገሮችን የመስራት ተምኔት ያለው ነው ብሎ ያምናል፡፡

ፖጅማን እንደሚገልጸው ቨርቹ ኤቲክስ ትኩረት የሚያደርገው ሆኖ መገኘት ላይ ነው፡፡ በተለምዷዊው ግዴታ ተኮር ስነ-ምግባር ውስጥ ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ የሚል የድርጊት ጥያቄ ሲጠየቅ፣ በቨርቹ/መልካም ስነ-ምግባር/ ውስጥ ግን ምን አይነት ሰው ነው መሆን የሚገባኝ የሚል የመሆን ጥያቄ የሚነሳበትና መልስ የሚያገኝበት ነው፡፡

ቨርቹ ኤቲክስ በራሳቸው ብርሃን የስነ-ምግባር ገጽታን እንደ እንቁ የሚያብረቀርቁ ሰዎችን፣ እንደነ ሙሴ፣ ኮንፊሼየስ፣ ሶቅራጥስ፣ አርስቶትል፣ ቡድሃ፣ እየሱስ፣ አብርሃም ሊንከን የመሳሰሉትን በምሳሌነት ይጠቅሳል፡፡ እነዚህም ስነ-ምግባርን ራሳቸውን ምሳሌ አድርገው ያስተማሩ እንደሆኑ በማዘከር ስነ-ምግባር የሚይዙት (ሆነው የሚገኙት) እንጅ የሚማሩት ብቻ እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡ አድርግ አታድርግ በሚል መመሪያን ማውጣትና ማስተማር ብቻውን እንደማይገባም "…these are role models, who teach us all what it is to be moral by example, not by precept." (Pojman, pp, 166) በማለት የሚገልጹት ሆኖ ማሳየት እንጅ መመሪያን አውጥቶ የሚደረግ የማይደረግ በሚል ማስተማር ብቻ በቂ አለመሆኑን ነው፡፡ እንደጠናም "ቨርቱ ኤቲክስ ጥረት የሚያደርገው እጅግ የላቀ ባህሪ ያለው ሰው መፍጠርን ወይም መቅረጽን ነው፡፡ ዋና አላማውም ለሰው ልጅ የሚልቅ ባህርይን ማጎናጸፍ ነው፡፡" ጠና፣ (2009፣102)

### 2.1.1.3 የሀይማኖትና የስነ-ምግባር ዝምድና

በሀይማኖት እና በስነ-ምግባር መካከል ያለው የጠበቀ ግንኙነት አንዱ በአንዱ ላይ ተጽእኖ መፍጠር እንደሚችል የሚያስረዱ የፍልስፍና ሰዎች ቢኖሩም፣ ሀይማኖትን ከስነ-ምግባር ነጥሎ ለመመልከት ሙከራ የሚያደርጉ ሊቃውንትም አልጠፉም፡፡

እንደ (Quarcoopome, 1987፡154) ገለጻ በተለምዷዊ ሀይማኖት (traditional religion) አተያይ ስነ-ምግባር የሀይማኖት ፍሬ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ Aghaም ሀይማኖትና ስነ-ምግባር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው በመግለጽ የQuarcoopome ሀሳብ ይደግፋል፡፡ (Agha,2003:43)

የስነ-ምግባር ፍልስፍናን ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚገልጹ በርካታ ምሁራን ናቸው፡፡ ሃይማኖት ከሌለ ስነ-ምግባር የሚባል ነገር እንደማይኖርም ያስረዳሉ፡፡ ስነ-ምግባር እስካሁን የሃይማኖት የአንጎል ክፍል ወይም ከአስፈላጊ የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ ነጥሎ ማየት እንደማይቻልም ያስረዳሉ፡፡ በዚህም ሃይማኖተኛ የሆነ ሰው በተመሳሳይ ስነ-ምግባራዊ (መልካም ባህሪ ያለው) ነው በማለት እውነታነቱን ያጸድቃሉ፡፡ የስነ-ምግባር ህይወት ምን አልባት ከሃይማኖት ውጭ ሊታሰብ አይችልም ወደሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርሱ የፍልስፍና ሰዎችም አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአለም ላይ ቤተ-እምነቶች የሚበዙ ከሆነ አለም የተዋበች ቦታ ትሆናለች የሚል እምነት ያላቸው ናቸው፡፡

በግሪክ ፈላስፎች እይታ ቡዲሂዝም፣ ክርስትናና ሌሎች ሀይማኖቶች ከስነ-ምግባር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሊነጣጠሉ የማይችሉ እና አንድ ማእከል ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ በግሪክ ፈላስፎች ዘንድ የሚነሳ ትልቅ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም የሶቅራጥስ ጥያቄ ሲሆን፣

መልካምነት በአማልክቶች ዘንድ የሚወደድ ነው፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው? መልካም ስለሆነ ነው ወይስ መልካምነት መልካም የሚሆነው በአማልክቶች ስለሚወደድ ነው? የሚል ነው፡፡ (Kelechi, 2018:43) በጥናቴ ዉስጥም ይህንን ሃሳብ ለመተንተኛነት የምጠቀመዉ ይሆናል፡፡

ሌሎች ሊቃውንት ግን ስነ-ምግባርን ያለ አምላክ የማይታሰብ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ Dostoevsky "ፈጣሪ ከሌለ ማንኛውንም ነገር ልንሰራ እንችላለን" ይላል፡፡ ሁሉን ማድረግ ሲል፣ የሰው ልጅ ለስሜቱ ተገዥ ሆኖ የሚፈጸመውን ድርጊት ሁሉ የሚያካትት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስሜት ደግሞ የህግንም ሆነ የስነ-ምግባር ደንቦችን የሚጠነቀቅና ተገዥ ስላልሆነ የስሜት ውላጅ የሆኑ ተግባራት ኢ-ስነ-ምግባራዊ መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡

ጀርመናዊው ኒቼ ግን ይህን ሀሳብ አይቀበለውም፡፡ ስሜትን ተከትሎ ተግባር መፈጸም እንዳለበት ያምናል፡፡

ከዘመናዊ ፍልስፍና ቀደም ብሎ ሀይማኖት ያለ ስነ-ምግባር ተነጥሎ ሊገኝ እንደማይችል ሁሉም የሚስማማበት ሀሳብ ነበር፡፡ ይህም ያለ ሃይማኖት ስነ-ምግባርም እንደሌለ ይገልጻል፡፡ "Before the modern period of philosophy, it was generally agreed that religion is the indisputable foundation of morality, thereby implying that without religion there can be no morality." በተመሳሳይ ሀይማኖት ለስነ-ምግባር መገኛ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ የሚደግፉት Laura Schlesinger "morality is impossible without belief in God" በማለት በእግዚአብሔር የማያምን ስነ-ምግባር ሊኖረው እንደማይችል ይገልጻሉ፡፡ Zuckerman ደግሞ "declining moral standards are at least partly attributable to the rise of secularism and decline of organized religion."በ (Kelechi, 2018:42 ውስጥ የተጠቀሰ) የስነ-ምግባር መውረድ "ሴኩላሪዝ"ም እንዲያድግ እና የደረጀ ሀይማኖት እንደይኖር ከፊል አስተዋጽኦ አለው በማለት የስነ-ምግባርን ቀጥተኛ ተዛምዶሽ ያጠናክራል፡፡

እንደ Kelechi አባባል ግን በዘመናዊ ፍልስፍና ከላይ የተገነቡት ሀሳቦች በተቃርኖ ስር የሚወድቁ ናቸው፡፡ ዘመናዊ ፈላስፎች በተጨባጭ እንደሚያስረዱት የብዙ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ እና ልምዶች ከስነ-ምግባር ፈተና የወደቁ ወይም ስነ-ምግባር የራቃቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ስነ-ምግባርን ለመገንባት የግድ ሃይማኖትን አስፈላጊ አድርጎ መውሰድ በቂ አይደለም በማለት ሃይማኖት ለሥነ-ምግባር ያለውን መሰረትነት ያጣጥሉታል፡፡ ይህ የዘመናዊ ፈላስፎች እይታ ደግሞ ለዘመናት ስነ-ምግባር መለኮታዊ መሰረትነት ያለው ነው፤ እግዚአብሔር (አላህ) ሰውን ሲፈጥረው ከስነ-ምግባር አስተውሎት ወይም የሰው ልጅ መልካምና መጥፎውን፣ ትክክልና ስህተቱን፣ እንክርዳዱን ከስንዴ የሚለይበት እውቀት ያለው አድርጎ ነው የሚለውን ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የሚቃረን ይሆናል፡፡

ለዚህ ማረጋገጫ ሆኖ የቀረበው ደግሞ የዘመናችን የስነ-ምግባር ጥያቄ ውስጥ መውደቅ ነው፡፡ በዘመናችን ቤተ እምነቶች በቁጥር ቢያሻቅቡም፣ የስነ-ምግባር ውድቀት ከሃይማኖት ችግር ጋር እንደሆነ ትልቅ ተቃውሞ ይስተጋባል፡፡ ሃይማኖት ስነ-ምግባርን በመቅረጽ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ካለው፣ ለምን በዘመናችን እልቆ ቢስ በሆኑ ቤተ እምነቶች በየጥጉ በግልጽ

እየተሰበከ የሥነ-ምግባር ዉድቀት ይመጣል የሚል ትልቅ ጥያቄ ይነሳል፡፡ (Kelechi, 2018:43) ይህም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ነው፡፡

በድሉ ዋቅጅራም "ጠርዝ ላይ" በሚለው መጽሐፉ የስነ-ምግባርን እና የሃይማኖትን መለያየት ሲያስቀምጥ፣

"...ስነ-ምግባር ከሃይማኖት በላይ ሰፊ ነገር ነው፡፡ ሃይማኖት የስነ-ምግባር አቻ ብያኔ ወይም መስፈሪያ ከተደረገ ሃይማኖተኛ ያልሆኑ ሰዎች የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ስነ-ምግባር ሰዎች ሃይማኖተኛም ሆኑ ሃይማኖተኛ ያልሆኑ፣ ሊኖራቸው የሚገባ እሴት ነው" (ገጽ፣145) በማለት አንድ አለመሆናቸውን ያስረዳል፡፡

በሌላ በኩል የቤተ እምነቶች እና የስነ-ምግባር እንቅስቃሴ የተቀራረቡና የተሳሰሩ እንደሆኑ የሚገልጹት ጠና ናቸው፡፡

ልማዳዊ ኃይማኖቶች፣ ቤተክርስቲያን፣ መስጊድና የመሳሰሉት የእምነት ተቋሞችና የማምለኪያ ቦታዎች፣ ጠቃሚ የሆኑ የግብረ-ገብ ስፍራዎች ናቸው፡፡ ...ሃይማኖቶች የሚሰሩትና የሚያሰርጹት በዋናነት፣ ሃይማኖታዊ ቀኖና ቢሆንም፣ ግብረገብን ለሃይማኖታዊ ግባቸው መጠቀም ግን ግድ ነው፡፡ ...በሰዎች መካከል መረዳዳት፣ መከባበር፣ መተዛዘንና መተጋገዝ እንዲኖር፣ ደግነትና ርህራሄ እንዲሰፍን፣ የአካል የአእምሮና የህሊና ንጽህናና ጥራት እነዲዳብር፣ ያረጁና የደከሙ የደኸዩ ወገኖችን መርዳት እንዲጎለብት ይጥራሉ፡፡ ጠና፣ (2009፣210)

የጠና አገላለጽ በሌላ አንጻር ስንመለከተው የአብዛኞቹ ቤተ እምነቶች ዓላማ ክፋት፣ ምቀኝነት፣ ሌብነት፣ ምዝበራ፣ ዝርፊያ፣ ቃለ-አባይነት፣ ውሸት፣ በሀሰት መመስከር፣ ሴሰኝነት፣ የሰው ነፍስ ማጥፋት የሚሉትን እኩይ ተግባራት ማምከን የሚል ይሆናል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያውያን መገለጫ ነው፡፡ የጠና ሀሳብ ግን ቀጠይ ለትንታኔ በተያዙት ልቦለዶች ውስጥ የሚስተዋል ይሆናል፡፡

የስነ-ምግባር ፍልስፍና ጥናት ስለ ስነ-ምግባር ህልውና፣ መገኛ እና መሰረት የሚያካትት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሲጠና ደግሞ ስለ ስነ-ምግባርና ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ለማወቅ መሰረት ይጥላል፡፡ የስነ-ምግባር ንድፈ ሀሳቦች መሰረታቸው በሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ላይ ነው፡፡ "Fortunately, there are moral theories that are based on the concept of human nature or a natural way and they can be used by those employing this method." (LaBossiere, 2012: 39) በሚል ያሰፈራቸው የሰው ልጆችን ባህሪ የታከኩ ናቸው፡፡ ስለ ስነምግባር ለመመርመር የተለያዩ የመታገጊያ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም ማጥናት ይቻላል፡፡ ንድፈ ሀሳቦቹ ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር ተዛማጅ መሆን ግን ይኖረባቸዋል፡፡

### 2.1.1.4. ስነ-ጽሑፍና ስነ-ምግባር

ሃያኛው ክፍለ ዘመን ዝንቅነት የተሞላበት ዓለም ነው፡፡ አንዱን ከአንዱ ለይቶ ለመመልከት አያስችልም፡፡ ቀደምት እንደነበሩት የመስኩ ምሁራን ድንበር ያበጀ የጥናት መስክ ላይ መሰማራት በዚህኛው ዘመን  ውጤቱ የልፋቱን ያህል ችግር ፈች አይሆንም፡፡ ከዚህ ይልቅ ድንበሩን ጥሶ የተለያዩ መስኮችን በአንድ ላይ አጣምሮ መመልከቱ የሚያስገኘው ውጤት ሚዛን የሚደፋና መፍትሄ በመሆንም ልዩ ግምትን እያገኘ መጥቷል፡፡ የተለያዩ መስኮችን ወስዶ በአንድ ላይ ለማጥናት ደግሞ እንደስነ-ጽሑፍ መስክ ሰፊ አይገኝም፡፡ ስነ-ጽሑፍ የሠው ልጅ ጉዳዩ በመሆኑ ከስነ-ምግባር ጋር የቅርብ ዝምድና እንደነበረው እና አሁንም ያለው ስለመሆኑ፣ Karim ያስረዳል፡፡

"Literature - morality relation has remained a point of vital critical debate since the ancient civilization. In the twentieth Century this question has continued to inspire critical debate despite phenomenal decline in religious and moral aspect of life. But literature and morality relationship is complex and oscillates between complete interdependence to dissociation of such a relation." (Karim, 2012:186)

ካሪም የሚገልጸው ከጥንት ስልጣኔ ጀምሮ እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የስነ-ጽሑፍና ስነምግባር ጉዳይ ዋና የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ እንደዘለቀ ነው፡፡ በሃይማኖታዊና ስነ-ምግባራዊ ህይወት ውስጥ አስደናቂ ክስተቶች የቀሩ ቢሆንም፣ ጥያቄው ግን መከራከሪያ ሆኖ መቀጠሉን ይገልጻል፡፡ የስነ-ጽሑፍና ስነ-ምግባር ግንኙነት ግን ውስብስብ እንደሆነ እና በመካከል ያለው ዑደትም ለመለየት የማይቻል መሆኑን ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም Karim የ Mathew Arnoldsን ሀሳብ በመውሰድ፣ ግጥም ከሀይማኖትም ከፍልስፍናም በላቀ መልኩ የchrished ideals of beauty and intelegenceን ለመቅረጽ እንደሚውል ይገልጻል፡፡ Recardes "poetry and belief" በሚለው ጽሑፋቸው ሳይንስና ሀይማኖት በአለም የሚኖሩ ህዝቦችን ስነ-ምግባርና ማህበራዊም ሆነ ግላዊ ህይወትን ለመቆጣጠር አቅማቸው ደቋል፡፡ ስነ-ጽሑፍ ግን ለዚህ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፤ ማህበራዊም ሆነ ግላዊ ህይወትን እንዲሁም ስነ-ምግባርን ለመቅረጽ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ያስረዳል፡፡ በ(Karim,2012:186) ውስጥ የተጠቀሰ፡፡ በሌላ በኩል Eldridge እንደሚለው

"A person's moral understanding can not be captured by general theories, but must be developed and sustained by an awareness and relation of her story to the stories of others, an awareness that literature is peculiarly well placed to articulate and extend" (Eldridge,1989፡20)

እንደ Eldridge የሰው ልጅን የስነ-ምግባር ግንዛቤ እንዲሁ በተጠቃለለ ንድፈ ሀሳብ መጨበጥ አይቻልም፡፡ የስነ-ምግባር ግንዛቤን ለማዳበርና ቀጣይነቱንም ለማረጋገጥ ታሪክን ከታሪክ እያገናኙ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ስነ-ጽሑፍ በግልጽ ለመናገርና ለማስፋት ልዩ ጸባይ/ባህሪ እንዳለው ያስረዳል፡፡ art and morality "relationship is complex and

oscillates between complete interdependence to dissociation of such a relation." በስነ-ጥበብና በስነ-ምግባር መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ እና ፍጹም በመደጋገፍ ዑደት ውስጥ ያለውን ለመለየት እስከሚያስቸግር ድረስ ትስስር እንዳላቸው ይገልጻል፡፡ በስነ-ጽሑፍ ውስጥ የምስል /ገጸባህሪያት ውክልና/ እንቅስቃሴ፣ በውበት ላይ የቅርጻውያን አተኩሮ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት የስእልና የሙዚቃ ስራዎች በአጠቃላይ ስነ-ጥበብ የጋራ ስነምግባርን በመቅረጽ በኩል ትልቅ ድርሻ እንደነበራቸው ያስረዳል፡፡

በዘመናዊ የስነ-ጽሑፍ ሀያሲዎች ሳይቀር ግጥሞችና ልቦለዶችን በሚመረምሩበት ጊዜ ትኩረታቸው ግጥሞችና ልቦለዶቹ ከያዙት ስነ-ምግባራዊ ዓላማ አንጻር ነው፡፡ "writes Hyman modern criticism has emphasized the autonomy of the poem and the novel from their moral purposes" እንዲሁም "… tragedy is based on the belief that this kind of literature will have a negative influence on human morality" (Karim, 2012:186)

የካሪም ገለጻ ስነ-ጽሑፍ እንደተጻፈበት የእምነት ወይም ባህል አንጻር በስነ-ምግባር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ለመረዳት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም አሳዛኝ ታሪኮች የሚዋቀሩት ህግን በተላለፉ ወይም ከስነ-ምግባር ደንብ በወጡ ገጸ ባህሪያት ድርጊት ላይ ተመርኩዘው በመሆናቸው ነው፡፡

"The changing face of moral visiton in the amharic novel" በሚል ርዕስ የቀረበው የዶክተር Tena Shale ጥናት የሚያረጋግጠውም ይህን የስነ-ምግባርንና የስነ-ጽሑፍን የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡

As can be perused from existing accounts of the origin and development of Amharic literature, morality continues to be the central concern of the Ethiopian writer. This is attested by many scholars who researched into the early stages of the literature, chief among whom are S.Wright (1963), A. Gerard (1968, 1971), T.L.Kane (1975), and R.K.Molvaer (1980). Tena, (2007,4)

ጠና በእውቅ ሊቃውንት በS.Wright (1963), A. Gerard (1968, 1971), T.L.Kane (1975), and R.K.Molvaer (1980). የተጠኑትን ጥናት ዋቢ አድርጎ እንደገለጸው የአማርኛ ስነ-ጽሑፍ ከመሰረታዊ እሳቤ ጀምሮ እያደገ በመጣበት ሂደት ሁሉ ስነ-ምግባር የኢትዮጵያዊያን ደራሲዎች ዋና የትኩረት ማእከል ሆኖ እንደዘለቀ ያስረዳል፡፡ እንደ ጠና ገለጻም የኢትዮጵያን ደራሲወች መልካሙን በማመስገን ክፉውን ደግሞ በመቃወም የተሰሳተችን ነፍስ በመታደግ በኩል ባለ ውለታ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን የተለመደ አካሄድ በማጽደቅ በኩል ከፍተኛ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በTena 2007 ገጽ 4 ውስጥ የተጠቀሰ)፡፡

Molvaer በበኩሉ ከ1923 -1974 ያለውን የስነ-ጽሑፍ ጉዞ በማጥናት የአንድ የስነ-ጽሑፍ ስራ የስነ-ምግባርን ጉዳይ ቀዳሚው ያደረገ ከሆነ ብዙ የአማርኛ ስነ-ጽሑፎች ከበሬታ

እንደነበራቸው አመላክቷል፡፡ Having studied the literature of the period, 1923 - 1974, Molvaer also points out that "a preoccupation with moral issues… is prominent in much of Amharic literature." (ገጽ፣4). Tena በተጨማሪም የሞልቤርን ሀሳብ ወስዶ በሚከተለው መልኩ አስቀምጦታል፡፡

"It is worth noting that the pioneers, namely Afeworq Gebreyesus and Heruy Woldeselasse, who introduced the art of writing the novel into the literature, dedicated their works to the purposes of upholding and teaching morality". Tena, (2007, 4)

ጠና እንደሚገልጸው በኢትዮጵያ ውስጥ በስነ-ጽሑፍ ፈር ቀዳጅ የሆኑት አፈወርቅ ገብረየሱስ እና ኅሩይ ወልደ ስላሴ የልቦለድ አጸጻፍ ጥበብን ከስነ-ጽሑፍ ጋር ያገናኙ እንደሆኑ የስነ ጽሑፍ ስራቸውም ለአንድ ነገር ዓላማ መዋል እንዳለበት፣ ይኸም ስነ-ምግባርን መደገፍና ማስተማር ላይ ትኩረት ያደርጉ እንደነበር ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል Nargis Khan "Role of

literature in moral development" በሚለው መጣጥፉ ውስጥ የስነ-ምግባር አስተምህሮ በስነጽሑፍ እንደሚሰጥ ይገልጻል፡፡

Modern educators are utilizing the literature in a multi dimensional approach for improving society, behavior development, problem solving skills and right attitude to handle social situations. By narrowing it can be said that literature is simply promoting moral literacy. … literature and literary works are playing very crucial role in shaping and cultivating our beliefs, cultural, aesthetic and moral senses. (Nargis Khan,2014,6-7)

እንደ ናርጊስ ገለጻ ዘመናዊ አስተማሪዎች ስነ-ጽሑፍ የማህበረሰብን ህይወት ለማሻሻል፣ ባህሪን ለማሳደግ፣ ችግሮችን የመፍታት ችሎታ እና ትክክለኛ አመለካከት፣ እንዲሁም መህበረሰብን በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል መጠነ ሰፊ ቅርርብ ያለው መሆኑን ይገልጻል፡፡ የስነ-ጽሑፍን ተግባር በጠበበ መልኩ ካየነው ሲያንስ ቢውል በቀላሉ የስነ-ምግባር ትምህርትን ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ናጊስ በተጨማሪም ስነ-ጽሑፍና ጽሑፋዊ ስራዎች የአምልኮ ስርዓትን፣ ባህልን፣ ውበትንና ስነ-ምግባራዊ ስሜቶችን በመቅረጽ በኩል ዋና ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን አውስተዋል፡፡

የዚህ ጥናት አካል በሆኑት ልቦለዶችም የሚፈተሸው ይህን የስነ-ምግባር ጉዳይ ባነጻጸረ መልኩ ነው፡፡

### 2.1.1.5 ኢትዮጵያዊ ስነ-ምግባር

ጥናቱ ኢ.ትዮጵያዊ በሆኑ ደራሲዎች የተጻፉትን ልቦለዶች ስነ-ምግባራዊ ይዘት መፈተሽ ስለሆነ፣ ስለኢ.ትዮጵያዊ ስነ-ምግባር ምንነት በጥልቀትም ባይሆን በግርድፉ ማውሳቱ ለአንጽሮት ስለሚረዳን ተገቢነት አለው፡፡ ለመሆኑ ኢ.ትዮጵዊ ስነ-ምግባር ምንድን ነው? በምንስ ይገለጻል? የሚሉትን ጥያቄዎች “ ሰው፣ ግብረ - ገ ብና ስነ - ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች ” በሚለው በእንዳለ ገበየሁ ጥናትና በዶክተር ጠና ደዎ መጻፍ በመታገዝ በሚከተለው መልኩ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

“ኢ.ትዮጵያ በእናትነት የምትመሰል ሀገር ናት፡፡ ሁሉም የተፈጠረባትና የሚፈጠርባት፣ ያደገባትና የሚያድግባት፣ ተከባብሮ የሚኖርባት፣ የራሱን ችሎታና ማንነት በእውን የገለጸባትና የሚገልጽባት፣ የሚያረጋግጥባትና የሚያሳውቅባት ሀገር ናት፡፡” (ጠና፣2009፣317) የጠና ገለጻ

ብዙ ነገሮችን እንድናሰላስል እድል ይሰጣል፡፡ አንደኛ እናት “ርህራተ-ልቡና” ያላት በመሆኑ ልጆቿን ከሚወለዱበት ጀምሮ አድገው ለአካለ መጠን እስኪደርሱ ከደረሱም በኋላ የሰመረ ህይወትን ይኖሩ ዘንድ ከጎረቤት ጋር አብሮነትን፣ መቻቻልን፣ መረዳዳትን፣ ፍቅርን እያስተማረች በስነ-ምግባር አንጻ ታሳድጋቸዋለች፡፡ በዚህም እናት ለልጆቿ ያደረገችውን ሁሉ ልጆችም ለእናታቸው መልካም ነገሮችን የማድረግ ስነ-ምግባራዊ ግዴታን በልቦናቸው ቀርጸው ማድረግ በሚገባቸው ጊዜ ያደረጋሉ፡፡

“አመሳለ እም” የሆነችው ሀገራችንም ለዜጎቿ ስነ-ምግባራዊ ሀላፊነትን ከሚወስዱ ሀገሮች ጎራ የምትሰለፍ ናት፡፡ ዜጎቿን በግልጽ በተጻፉ ህጎችና ደንቦች ወይም በህሊና በተቀረጹ ወጎች፣ እሴቶች፣ ልማዶችና ስነ-ስርዓቶች ህይወታቸው የሰመረ፣ ኑሯቸው ያማረ እንዲሆን የስነምግባር እሴቶችን የድርጊታቸው ሁሉ መነሻ አድርገው እንዲጠቀሙ ስታስተምር ኑራለች፡፡ ለምሳሌ፡- ኢ.ትዮጵያዊ ቤተሰብ ለልጅ ስላላቸው ስነ-ምግባራዊ ግዴታን በተመለከተ ጠና የሚከተለውን ያስቀምጣሉ፡፡

ሁሌም ለልጅ ፍቅር ማሳየት፣ የልጆችን ፍላጎት ማወቅና ማክበር፣ የሌላውን ወገን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ማፍቀርና ማክበር፣ ልጆችን ከማናቸውም ጎጅ ነገሮች መከላከል፣ የሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ለልጆች መማሪዎች ናቸው በማለት ሁሌም መልካም ቦታዎች እንዲገኙ መርዳት፣ ልጆች በበጎ ምግባር እንዲታነጹ መምከር ወይም ማገዝ፣ ልጆች ትህትናን፣ ቅንነትን፣ ግልጽነትን፣ታማኝነትን እንዲማሩ መርዳት፣ ባንጻሩ መልካም ያልሆኑ ነገሮችን እንዲጠየፉ ማድረግ፣ ልጆች የሀገርና የወገን ፍቅርና አክብሮት እንዲያድርባቸው ማድረግ የሚሉት ኢ.ትዮጵያዊ ቤተሰባዊ የስነ-ምግባር ግዴታዎች እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፡፡ ጠና (2009፣268)

ከላይ የተጠቀሱትን መልካም ነገሮችን የማድረግ ተነሳሽነቱ የሚመነጭበትን መንገድም ከምንና በምን አይነት ሰው እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡

ግብረ-ገባዊ /ስነ-ምግባራዊ/ እውቀት ጥልቀት ካለው አስተሳሰብና ከአርቆ አስተዋይነት የሚመነጭ ነው፡፡ በቂና በሳል ግብረ-ገባዊ ዕውቀት የቀሰመ ሰው በስሜት፣ በስጋዊና ቁሳዊ ፍላጎት የሚነዳ ወይም የሚገፋ አይደለም፡፡ በሚግል ወይም በሚቀዘቅዝ ስሜት አይመራም፡፡ ይልቁንም የማመዛዘን ችሎታ ያለው በፈቃደኝነት ለበጎ ተግባሮች የመነሳሳት ፍላጎት ያዳበረና ራሱን በራሱ የማዘዝ አቅሙ ነጥሮ የወጣ ነው፡፡ ጠና (2009፣212) በኋላ በትንተና የምንመለከታቸው ገጸ ባህሪያት ግን በስሜት እየከነፉ እነሱነታቸውን የማይጥሉ እና የሚጥሉ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያዊ የስነ-ምግባር መገለጫን ከሙሉው በጣም በትንሹ ወስደን ስንመለከተው የሀገራችን ህዝብ በስራ፣ በአኗኗር፣ በእምነት፣ በአመለካካትና በመሳሰሉት ዙሪያ በፈጠራቸው የወንድማማችነት ወይም እህትማማችነት፣ የጓደኝነት ወይም የወዳጅነት፣ የጉርብትና ወይም የዝምድና ግንኙነቶች ውስጥ የመፈቃቀድ፣ የመረዳዳትና የመተባበር ባህል አለው፡፡ የሞተን በስርኣት ይቀብራል፡፡ የተረዳን(መርዶ) ሰው በአግባቡ ያስተዛዝናል፣ የታመመንና የታሰረን ይጠይቃል፣ አደጋ የደረሰበትን ይረዳል፣ ያጽናናል፣ ... ትንሹ ትልቁን በአግባቡ ያከብራል፡፡ ትልቁም ትንሹን ያፈቅራል፣ አንዱ ሌላውን ያምናል፣ በተራውም በእርሱ ይታመናል፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች ሲከሰቱ አብሮ ይቆማል፡፡ የሚሉትን የመልካም ስነ-ምግባር መገለጫዎችን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡

የኢትዮጵያህዝብ በተለየ ዓይን የሚያያቸው እና የሚተገብራቸው እንዲተገበሩም የሚፈልጋቸው ከሁሉም በላይ ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው የሙያ ስነ-ምግባራትም አሉት፡፡ ለምሳሌ፡- የህግና የፍትህ ሙያዊ ስነ-ምግባር፣ የንግድ ዓለም ሙያዊ ስነ-ምግባር፣ የመመህርነት ሙያዊ ስነምግባር የህክምና ሙያዊ ስነ-ምገባር እያልን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡ ሙያን በተመለከተ ጠና እንዲህ ያስረዳሉ፡፡

ማነኛውም ሙያ የራሱ ስነ-ምግባር አለው፡፡ ሙያ ሙያ በመሆኑ ብቻ የሚጠቅም ሊሆን አይችልም፡፡ ባለሙያዎች በሙያ እውቀትና ክህሎት የተካኑ መሆናቸው ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ሙያ ከእኩይ ነገሮች ባለሙያም ከእንከኖች ሊጠበቁና ሊጸዱ የሚችሉት በስነ-ምግባር ሲታነጹ ነው፡፡ ሙያ ለተፈለገው ጉዳይ የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት የሚችለው ውጫዊ በሆኑ ማህበራዊ ህግጋት በሚደረግበት ቀጥጥር ብቻ ሊሆን አይገባም፡፡ ከምንም በላይ በሙያተኛው ህሊና ወይም ውስጣዊ ስነ-ምግባር መዳኘት አለበት፡፡ ጠና (2009፣330 አጽንኦት ተጨመሯል)

እንደጠና ገለጻ ሙያ ድርብርብ ሃላፊነት ያለውና ለህሊና ተገዥ መሆን እንደሚገባ ያስገነዝበናል፡፡ ምክንያቱም በሙያተኛውና ሙያውን ፈልጎ በሚመጣው ተገልጋይ መካከል ያለው ግንኙነት የፈጣሪና የፍጡርን ያህል እምነት የሚጣልበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ጠና በተጨማሪም "የደንበኛን ፍላጎት መጠበቅና የሚቻለውን ሙያዊ አገልግሎት መስጠት የሙያተኛው ግዴታ ነው፡፡ ለራስ ጥቅም ሲባል፣ ሙያዊ አቅምንና የተሰጠ እምነትን በመጠቀም ደንበኛን የሚጎዳ ሙያተኛ ግን መጥፎ የሆነና ከሙያ አንጻርም ኢ-ስነ-ምግባራዊ

ድርጊት ነው” በማለት ይገልጻሉ፡፡ ጠና (2009፣333) ጠና ስለመምህርነት ሙያ እና ስለ አለው ፈታኝ ሁኔታም ከጉድለቱ በመጀመር ይገልጻሉ፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች መምህራን ብዙ ነገሮችን አሟልተው አይገኙም፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ከመምህራን የሚማሩት ከአንደበታቸው የሚወጣውን ሀሳብ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር ከሚፈጽሙት ድርጊቶቻቸውም ጭምር ነው፡፡ ከሀሳብና ተግባራቸው ብቻ ሳይሆን ከቁመናቸው፣ የሚቀስሙት ራሱ ብዙ እውቀት አለ፡፡ ቁመና ራሱ ብቻውን ስለ ሰው ብዙ ነገር ይናገራል፡፡ የመምህራን አነጋገርና አረማመድ፣ አለባበስና አኗኗር፣ የቋንቋ አጠቃቅምና የሀሳብ አጣጣል፣ ለሰው ያላቸው አክብሮትና ፍቅር፣ ለተማሪዎቻቸውና ለሙያቸው የሚሰጡት ፍቅርና ክብር፣ ለስራ ያላቸው እምነት፣ ለጊዜ አጠቃቅም የሚሰጡት ዋጋ ለተማሪዎች ትምህርት የሚቀስሙባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ጠና፣ (2009፣ 346)

የኢትዮጵያ ህዝብ በበጎ አይን የሚያያቸው እና የሚደግፋቸው ስነ-ምግባራዊ ድርጊቶች እናአስተሳሰቦች ያሉትን ያህል፣ በተቃራኒው የሚመለከታቸው እኩይ ተግባራት ወይም ግብረገባዊ ግድፈቶችም አሉት፡፡ ለምሳሌ የዳበረ የስራ ባህል አለመኖር፣ የጊዜ አጠቃቀም ስነ-ምግባራዊ ጉድለት፣ ልመና፣ የተንዛዙ አሰራሮችና ስነ-ስርዓቶች፣ ሙስና፣ መናናቅና መተማማት፣ገንዘብን ማምለክ፣ ሴሰኝነት /ዝሙት/፣ ፈላጭ ቆራጭነት፣ ልጆችን በመሳሪያነት መጠቀም፣ የቁጥጥር መላላት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ጠና (2009፣ 242፣ 250-251፣ 280-303) የተወሰደ፡፡ ለትንተና በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ የሚስተዋለው ግን ግብረ ገባዊ ግድፈቶች ሲሆኑ፣ ወዝ የለሽ የመምህራን ንግግር እና አቋመቢስ ሆኖ መገኘት እውቀትም ሆነ ምግባር ሊሸመትባቸው የማይችሉ “ከንቱወች” ሆነው የሚታዩ ናቸው፡፡

## 2.1.2 የስነ-ምግባር እሴቶች

ስነ-ምግባራዊ እሴት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን የሚያስማማ ትርጉም የለውም፡፡ ይህም ከሰው ሰው፣ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ፣ ከባህል ባህል የሚለያይ በመሆኑ ነው፡፡ በመጀመሪያ እሴት ምንድን ነው? የሚለውን መረዳቱ ተገቢነት አለው፡፡ benniga እንደሚለው “The term “value” may sujest that judgements of right and wrong, lofty and base, just and unjust and more personal preference, that things are useful as individuals happen to value theme.” (Benniga, 1991:131) እንደቤኔጋ ገለጻ እሴት ትክክለኛነትንና ስህተትነትን፣ ከፍተኛነትን እና ዝቅተኝነትን፣ ፍትሃዊነትን እና ኢ-ፍትሀዊነትን ከሁሉም በላይ ግን የግለሰብ ምርጫዎችን ፍርድ የምንሰጥበት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ እሴቶች የሚያስፈልጉን፣ የምንፈልጋቸው፣ የሚያስደስቱን፣ የምንወዳቸው በአጭሩ መልካም ነገሮችን የሚያጠቃልሉ ሀሳቦች ናቸው፡፡ (Bertens, 2000:139) የሰው ልጅ ማንነት ከሚሸመንባቸው አንዱ እሴቶች መሆናቸውን ጠናም ያስረዳሉ፡፡

ሰው የሚያስብ፣ የሚያውቅና የሚሰራ ብቻ ሳይሆን፣ የራሱን ድርጊትና ውጤት “ቆንጆ” ወይም “አስቀያሚ”፣ “ትክክል” ወይም “ስህተት”፣ “ሰናይ” ወይም “እኩይ”፣ “የሚበጅ” ወይም

“የማይበጅ”፣ “የሚጠቅም” ወይም “የሚጎዳ” በማለት እሴት የሚፈጥር እና የሚሰጥ ነው፡፡ ህይወቱን የሚመራው ስለ ፋክት ባለው እውቀት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እሴት ባለው ግንዛቤም ጭምር ነው፡፡ ማንነቱን በመቅረጽም ከእውቀት በላይ እሴት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ … ውስጣዊ ማንነቱን የሚያንጽውና ውጫዊ አካሉን የሚገነባው … የእሴት መገለጫ በሆኑ መርሆች ነው፡፡ ጠና (2009፣69)

የጠና ገለጻ የሚያስረዳን የሰው ልጅ ውስብስብ የሆነው ማንነቱን (የአስተሳሰብ፣ የድሪጊት፣ የሚወደው፣ የሚጠላው ነገር) ሁሉ በእሴት ላይ የተመረኮዘና እሴት በሰዎች ምርጫና ጸባይ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ “የነገሮች” መመረጥ አለመመረጥም ማህበረሰቡ በሰጣቸው ትልቅ ዋጋ/እሴት/ ልክ እንደሆነም ያመላክታል፡፡ ሌላም ልንረዳ እንችላለን የሰው ልጅ በብዙ ከሚቀርቡለት አማራጮች የእኔ የሚለውን ይመርጣል፡፡ አንዱን አንስቶ አንዱን ይጥላል፡፡ አንዱን ይዞ አንዱን ይለቃል፣ አንዱን በጥሩ አይን ሌላውን በተቃራኒው ይመለከታል፡፡ ይህን የሚመርጠው ወይም የሚወስነው በራሱ የእሴት ግንዛቤ አንጻር የተሻለ ሆኖ በማግኘቱ ነው፡፡

የስነ-ምግባር እሴቶች ስንል ከሌሎች እሴቶች የሚለዩበትን እና ግንኙነት የሚፈጥሩበትን የሚመለከት ነው፡፡ እሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር ሆኖ በተግባር የሚገልጠውን ድርጊት ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን የምንገመግምባቸው መርሆች ናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ከሌሎች እሴቶች (ከኢኮኖሚና ከውበት እሴት) ጋር ሲወዳደሩ በአራት መሰረታዊ ባህሪያት የተለዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

የመጀመሪያው የስነ-ምግባር እሴቶች ከኃላፊነት ጋር የሚወራረሱ መሆናቸው ሲሆን፣ ህዝብ ለሰራው ስራ ስህተት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ያስችሉታል፡፡ ምክንያቱም እሱ/እሷ/እነሱ ኃላፊነት የተሸከሙ ናቸውና፡፡ የስነ-ምግባር እሴቶች ኃላፊነት በሚሰማቸው ግለሰቦች የሚያዙ ከሆነ እሴቶቹ በሙሉ በተግባር ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ እሴቶች ከንፅህ ልቦና ጋር የሚገናኙ መሆናቸው ሲሆን፣ ሁሉም እሴቶች የስነ-ምግባር እሴቶችን በትክክል ተግባራዊ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም የስነ-ምግባር እሴቶች አሳማኝ ኃይል ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡ ያልተስተካከለ ሚዛን ነገሮችን በተክክል መለካት እንደማይችል ሁሉ፣ የስነ-ምግባር እሴቶችም ሌሎች እሴቶችን በትክክል ለመለካት መስተካከል አለባቸው የሚል ተጠየቃዊ አመክንዮም አለ፡፡

ለምሳሌ የውበትን እሴት አስመልክቶ አንዱ ስእል ማሳየት ቢፈልግ፣ አንዱ ደግሞ ሙዚቃ ማሰማት ቢፈልግ በሁለቱ ውጤት ላይ ሚዛናዊ አስተያይት ለመስጠት እና የስነ-ምግባር እሴቶችም ተገባራዊ እንዲደረጉ ከንጹህ ልቦና ይግባኝ ማለት ያስፈልጋል፡፡ የስነ-ምግባር እሴቶችን ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ የንጽህ ልቦና ሲሆን፣ የስነ-ምግባር እሴቶችን በእውነት ተግባረዊ ባደረግን ጊዜ ራሳችንን እንድናመሰግን፣ እሴቶችን በተቃወምን እና ተግባራዊ ሳናደርግ በቀረን ጊዜ ራሳችንን የምንወቅስበት ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሚለዩበት የስነምግበር እሴቶች የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ

ሀቀኝነት የተበደሩትን ነገር መመለስ እንደሚገባ ያስገድዳል፡፡ ምክንያቱም የስነ-ምግባር እሴቶች በውስጣቸው ህሊናዊ ትእዛዝ ያላቸው ስለሆኑ ነው፡፡

### *2.1.2.1. ማህበራዊ እሴት*

*መልካም የተሸለ ህይወት መኖርን መሰረት ያደረገዉ ጽንስ ሃሳብ የሰዉ ልጅ ለሚያደርጋቸዉ ነገሮች ሁሉ እሴትና ዋጋ መስጠቱ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ግብረ ገባዊ ድርጊቶች መፈጸም ያለባቸዉም የተሰጣቸዉን እሴት ከግብ ለማድረስ ነዉ፡፡ግብረ ገብም ሲመዘን ለሰዉ ልጅ ከሚኖረዉ እሴት አኳያ ነዉ፡፡የግብረ ገብ ህግጋት በራሳቸዉ ግብ ናቸዉና ልንፈጽማቸዉ እንገደዳለን፡፡*

*የሚለዩበት የስነ-ምግበር እሴቶች ብቻቸውን የሚቆሙ አለመሆናቸው ነው፡፡ ምንም እንኳ የስነ-ምግባር እሴቶች ከሁሉም በላይ መሰረታዊ ቢሆኑም፣ ያለሌሎች እሴቶች የበላይ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የስነ-ምግባር እሴቶችን ከሌሎች መለየትም አይቻልም፡፡ ለምሳሌ አንድ ነጋዴ የኢኮኖሚን እሴት ተግባራዊ በሚያደርግበት ጊዜ የስነ-ምግባር እሴትንም በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡* (Bertens, 2000:143-147)

#### **2.1.2.1.1 ግብረገባዊነት**

*የስነ ምግባርና የግብረገብ ባህሪ የማይነጣጠሉና በተቃራኒ ጽንፉ ያሉ ሃሳቦችን በጋራ ይዞ መቅረቡና እኩል የመልካምነትና የእኩይነት መለያ መስጠቱ ነዉ፡፡ቀጥሎ በሚቀርቡት ጽንስ ሃሳቦች ዉስጥም የሚከተለዉ ይህ ነዉ፡፡* (ጠና 2008፤69-100) *ግብረ ገብን ለማጥናት የሚረዱ ጽንስ ሃሳቦች ትንታኔዎች፣ለዚህ ጥናት በጽንስ ሃሳብነት ለጥናቱ ትንታኔ ስለሚያገለግሉ ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርበዋል፡፡*

*ሰዎች በግብረ ገብ የጋራ ስምምነት ዉስጥ ማድረግ የሚገባና የማይገባ ብለዉ ባስቀመጧቸዉ መርሆች መሰረት ለድርጊታቸዉ ተገቢነትና ኢ ተገቢነት ዋጋ የሚሰጥበትና የሚመዘንበት ጽንስ ሃሳብ ነዉ፡፡የቆመለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መልካም ወይም እኩይ መንገድን ሊጠቀም ይችላል፡፡ሰናይና እኩይ ነዉ ብሎ ከለየ በኋላ መልካሙን መንገድ የሚጠቀመዉ ይህ ዘዴ ነዉ፡፡ሰናይ ድርጊቶች ሲባሉ ሁሉም ተመሳሳይ ዋጋ የላቸዉም፡፡ስለዚህ ለሰናይ ድርጊቶችም የተሸለ ደረጃን ያበጃል፣ይህም ‹‹ከፍተኛ ሰናይ›› ይባላል የመጨረሻዉ መልካም ድርጊት፡፡የሰዉን ሰባዓዊነት የሚያጎድፍ፣ ክብርን የማያስጠብቅና ጥቅም አልባ ድርጊት ሁሉ እኩይ ነዉ፡፡እኩይ ለመባሉም፡-የተፈጥሮ አኩይና ግብረ ገባዊ እኩይ ይባላሉ፡፡ግብረ ገባዊ እኩይ የሚባለዉ አንድ ሰዉ ሆን ብሎ አቅዶና አልሞ ማህበረሰቡ የማይፈቅደዉን ኢ-ግብረ ገባዊ ድርጊት ሲፈጽምና ሰዉን ሲጎዳ ነዉ፡፡*

### 2.1.2.1.2 የሰዉ ባህሪና ጸባይ

መልካምና እኩይ ድርጊትና ምግባር ተብለዉ እንደተገለጹት ሁሉ የሰዉ ልጅ ባህሪዉና ጠባዩ ለግብረ ገባዊነት ማሳያ ናቸዉ፡፡ከዉስጣዊ ማንነቱ ዋነኞቹ የሆኑት ባህሪና ጠባይ በጊዜና ሁኔታዎች ለዉጥ ሊለወጡ የሚችሉ ናቸዉ፡፡የሰዉ ልጅ ባህሪዉን የሚያገኘዉ ከአካባቢዉ እንደመሆኑ መጠን ግብረ ገባዊ ጉዳዮችን ስንመረምርም ለዉን ግብረ ገብ ብቻ ተቀብሎ የሚኖር ሳይሆን ወደ ተሻለና የላቀ ወደሚባል የግብረ ገብ ደረጃ የሚደርስበት ጽንስ ሃሳብ ላይ መድረስ አለበት፡፡

### 2.1.2.1.2.1. ኅሊና

ኅሊና የሚለዉን ሃሳብ ከነ ጓዙ ጠቅሎ ወክሎ የሚቀርብ ሲሆን የሰዉ ልጅ ግብረ ገባዊ ተግባራትን እንዲፈጽም የዘህ ተቃራኒ ካደረገ ደግሞ እንዲጸጸትና እንዲስተካከል የሚመራዉ የግብረ ገብ ማዕከል ነዉ፡፡ለእያንዳንዱ ድርገት ትክክልና ስህተት ተገቢና የማይገባ ብሎ መመሪያ የምናበጅበት ቅጥ የሚያበጀዉ ህሊና ነዉ፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለዉም ከአካባቢያዊ ግንዛቤና ከዉስጣዊ ስሜት በሚጠራቀም እዉቀት አማካኝነት ነዉ፡፡የሚለዩበት የስነምግበር እሴቶች የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ሀቀኝነት የተበደሩትን ነገር መመለስ እንደሚገባ ያስገድዳል፡፡ ምክንያቱም የስነ-ምግባር እሴቶች በውስጣቸው ህሊናዊ ትእዛዝ ያላቸው ስለሆኑ ነው፡፡እንደዚህ አይነቱ ክስተትም ለስነ-ምግባር መርህ አለመታዘዝ (ethical dissonance) ይባላል፡፡ ይህም ለአዕምሯዊ እውቀት (ህሊና አለመታዘዝ) ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡ ለአእምሮ አለመታዘዝ ማለት ህሊና አድርግ የሚለንን ችላ ብለን አእምሮአችንን አታለን ከስነምግባር ውጭ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት ራሰችንን የምንሸውድበት ስልት ነው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሲያታልሉ፣ ሀቀኝነት የጎደለውን ባህሪያቸውን እና ተግባራቸውን ሀቅ እንደሆነ አድርገው መተርጎም ይጀምራሉ፡፡ (Shahar and Francesica, 2012፡3)

### 2.1.2.1.2.2. ለዉሸት መገዛት

Cheating, fraud, racketeering, and other forms of dishonesty are among the greatest personal and societal challenges of our time. (Shahar and Francesica, 2012:1)

ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ክህደትና ሌሎች የሐቀኝነት መገለጫ ቅርጾች የዘመናችን ትልቅ የግለሰባዊና ማህበራዊ ችግር ከሆኑት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ለዉሸት መገዛት በብዙ መልክ  የሚገለጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው ሲሆን፣ ጽንሰ ሃሳቡ ከማታለል፣ ከመካድ፣ ከማጭበርበር በአጠቃላይ እነዚህ ሁሉ ተጠቃለው በሚገለጹበት ራስን በማታለል የራስ ጽንሰ ሀሳብ እና ተግባር የሚገለጽ ነው፡፡ የሰው ልጅ ስለራሱ ጥሩ ነገር እንዲሰማው እና እንዲሰማለት ይፈልጋል፡፡ የራሱን መልካም ገጽታ ለመጠበቅም ጥረት ያደርጋል፡፡ ምንአልባትም ራሱን በስነ-ምግባር የታነጸ ዜጋ አድርጎ መመልከትንም እንዲሁ፡፡ ይሁን

እንጂ ይህ አይነቱ ፍላጎት ራስን ከማታለል ጋር ተጣምሮ ይታያል፡፡ ሰዎች በምንም መንገድ ይሁን ያገኙትን ስኬት የራሳቸው አድረገው ይቀበላሉ፡፡ ስኬት ያገኙበትን የስህተት መንገድ ግን አይቀበሉም፡፡ (Miller & Ross, 1975)

ሀቀኝነትን በተለምዶ ከፍ አድረገው የሚመለከቱት በርካቶች ናቸው፡፡ በራሳቸው ስነ-ምግባርም በጽኑ ያምኑበታል፤ የራስን የስነ-ምግባር ምስል(ገጽታን) ለመጠበቅም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ብዞዎቹም ታማኝና ስነ-ምግባራዊ ነን ብለው ያምናሉ፡፡ ይሁን እንጂ የራሳቸውን አወንታዊ የስነ-ምግባር ምስልን ለመጠበቅ ያላቸውን ፍላጎትና ሀቀኛ ያለመሆን ባህሪን በወል የሚመረምሩ ባለመሆናቸው በመካከላቸው ትልቅ ክፍተት ይስተዋላል፡፡

እንደዚህ አይነቱ ክስተትም ለስነ-ምግባር መርህ አለመታዘዝ (ethical dissonance) ይባላል፡፡ ይህም ለአዕምሯዊ እውቀት (ህሊና አለመታዘዝ) ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡ ለአእምሮ አለመታዘዝ ማለት ህሊና አድርግ የሚለንን ችላ ብለን አእምሮአችንን አታለን ከስነምግባር ውጭ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት ራሳችንን የምንሸውድበት ስልት ነው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሲያታልሉ፣ ሀቀኝነት የጎደለውን ባህሪያቸውን እና ተግባራቸውን ሀቅ እንደሆነ አድርገው መተርጎም ይጀምራሉ፡፡ (Shahar and Francesica, 2012፡3)

የሰው ልጅ በራስ ወዳድነት ባህሪው የተነሳ ግለሰባዊ ትርፍን ለማግኘት ከሀቅ የራቀ ድሪጊትን ይፈጽማል፡፡ ይህ ድርጊቱም የውስጥ ፍላጎትን ለማሳካት ከመሻት የሚመጣ ነው፡፡ ያልተገባ ትርፍን ለማግኘት፣ በማታለል፣ በማጭበርበር፣ በመካድ፣ በመዋሸት፣ በመስረቅ፣ በመዝረፍ እና እነዚህን ሁሉ በሚጠቀልለው ራስን የማታለል ስራ በመስራት ከሀቅ ከፍታ ሲወርድ ይታያል፡፡ ስርቆ፣ ማጭበርበር እና ዝርፊያ ሀቅን የሚያጎድፉ ሰዎች ያልተገታ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ዋና ግባት አድርገው የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ናቸው፡፡ የሀቀኝነት መጉደል መበራከትና ተዘውትሮ እንዲተገበር መደረግ፣ ለሰዎች አነሳሽ ኃይል ሆነው የሚያገለግሉ በርካታ ምክንያቶች መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህም፡-

አንደኛ ግለሰቦች (ቡድኖች) ከሐቀኝነታቸው ወርደው ተገቢ ያልሆነ ስራ ሲሰሩ የሚያገኙት ጥቅም ከፍተኛ የሚሆን ከሆነ፣

ሁለተኛ ሀቀኝነታቸውን በመሳት ከማህበረሰብ ደንብ (ህግ) የማምለጥ ወይም የመያዝ እድላቸው አናሳ ሆኖ ሲገኝ፣

ሶስተኛ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ከሀቅ ከፍታ ወርደው ፣ ማህበራዊ ህገ-ደንብን ወይም የመተዳደሪያ እሴት ግንቦችን አፍርሰው ቢገኙ እንኳ፣ በህግ የሚደርስባቸው መቀጮ (ማህበራዊ ቅጣት) ቀላል ሆኖ ሲያገኙት ሀቀኝነትን የማጉደል ተግባር ይፈጽማሉ፡፡ (Mazar, 2008:633)

### 2.1.2.1.2.3 *ክብረ ቢስነት*

*ማንኛውም ሰው ለሰራተኛዋ ሲወለድ የራሱን ክብርና መብት ተጎናጽፎ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ምክንያታዊነቱ እና በህሊና መታደሉ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የተለየ ክብር እንዲሰጠው አድርጎታል፡፡ በምክንያታዊ እና በህሊና የተገነባ መሆኑ ደግሞ ስነ-ምግባራዊ/ግብረ-ገባዊ/ እየተባለ እንዲጠራ አስችሎታል፡፡* "every person endwed with reasons and conscience is a name of moral status." (lenner, 2004:70) *የሰው ልጅ ክብር የተለየ እና የእሴቶች ከፍተኛ መለኪያ/ልኬት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን፣ ምክንያታዊ ያልሆኑ ነገሮች የሚታደሉት አይደለም፡፡*

Kaufmann *እንደሚለው* the theoretical discussion about human dignity usually starts with abstract values such as the sanctity of life or with human capacities such as autonomy, rationality or moral agency (Kaufmann, 2011:1)

*እንደ ካውፍማን ገለጻ ሰባዊ ክብር የላቀ የስነ-ምግባር መገኛ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜም የሰው ክብር ከህይወት ቅድስና፣ ራሱን በራሱ ከማስተዳደር፣ ምክንያታዊ እና የስነ-ምግባር እንደራሴ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚገለጽ ነው፡፡*

*ሰባዊ ክብር ውርደትን፣ በተበላሸ ስነ-ምግባር መለካትን፣ ስቃይን፣ ድህነትን፣ ጦርነትን እና ባርነትን የሚያሳስብ ሀቲት እንደሆነ እና ክብር ባለበት ሁልጊዜም የሰባዊ ክብር መጣሻ መንገዶች ከጎን አይጠፉም የሚለው ሌላው የካውፍማን እሳቤ ነው፡፡*

## 2.2 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

*በዚህ ንውስ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ እና የመተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች ጋር ቅርበት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች በመለየት በጥናቱ ተዳሰውበታል፡፡ ከጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቅርበት ያላቸው አራት ጥናታዊ ጽሑፎችን ለማየት ሙከራ ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ የታዩት ጥናታዊ ጽሑፎች ሲሆኑ፣ ቀዳሚ ያረኩት የእንዳለ ገበየሁ ስነ ምግባራዊ ዝቅጠት በ ኢያሪኮ 777፣ ኢያሪኮ 888፣እና ኤፍ ልቦለዶች ዉስጥ በ2012 ዓ.ም በ ባህር ዳርዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የስነ ምግባር ዝቅጠትን መመርመር ላይ ዓላማዉ ያደረገ ሲሆን፣ በቴክስቶች ላይም የስነ ምግባር ንድፍ ሃሳቦችን መሪ በማድረግ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም፣ዲኦንቶሎጅካል፣ቴሎጅካል እና ቨርቹ ኤቴክስን የንደፈ ሃሳብ ማዕቀፍ አድርጎ እንደ አስፈላጊነታቸዉ በመጠቀም የሞራል ፍልስፍናን በመጠቀም፣ቴክስትን በንድፈ ሃሳብ በመመርመር የመረጃ ማሳያ/ማቅረቢያ መንገድ ተንታኝ ዘዴን ለመፈክር፣ ለማብራራትና ለመተንተኛነት ተጠቅሞበታል፡፡*

*በትንታኔዉም የስነ ምግባር ዝቅጠትን በመመርመር መገለጫዎችን ማሳየት እንደ ዝሙት፣ ሀቀኝነትን ማጉደል፣ክብርን ማዋረድ፣ሙስና እና የሰባዓዊ ክብር መዉረድን በጉልህ እንዲስተዋሉ እና እንዲሁም ለስሜት በሚገዙና ለባዕደወ አምልኮ ይሁንታን በሰጡ የተለያዩ*

ማህበራዊ ደረጃዎች ከፍታ ባላቸዉ ገጸ ባህሪያት በመግለጽ የስነ ምግባር እሴት መሰረት ናቸዉ እየተባሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ግምት የተሰጣቸዉ የእምነት ተቋማት ሆኑ በዉስጡ ግልጋሎት የሚሰጡ አገልጋዬች ከመንበረ ክብራቸዉ በራሳቸዉ ሲሰርጉ፣ተከዮቻቸዉ እናዚህ ትልቅ ግምት የሰጧቸዉን የእምነት ተቋማትና አገልጋዮች በስነ ምግባር አምነዉ ሲቀበሉ ማየት የሚቸገሩበትን ሁኔታ በቴክስቱ ላይ ተመስርቶ ትንታኔ አድርጓል፡፡

በግኝቱም በቴክስቶች ውስጥ ያሉ ባለታሪኮች መካካድ፣ መናናቅ፣ቃል ኪዳንን አለመጠበቅ፣ ለመልካም ድርጊት መጥፎ ምላሽ መስጠት፣ ውሸት፣ ማስመሰል፣ የበላይነትን ለማስፈን የሚጥሩ፣ ራስ ወዳድነት፣ በሌሎች ላብ ራስን ማክበር፣ ፍቅረ ንዋይ የመሳሰሉ ጉዳይዎች እንደተስተዋሉ እና  የስነ ምግባር ዝቅጠት መገለጫዎች ጎልተዉ እንዲወጡ አድርጓል፡፡

የእንዳለ ጥናት ግብረገብን የሚያነሳ እና መተንተኛ ንድፈ ሀሳቡም የሞራል ፍልስፍና መሆኑ፣ ግብረ ግብ እሳቤዎችን ማንሳቱ፣እኩይ የገጸ ባህሪያት ድርጊትን መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፣ ይዘነው በተነሳነው ዓላማ እና ግብ አንገናኝም፡፡ እንዳለ የስነ-ምግባር ዝቅጠትን በመመርመር መገለጫዎቹን ማሳየት ላይ ሲሆን የእኔ ጥናት የስነ ምግባር ዝቅጠትም ይሁን ከፍታ፣መልከምነትም ይሁን እኩይነት አንዱ ላይ ብቻ ተመስርቶ ሳይሆን አጠቃላይ በቴክስቱ የቀረቡ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡

በአጭር ልቦለድ ዉስጥ ቴክስቱ ይዞት በተነሰዉ የስነ ምግባር ጉዳይ ላይ በመመስረት፣ ገጸ ባህሪያቶች ይዘዉት በሚነሱት ሃሳብና ድረጊት አመካኝነት፣ የሚከናወኑ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን ነቅሶ በማዉጣት፣ መልካምም  ይሁን እኩይ  ጉዳዮችን ስነ ምግባራዊ ሂስን መርህ በማድረግ  ትንታኔ ማድርግ ነዉ፡፡  ከዚህም ሌላ የቴክስት ምርጫችን ይለየናል፡፡

በሁለተኛነት የሰላማዊት በየነ "የተፈጥሮና የባህል ግጭትና እርቅ በአዳም እረታ ህማማትና በገና ውስጥ" 2010 ዓ.ም  በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የተፈጥሮንና የባህልን ግጭት ማሳየት ዓላመው ያደረገ ሲሆን፣ በቴክስቶቹ ላይ የአንድምታ ዲኮንስትራክሽናዊ ንባብን በማናበበያ ዘዴነት በመጠቀም የደመ ነፍስንና እና የግብረ-ገብን ጉዳይ ተንትና አቅርባለች፡፡ ትንተናው የሳር ልጆች፣ እራት፣ ስንዝሮ፣ የሐር ነዶ፣ ህማማትና በገና ፣ የምስራች ልጅ እንደናቷ ሆነች እና መንገዶች ሁሉ ወደ ዘሴ ይወስዳሉ በሚሉ ሰባት ቴክስቶች ላይ ተመስርታ ትንታኔ አድርጋለች፡፡

በትንታኔዋም ደመነፍሳዊነትን ሰዎች ከእንስሳት ጋር የሚመሳሰሉበት ባህሪ እንደሆነ፣ ይህም እንስሳት ሲርባቸው ብቻ ምግባቸውን ፈልገው ማግኘት እንደሚችሉ፣ጠላትም ሲመጣባቸው በደመ ነፍስ መከላከል እንደሚችሉ፣መራባት የሚችሉትም እንዲሁ አስበው ፣አቅደው ፣መቼና የት እንዴት የሚሉ ተጠየቃዊ ምክንያቶችን መሰረት አድረገው ሳይሆን፣በዘፈቀደ እንደሆነ በመረጃ የታገዘ ማብራሪያ ሰጥታለች፡፡ የግብረገብ ፍልስፍን በመጠቀም፡፡ ጥልቅ የሆነ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በግኝቷም በቴክስቶች ውስጥ ያሉ ባለታሪኮች መካካድ፣ መናናቅ፣ቃል ኪዳንን አለመጠበቅ፣ ለመልካም ድርጊት መጥፎ ምላሽ መስጠት፣ ውሸት፣ ማስመሰል፣

የበላይነትን ለማስፈን የሚጥሩ፣ ራስ ወዳድነት፣ በሌሎች ላብ ራስን ማክበር፣ የመሳሰሉ ጉዳይዎች እንደተስተዋሉ እና የባህልና የተፈጥሮ ግጭት ጎልተው እንደወጡ ገልጻለች፡፡

ደመነፍሳዊ ባህሪ በገጸ ባህሪያት ላይ ጉልህ ሆኖ የቀረበበት እና ከአእምሯቸው በላይ የሆኑ ባለታሪኮች እንዳሉ፣ ይኸ ደግሞ እንስሳዊ ባህሪ የተላበሱ መሆናቸው እንደሆነ አመላክታለች፡፡ በህማማት እና በገና ውስጥ ለሞትና ለሕይወት ክበር የሚሰጡ ባለ ታሪኮች እንዳሉ ተመላክቷል፡፡

የሰላመዊት ጥናት ግብረገብን የሚያነሳ እና መተንተኛ ንድፈ ሀሳቡም የሞራል ፍልስፍና መሆኑ፣ ግብረ ግብ እሳቤዎችን ማንሳቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፣ ይዘነው በተነሳነው ዓላማ እና ግብ አንገናኝም፡፡ ሰላማዊት የሰው ተፈጥሮና ባህል አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠርና የበላይ ለመሆን የሚያደርጉትን ትግልና ትግሉ የሚያስከትለውን ቀውስ በመፈተሽ የመመልከቻ መንገዶችን ማውጣት ሲሆን የእኔ ጥናት ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች በአጭር ልቦለድ ዉስጥ ቴክስቱ ይዞት በተነሳዉ ሀሳብ አማካኝነት እንዴት ቀረቡ ነዉ፡፡ ከዚህም ሌላ የቴክስት ምርጫችን ይለየናል፡፡

በሶስተኛነት የተመለከቱኩት የስነ ህይወት ገዛኸኝ "ባይተዋርነት በሰባተኛው መላክ ትኩሳትና ሌቱም አይነጋልኝ ውስጥ" በሚል ርእስ በ2007 ዓ.ም በሚል ርእስ ለአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ያቀረበችው ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ የተወከሉ ሰባዊ ጉዳዮችን በሐቲት መተንተኛነት መተንተንና በመተርጎም ማሳየት የሚል ዋና አላማ ይዟል፡፡ የባህል ጥናት የጥናቱ ማስሂጃነት ሆኖ ተመርጧል፤ ንድፈ ሀሳቡም ከተለያዩ ምሁራን እይታ አንጻር ተቃኝቷል፡፡ የነገረ-ህላዌ ጭብጦች ፍርቅነት፣ ስነ-ምግባራዊ ሞት፣ የሰባዊነት መንጠፍ እና ባይተዋርነት ራሳቸውን ችለው ተብራርተዋል፡፡

የባይተዋር መከሰቻዎችንም ለስልጣን ባይተዋር መሆን፣ ወለፈንዲነት፣ ማህበራዊ ባይተዋርነት፣ ለህግና ድንብ ባይታዋር መሆን እና ለራስ እንግዳ መሆን የሚሉ ንዑሳን ጉዳዮችም ተብራርተዋል፡፡ በዚህም ሦስቱ ልቦለዶች የባይተዋር መከሳቻ እንደሆኑ አረጋግጣለች፡፡ በትንተናዋ ልቦለዶችን ከሰባዊነት መንጠፍ፣ ከባይተዋርነት አንጻር፣ በስሩ ከሚገኙ የስልጣን ባይተዋር መሆን፣ ወለፈን ዲነት፣ ከማህበራዊ ባይተዋርነት፣ ለገዛ እራስ እንግዳ መሆን እና የሦስቱንም የመባያ ጉዳዮች በተብራራና ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ ከልቦለዶቹ ታሪክ እየተቀነጨበ በአንድምታ ተተንትኗል፡፡

በትንታኔው ውጤትም የነገረ ህላዊ ጭብጦች በሦስቱም ልቦለዶች እንደተንጸባረቁ በመግለጽ ለእያንድ አንዱ የነገረ ህላዌ ጭብጦች መገለጫ አስቀምጣለች፡፡ ስነ-ምግባራዊ ሞት ለስነ-ምግባር ህግጋት ተገዥ አለመሆን፣ ለማህበረሰቡ ስርዓት ምላሽ አለመስጠት፣ነባሩን የስነ-ጽሑፍ ይተባ ባህል መጣስ፣የአንድ ማህበረሳባዊ ስነ-ምግባራዊ ሞት እና የህግና ደንብ ጥሰት መከሰቻ ሆነው እንደቀረቡ አስቀምጣለች፡፡ በሐይማኖት ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳን ማህበረሰቡ

ከአጎናጸፋቸው የተከበረ ስፍራ ወርደው ነውር ለሚባል እሳቤ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው የቀረቡበት እንደሆነ እና ትልቅ ቦታ የነበሩት ከነውር ወለል ላይ ተነጥፈው የሚታዩበት ሁሉ ለስነ-ምግባር ሞት መገለጫ ሆነው ቀርበዋል፡፡

የሰባዊነት መንጠፍ የሚለውን ደግሞ በአብዛኛው በወንዶች የሚስተዋል ሲሆን፣ ራሳቸው አንሰው ሲያሳንሱ ወረደው ሲያዋርዱ፣ ምንም አይነት የሐፍረት ስሜት በማይሰማቸው ገጽባህረያት ተወክሎ እንደቀረበ ትገልጻለች፡፡ የሴቶች ተስፋ መቁረጥ፣ ሴቶቹ በሌላ ማህበረሰብ /ራሳቸውን ይጨመራል/ ከሰውነት ክብራቸው ሲያንሱ ሙሉ ሰውነትን ሳይሆን ከወንዶች የሚያንስ ሰብዕና ያላቸው መሆኑን አምነው በሚቀበሉ ገጸባህሪያትም ተስተማስሎ ቀርቧል፡፡ እንዚህ ገጸባህሪያት ከሰውነት ክብር መውረዳቸው ከተፈጠሮ የታደሉት አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው፡፡

ባይተዋርነት የሚለውን የነገረ ህላዌ ጭብጦችም ገጸባህሪያት ጉዳያቸውን አቤት የሚሉበት ህግ አለመኖር፣ባለመኖሩም በየአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲያጣጥሉ እሴቶቹን ሲያረክሱ በሚስተ ዋሉና ህይወት ትርጉም ባልሰጠቻቸው፣ለማህበረሰቡ ህግና ደንብ ባለመታዘዝ ለምሳሌ የቤተ እምነትን ስርዓት መጣስ በሚያሳዩ ገጸ ባህሪያት ተወክለው መቅረባቸውን ገልጻለች፡፡ ግለሰቦች በሚፈጠሩባቸው ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ጫናዎች ሰው ራሱን በሚያገል መልኩ የሚያሳዩትን ለባይተዋር መገለጫ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም የመባያ ጉዳዮች በሚል በሶስቱም ልቦለዶች በተደጋጋሚ መከስተ ነገር ሆነው የመጡትን ቀይ ቀለም፣መጠጥ ሴተኛ አዳሪነት፣ወሲብ፣ ዘመናዊ ትምህርት እና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚሉትን በመዘርዝር እያንዳንዳቸው የተወከሉበትን ትርጓሜ አስቀምጣለች፡፡

የጥናቱ ማጠቃለያ አጭርና ጨመቅ ያሉ ሀሳቦች የጥናቱን አጠቃላይ የግኝት ውጤት ይዞ ተቋጭቷል፡፡ የጥናት ወረቀቱን ሲመለከቱት ከመነሻው ጀምሮ የሀሳብ ፍሰቱና የቃላት አደራደሩ ጥሩ የሚባል ይመስለኛል፡፡ ለሁሉም ማብራሪያ ለሚያሻቸው አቢይም ሆነ ንዑሳን ጽንሰ ሀሳቦች በቂ ማብራሪያ በመስጠት ግልጽነትን የፈጠረ መሆኑ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡ የስነ-ህይወት ገዛኸኝ ጥናት ስነ-ምግባራዊ ብከታ የሚል ጽንሰ ሀሳብ እንደ አንድ ንዑስ ርዕስ በማንሳቷ ከእኔ የጥናት ርዕስ ጋር የስነ ምግባር እኩይ ባህሪያትን በመንሳት ረገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይመሳሰላል፡፡ ባይተዋርነት እና የሰባዊነት መንጠፍ የሚሉ የነገረ-ህላዌ ጭብጦች መከሰቻ ስነ-ምግባርዊ ሂስ ይዞት ከሚነሳዉ ሀሳብ ጋር የመወራረስ ባህሪ ያላቸው በመሆ የስነ-ኽይወት ገዛኸኝ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነገር ቢኖረውም፣ በመሰረታዊ ይዘትነት እና ልናሳይ በምንፈልገው ጭብጠ ሀሳብ እንለያለን፡፡ በንደፈ ሀሳብም እንዲሁ፡ ስነ ኽይዎት የባህል ጥናትን የተጠቀመች ሲሆን የእኔ ጥናት የስነ-ምገባር ንድፈ ሀሳብን የሚጠቀም በመሆኑ እንለያያለን፡፡ የቴክስት ምርጫችንም ሌላው መለያችን ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ የወንድ ወሰን ሽመልስ “የሰባዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦቻቸው በየሕሊና ባርነት ልቦለድ ውስጥ” በሚል የቀረበ ሲሆን፣ ይህ ጥናት በልቦለዱ ውስጥ የሳባዊነት መንጠፍ የቀረበበትን መንገድ መመርመር፣ ዓላማው ያደረገ እና የመተንተኛ

ዘዴውም የግብረገብ ፍልስፍናን ተከትሎ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በጥናት ትንተና ሂደትም፣ ልቦለዱ እንደ ክፋትና ደግነት፣ ፍርሃትና ጀግንነት፣ እውቀትና ድንቁርና፣ በቀለኛነትና ይቅር ባይነት፣ ራስ ወዳድነትና እኛ ባይነት፣ ክብርና ውርደት፣ ረሃብና ጥጋብ የተስተዋለበት እንደሆነ ተገልጾል፡፡ የወንድ ወሰን ጥናት በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሞራል ወይም ስነ-ምግባር ንድፈ ሀሳብን መጠቀሙና የሰባዊነት መንጠፍ ስነ-ምግባራዊ ሂስ ከሚዳስሳቸዉ ጉዳዮች ጋር የተቀራራበ ዝምድና ያላቸው በመሆኑ፣ በቴክስት ላይ መመስረቱ የሚያመሳስለው ቢሆንም ይዘነው በተነሳነው የጥናተችን ጥያቄዎች፣ ዓላማዎችና  በማተኩሪያ ነጥባችን እንለያለን፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ጥናቶች ዉስጥ የስነ-ምግባር ጉዳዮችን በዋና ርዕስነት በስነ-ጽሑፍ ውስጥ ማየት መቻሉ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖርም የስነ-ምግባር ጉዳዮችን ማሳየት በምንችልባቸው መሰረታዊ ነጥቦች፣ በቴክስት ምርጫችን እና ቴክስቱን ለማየት በምንጠቀማቸው ንድፈ ሀሳቦች፣አጠቃላይ የስነ ምግባራዊ ጉዳዬችን በመዳሰስና ከስነ ምግባር ጉዳዬች የተወሰኑት ነጥሎ በማየት፣ እንዲሁም በቴክስቱ ውስጥ ያሉት ባለ ታሪኮች በሚወክሉት የዘመን መንፈስ የተራራቁ በመሆኑ እንለያያለን፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3 የጥናቱ ዘዴ

በጥናቱ የተካሄደዉ አጭር ልቦለድ  ስነ ምግባራዊ  ጉዳይ ላይ ስነ ጹሑፋዊ ሂስ መስጠት እንደመሆኑ መጠን ጥናቱ ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴን መሰረት አድርጎ የተሰራ ሲሆን የጥልቅ ንባብ የትንታኔ አጠናን ስልትን የተከተለ ነዉ፡፡  ጥናቱ  ቴክስትና በንድፈ ሀሳብ መተንተን ስለሆነ የመረጃ ማሳያ/መቅረቢያ መንገዶች ተንታኛ ዘዴ ነዉ፡፡ የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ዉለዋል፡፡ካዓላይ የመረጃ ምንጭች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉ መጽሐፎች፣ ቀድመዉ በዕርሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ እነዚህ ከዓላይ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ለጥነቱ ከፍተኛ ጠቀሚታ አበርክተዋል፡፡ በተለይም የጥናቱን መነሻ ሃሳብ ለማጠናከርና ልቦለዱን በማንበብ የሚገኘዉን መረጃ ለመተንተን ማመሳከሪያና መመዘኛ በመሆን አገልግለዋል፡፡

እንዲሁም ለዚህ ምርምር የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፍ በመሆን ግልጋሎት ላይ የሚዉሉት ሦስት ሲሆኑ፣ ዲኦንቶሎጂካል፣ ቴሊኦሎጂካል እና ቨርቹ ኤቲክስ ናቸው፡፡ የዲኦንቶሎጂካልን ንድፈ ሀሳብ የስነ-ምግባርን መነሻ እሴት ከመጠበቅ አለመጠበቅ ጋር ወይም የተቀመጡ ደንቦችን ከማክበር አለማክበር ጋር የሚመጣውን የስነ-ምግባር ዉድቀት ለመለካት ያስችላል፡፡ የቴሊኦሎጂካል ንድፈ ሃሳብ፣ ገጸ ባህሪያት መነሻ ድርጊታቸው ምንም ይሁን ምን የመጨረሻ ውጤታቸውን በማየት ለመወሰን እና መልካም ስራን ሆነው በመገኘት የሚሰሩ ገጸ ባህሪያትን ለመመልከት ደግሞ ቨርቹ ኤቲክስ እንደ አስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 3.1 የናሙና አመራርጥ

በአንድ በተጻፉ ሰነዶች ዙሪያ ትንትና ለመስራት የቃላት፣ የሐረጋት፣ የዓ.ነገሮች እና አንቀጾች በተገቢው መልኩ ወስዶ መመርመር እንደሚቻልም (Berg 2011, 245) ያስረዳል፡፡ በዚህም ጥናቱ "ቴክስት" መተንተን ስለሆነ ዓላማ ተኮር የቴክስት አመራረጥ ዘዴን እንዲከተል ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በልቦለዶቹ ውስጥ የመልካምም ይሁን የእኩይ ሀሳብና ተግባር ገላጭ ሆነው የተወከሉ ገጸባህሪያትን እና ሀሳብ የተስተላለፈባቸውን የቃላት፣ የሀረጋት የዓ.ነገርን እና አንቀጾችን አውድ በመለየት ለትንተና አዘጋጅቷል፡፡

ጥናቱ የስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን በልቦለዶች ላይ የመፈተሽ ዓላማ ያለው ስለሆነ፣ የስነ-ምግባር ጉዳዮችን በሰፊው የቀረበባቸው ናቸው ተብለው የታሰቡትን መረጃዎች ኢላማዊ የቴክስት አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ለመምረጥ ተችሏል፡፡ "ቴክስትን" ለመመርመርም የBergን ሀሳብ  መሰረት በማድረግ ቃላትን፣ ሀረጋትን ዓ.ነገርን፣ አንቀጾችን፣ ምዕራፎችን፣ መጻህፍትን ደራሲዎችን እና ርዕዮተ ዓለሞችን  በመውሰድ ለትንተና አዘጋጅቷል፡፡

ጥናቱ በዋናነት ይዞት የተነሳዉ ስነ ምግባዊ ሂስ በተመረጡ አጭር ልቦለድ ላይ ማካሄድ እንደ መሆኑ መጠን ለዚህም አመች ነዉ ተብለዉ ለጥናቱ የተመረጡት ለትንተና አዘጋጅቷል፡፡

## 3.1.1 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት ግብ መሳካት ይረዳሉ ተብሎ የተመረጡት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፣ሰነድ ፍተሻ ነዉ፡፡ ይህ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎች ለመሰብሰብና በጥናቱ መመለስ የሚገባቸዉን የምርምር ጥያቆዎች ለመመለስ ዋነኛ መሳሪያ ነዉ፡፡

በጥናቱም በተመረጡ አጭር ልቦለድ ዉስጥ የቀረበዉን ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች ከገጸ ባህሪት አቀራርጽ እስከ ተግባራቸዉ ድረስ ያለዉን ስነ ምግባራዊ ጉዳዩች ለመተንተን ልቦለዱን ደጋግሞ ማንበብ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ጥልቅ የሆነ የንባብ ስልት በመጠቀም አስፈላጊዉን መረጃ ተሰብስቦበታል፡፡መረጃዉ ለህዝብ በሚደደርስ መልኩ የታተመ ልቦለድ እንደመሆኑ መጠን በህዝብ ሰነድ አይነት ስር ሊካተት ይችላል፡፡

## 3.1.2 የአተናትን ስልት

ይህ ጥናት በቴክስት ላይ የተወሰነ አይነታዊ ጥናት እንደመሆኑ ለትንተና የተመረጡ “ቴክስቶችን” ምንባባዊ የትንተና ዘዴን በመከተል የጥናቱን ዓላማ ከግብ በሚያደርስና የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መመለስ በሚያስችል መልኩ ለትንተና ተለይተው የተቀመጡ፣ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀት በመመርመርና የተመረጡትን የስነ-ምግባር ንድፈ ሀሳቦች መሪ በማድረግ እና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ትንተና ተደርጓል፡

# ምዕራፍ አራት

## 4 የመረጃ ትንተና

በአልፎ ያላለፈ የተመረጡ አጭር ልቦለድ ወስጥ የተለያዩ ስነ ምግባራዊ ጉደዳዮችን በወሰጡ ያካተተ ሲሆን ስነ ምግባራዊ ጉዳዬችን ደራሲዉ እንዴት ባለ መንገድ በአጭር ልቦለድ ድርሰቱ ዉስጥ አካተታቸዉ፣ በተለያዩ ገጸባህሪያት አማካኝነት እኩይ ሰናይ ባህሪያት የቀረቡበትን መንገድ፣ በቴክስቱ ዉስጥ ማህበረዋና ስነ ምግባራዊ ጉዳዬች ያቀረበበት ሁኔታ፣ በመዳሰስ ከስነ ምግባራዊ ጉዳዮች ጋር ግንኙት ያላቸዉን ይዘቶች ከተለያዩ ሰነዶችና ነድፈ ሃሳቦችን ጋር በማቀናጀት የጥናቱን ዓላማ በጠበቀ መልኩ ትንተና ተደርጓል፡፡

መረጃዎችንም ለመተንተን ስነ ምግባራዊ ሂስን በመሰረታዊነት በመጠቀም ከሞራል ፍልስፍና ጋር በማቀናጀት፣ ከንድፈ ሃሳቦች ጋር በማዋሃድ የተጠቀምኩ ሲሆን በተለይም ለዚህ ጥናት ለመረጃ መተንተኛነት ለመጠቀም አስችሎኛል፡፡ ምክንያቱም ስራዎችን ከስነ-ምግባራዊ ሂስ አንጻር ለመተንተን የተመረጡበት መንገድ፣ ስነ ምግባራዊ ጉዳዬችን ለመዳሰስ ሲሆን የሥነ ምግባራዊ ሂስ ይዞት የቀረበዉ የስነ ምግባር ጉዳዮች፣ መሰረት በማድረግ የተመረጡትን ቴክስቶች በመዳሰስ፣ እንዲሁም ከስነ ጹሑፉ ትርጉምና ከስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን ጋር  በማገናዘብ ይዘታቸዉን በጠበቀ መልኩ በልቦለዶች ዉስጥ ያለዉን ታሪክ በማየት ከስነ መግባራዊ ይዘት አንፃር ለመተንተን በማስቻሉ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

## 4.1 የልቦለዱ ጭምቅ ታሪክ በአልፎ ያላለፈ አጭር ልቦለድ

ሶስት የአዲስ አበባ የአዲስ ከተማ ትምህት ቤት የመሰናዶ ተማሪዎች ነበሩ አይናበባ ሔራንና ሰሎሞን ይባላሉ፡፡ሰሎሞን የኖሮ ዉጣ ዉረድ የበዛበትና ኑሮን ለማሸነፍና ትምህርቱንና አይነ ስዉር እናቱን ለመጦር ከትምህርቱ ጎን ለጎን የቀን ስራ እየሰራ ግማሹ ሰዓቱን ለትምህር ቀሪዉን ህይወቱ እነድትቀጥል የቀን ስራ እየሰራ በትምህርቱ ጎበዝና ታተሪ ከትምህረቱ በሰተጀርባም አረብ ሀገር ኑሮን ለማሸነፍ ብላ ወጥታ የቀረችዉን የእህቱን ሀዘን በመቻልና አይነ ስዉር እናቱንም በማስናናት ኑሮዉን እንደሚገፋ የምታዉቀዉ አንዳንድ ጊዜ የቀን ስራ ሰርቶ ለምሳ ከክፍል ሰወጣ አብራዉ እየሄደች ትታዘብ የነበረችዉ ሄራን የሰሎሞንን የኑሮ ሁኔታ ከማወቅም በላይ አቅሞ በቻለዉ ልክ ሰሎሞንና አይነ ስዉር ደካማ እናቱን በተለያ መንገድ ታግዛዉ ነበር፡፡የሶሎሞንና የሄራን መቀራረብ ችግሩን ከመረዳት የመነጨ እንጅ ከዚያ የዘለለ አልነበረም አይነ ስዉር እናቱም ቢሆን የሰሎሞንን ጎዳኛ ሄራንን አረብ ሀገር ለስራ ወጥታ በቀረችዉ ልጅ ምትክ ፈጠሪ የሰጣት መሆኑን በመቀበል እያመሰገነች ትኖር ነበር፡፡ሰሎሞንን በዓይን ሄራንን በቅርበት የምታዉቃት የመሰናዶ ትምህርት ቤት ጎደኛ ነበረችዉ ያይን አበባ በተክለ ቁመናዎና በዉበቷ አማላይ ስንት ጎረምሳዎች በፍቅር ለማጥመድ የሚፈልጎት ሲሆን ብዙዎችንም አመራርጣ ያየችና የወነወዶችን ባህሪ ጠንቅቃ ያወቀች በመሆኖ የሶሎሞን አይነፋርነት የሄርን ሰሎሞንን የመቅረብ ሚስጥር ያሳሰበት ነበር፡፡  ሶስቱም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ተፈትነዉ ዉጤት ተሳክተላቸዉ ሄራን ባህር ዳር ሶሎሞንና አይናበባ አዚያዉ አዲስ አበባ ሲደርሳቸዉ ሄራን

ከሶሎሞን ጎን መራቅ ባትፈልግም ወደ ተመደበችበት ቦታ ለመሄድ ትገደዳለች ለመሄድ ስትወስንም የሰሎሞን እናት እና ሶሎሞንን ለመሰናበት ወደ እናቱ ቤት ታመራለች እናቱን ተሰናብታ ለሰሎሞንም ቤት አለመኖሩን ስታረጋግት ነገሮች እስከሚመቻቹት ስልክ ልደዉል እንደማችል በመግለጽ ደብዳቤ ለእናቱ እንድታደርስ ሰጥታ ስትሰናበት የሶሎሞን እናት እንደዚያ ቀን ሁነዉ አልቅሰዉና አመረዉ ወደ ሰማይ እያንጋጡ ኦ ፈጣሪ ሆይ ምን አልኩህ ወጣ በቀረችዉ በልጀ ምትክ ልጅ ሰጥተሁኝ መልሰህ ለምን ነሳህኝ በማለት እያመረሩ ያለቀሱበት ቀን ሲሆን ሄራንም ከሰሎሞን ለመለየቷ የሞት ያህል ቢከብዳትም ከቤተሰብ ትዕዛዝና ከለፉችለት አላማ መዉጣት ስለሌለባት እያመረርችም ቢሆን ለመሄድ በመወሰኖ ያሰሎሞን እህት እንዳሁኑ አድራሻዋ ሳይጠፋ የላከችለትን ኮምፒትር እንድትመልስለት ለጎደኛዋ በመንገር ወደ ባህር ዳር ዩኒበቨርሲቲ ትሄዳለች በዚህም አጋጣሚ ድሮዉንም የሠሎሞን ዓይናፋርነትን የሁለቱን የጠበቀ ግንኙነት ስትከታተል የነበረችዉ ሄራን ጎደኛ በኮፒተሩ ስም ሰለሞንን ለመግኘት ተጣደፈች አጋጣሚዉ የተመቻቸላት ጎደኛዋ ሰሎሞንን ከአንዷም ሁለቴም በማግኘት ያላስፈላጊ የፍቅር ወጥመድ ዉስጥ ትከተዋልች መጨረሻ ላይም በሰሎሞን መልካም ምግባርነት ሳይሆን በራሶ ፍጥነትና በእናቱ እንዲሁም የሰሎሞንን እናት ለመጠየቅ በሄደችበት ወቅት ጎረቤቶች ባደረጉት የቡና ጥሪ ላይ የሁለቱን ግንኙነት እንደ ፍቅረኛሞች አድርገዉ እንደ ጥንቂልና በሚመስል መልኩ አወቅንላችሁ የሚለዉን ሲመረምሩ ስላየች ሰሎሞንን ከነ መልካም ብህሪዉ አንተም ከዚህ ቤተሰብ ነዉ የተገኘህ በማለት ከዚያ በሆላ ዓይኑን ለማይት አልፈለገችም በተቃራኔዉ ሶሎሞን እሷ ባስጀመረችዉ በማያዉቀዉ የፍቅር ግንኙነት ተጠምዶ ሲካትን ዩኒበቨርሲቲ ዉስጥ ለመማር እስከሚከብደዉ እሷን ለማግኘት ያልፈነቀለዉ ደንጋይ የለም በመጨረሻም እናቱ የልጀዬ ሚስት ናት በማለት የሰጣቻትን የወርቅ ሀብል በጥሳ ለሰሎሞን ትወረዉርለታል እሱም ትምህርት በማቋረጥ ወደ እናቱ ይሄዳል እናቱም ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ እሱም እናቱ እንደሞቱ በደብዳቤ ገለጸላት ይሄዳል፡፡መጨረሻ ላይ በድርጊቷ በመጸጸት ሰሎሞንን ለማግኛት ወደና ሰሎሞን ቤት ትሄዳለች በሩ ላይ ስትደርስ አሁን እንዲት ሁኘ ልግባ ብሶቱን እጨምርበት ይሁን እያለች የተለያዩ ሃሳቦች እየመጡባት እያመነታች ከቆየች በሆላ ሳታገኘዉ ትመለሳለች፡፡

## 4.1.1 ስነ ምግባር በተማሪዎችና በመምህራን መካከል

አንድአስተማሪ ለስምንት አመታት ቾክ አቡንኖ ያገኛትን ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር በቡክሽ ላርልሽ ብሎኝነ በር፡፡ከጋበዝከኝ ይበቃል ብዬ አሳዝነኖኝ ተዉኩ፡፡ ቀሪዎቹ የማይጋብዙኝ ነገር አልነበረም አለምን ሊገዙልኝ የሚሞክሩ ሁሉ ነበሩ፡፡አስተማሪዎች ከነጬ ጋዉን በላይ ደርበዉ የለበሱት ከብር ጥለዉ ምራቃቸዉ እየተዥረበረበ ሊሰለቅጡኝ ሲሯሯጡ ለአንዳንዶች እያወኩኝ ተበልቾላቸዋለሁ፡፡ሌሎቹ ከከንፈሬ ሳያልፉ የእድሜ ልክ የትዝታቸዉ ፋና ሁኘ ተለይቻቸዋለሁ፡፡ (ሱለይ አደም፣ገጽ፣54)

ከላይ በልቦለዱ አጽመ ታሪክ መሰረትም በተላም በለንበት ዘመን የስነ ምግባር መጎደሎች ከለንበት ዘመን ጋር በማስተሳሰር በአንዳንድ መምህራንና በተማሪዎች መካከል ሚታየዉን

የስነ ምግበር ጉድለትና አቀራረብ በለንበት ዘመን እነደዚህ አይትና መምህርና ተማሪ ከቀለም ልጅነት ከቀለም አባትነት የዘለለዉን የስነ ምግባር ጉድለት ደራሲዉ በምናቡ በሳላቸዉ አስተማሪዎችና ተማሪዎች አማካኝነት የዘመኑን የአንዳንድ መምህራንና ተማሪዎችን ስነ ምግባር ከጋሃዱ ዓለም ንጽብራቆች ጋር በማንጸባረቅ ገልጸበትል፡፡ድርጊት ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ጠና (2009፣333) ጠና ስለመምህርነት ሙያ እና ስለ አለው ፈታኝ ሁኔታም ከጉድለቱ በመጀመር ይገልጻሉ፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች መምህራን ብዙ ነገሮችን አሚልተው አይገኙም፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ከመምህራን የሚማሩት ከአንደበታቸው የሚወጣውን ሀሳብ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር ከሚፈጽሙት ድርጊቶቻቸውም ጭምር ነው፡፡ ከሀሳብና ተግባራቸው ብቻ ሳይሆን ከቁመናቸው፣ የሚቀስሙት ራሱ ብዙ እውቀት አለ፡፡ ቁመና ራሱ ብቻውን ስለ ሰው ብዙ ነገር ይናገራል፡፡ የመምህራን አነጋገርና አረማመድ፣ አለባበስና አኗኗር፣ የቋንቋ አጠቃቅምና የሀሳብ አጣጣል፣ ለሰው ያላቸው አክብሮትና ፍቅር፣ ለተማሪዎቻቸውና ለሙያቸው የሚሰጡት ፍቅርና ክብር፣ ለስራ ያላቸው እምነት፣ ለጊዜ አጠቃቅም የሚሰጡት ዋጋ ለተማሪዎች ትምህርት የሚቀስሙባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ጠና፣ (2009፣ 346)

የኢትዮጵያ ህዝብ በበጎ አይን የሚያያቸው እና የሚደግፋቸው ስነ-ምግባራዊ ድርጊቶች እና አስተሳሰቦች ያሉትን ያህል፣ በተቃራኒው የሚመለከታቸው እኩይ ተግባራት ወይም ግብረገባዊ ግድፈቶችም አሉት፡፡ ለምሳሌ የዳበረ የስራ ባህል አለመኖር፣ የጊዜ አጠቃቀም ስነ-ምግባራዊ ጉድለት፣ ልመና፣ የተንዛዙ አሰራሮችና ስነ-ስርዓቶች፣ ሙስና፣ መናናቅና መተማማት፣ገንዘብን ማምለክ፣ ሴሰኝነት /ዝሙት/፣ ፈላጭ ቆራጭነት፣ ልጆችን በመሳሪያነት መጠቀም፣ የቁጥጥር መላላት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ጠና (2009፣ 242፣ 250-251፣ 280-303) የተወሰደ፡፡ በዚህ ታሪክ ዉስጥም የሚስተዋለው ሴሰኝነት (ዝሙት) ግብረ ገባዊ ግድፈቶች ሲሆኑ፣ በእንደዚህ አይነት ምግባር ዉስጥ የሚሳተፉ ከሙያዉ ምግባር ጋር የሚጣረስ እና ኢ-ሰባዊ ድርጊት የሚፈጽሙ መምህራንን አቋመቢስ ሆኖ መገኘትና እውቀትም ሆነ ምግባር ሊሸመትባቸው የማይችሉ "ከንቱወች" ሆነው የሚታዩ ናቸው፡፡

### 4.1.1.1 መልካም ስነ ምግባር በዘመኑና በአጭር ልቦለዱ ገጸ ባህሪያት የቀረበበት

‹‹… ልጅ ሁኘ ነዉ ወደ እዚህ የመጣነዉ!"አለኝ፡፡ወደ ቤተሰብ ወሬ የሄድን ስለመሰለኝ መንገዱን ቀየርኩበት፡፡"ኦ ባህረዳር ዉብ ነች ይባላል!"ካልኩ በኋላ "ኮምፒተሩን ያዋሰህ ሰዉ መልካም ነዉ ብክህ እንዲህ አይነት ሰዉ በዚህ ዘመን ይገኛል? ከተገኘ አስተዋዉቀኝ አልኩት"…››(ሱለይ አደም፣ገጽ፣61-62)

መልካምና እኩይ ድርጊትና ምግባር ተብለዉ እንደተገለጹት ሁሉ የሰዉ ልጅ ባህሪዉና ጠባዩ ለግብረ ገባዊነት ማሳያ ናቸዉ፡፡ከዉስጣዊ ማንነቱ ዋነኞቹ የሆኑት ባህሪና ጠባይ በጊዜና ሁኔታዎች ለዉጥ ሊለወጡ የሚችሉ ናቸዉ፡፡የሰዉ ልጅ ባህሪዉን የሚያገኘዉ ከአካባቢዉ እንደመሆኑ መጠን ግብረ ገባዊ ጉዳዮችን ስንመረምርም ያለዉን ግብረ ገብ ብቻ

ተቀብሎ የሚኖር ሳይሆን ወደ ተሻለና የላቀ ወደሚባል የግብረ ገብ ደረጃ የሚደርስበት ጽንስ ሃሳብ ላይ መድረስ አለበት፡፡

በዚህም ደራሲዉ መልካም ስነ ምግባርን ከልቦለዱ አብይ ገጸ ባህሪያት ጋር በማስተሳሰር በተለይም በዓለንበት ዘመን ምቀኝነት ክፋትና አለመተማመንን በማስወገድ በመልካምነትና ምሌዎችም የታነጹ በመሆን ታማኝነታቸዉን የሚያንተጸባርቁ ከእኩይ ስነ ምግባር የወጣ አመለካክትን በዚህ አጭር ልቦለድ ዉስጥ በተመጠነ መልኩ ያንጸባረቀበትን መንገድ ያሳየናል፡፡ገጸ ባህሪያት የጋሃዱ ዓለም፣ ሰዎች ንጸብራቆች እንደመሆናቸዉ መጠን በልቦለዱ ዉስጥም የተለያዩ ስነ ምግባር ጉዳዮችን ሲያንጸባርቁ ይትያሉ፡፡ በዘመናችንም እኩያም ይሁን መልካም ምግባር የሚስተዎሉና የሚንጸባረቁ መሆናቸዉን በገጸ ባህሪት ተግባር አማካኝነት ያሳየናል፡፡

### 4.1.1.2 የዘመኑ የጥንዶች ግንኙነት በአብይ ገጸ ባህሪት ከነ-ምግባር አንጻር የቀረበበት

‹‹…ስንጫወተወ ከቆየን በኋላ ሌላ ጊዜ በሰፊዉ ምሳ እየበላን እንደምንጫወት ነግሪዉ ተለያየን፡፡ስናለያይ በፊት እንደሌሎች ወንዶች ልሸኝሽ ይላል ብዬ ስጠብቅ ወይ ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ ከእኔ በተቃራኔዉ መንገድ ዞሮ ሄደ፡፡…ሌሎች ወንዶች ሁሉ አነሱብኝ፡፡ወንድ ማለት ከሁሉ ነገር ቆጠብ ሲል ነዉ!" ብዬ ፊስ ቡኬ ላይ ለጠፍኩ፡፡ ወዲያዉ መዓት ወነወድና ሴት የመረቡ ጓደኞቼ ይከራከሩበት ጀመር፡፡እንደ ፈለጋችሁ ያመንኩበትንና የሆነዉን ለጥፊያሁ፡፡… የፈለገዉ ቢሆን እጄን አላወጣም!"ብዬ ድርቅ አልኩና ተደገፍኩት፡፡ተደነባብሮ የሚያወራዉ መዓት ርዕስ ነበር፡፡መደነባበሩ -የዚች ዓለም ክፋት ያልነካካዉ መሆኑን ስለነገረኝ ወደድኩት፡፡ (ሱለይ አደም፣ገጽ፣63-64)፡፡

በዚህ አጽመ ታሪክ ዉስጥ የሶሎሞን የመልካም ወንዶች ስነ መግባር መገለጫ ባህሪ በማድረግና፣ ከሌሎች ያለ መረጋጋትና የቤተሰብንም ሆነ የማህበረሰቡን መልካም ባህሪ ከተላበሱ ወንዶች ያልተላበሱ ወንዶች፣ በዘመናችን ምን ይህል እነደበረከቱ፣ በዘመኑ ስነ ጹሁፍ አማካኝነት በሁለቱ ገጸ ባህሪያት በማስተሳሰር ደራሲዉ ለተደራሲያን ልብን በሚነካና ህሊናን በሚዳስስ መልኩ ያቀረበበት፣ ዘመኑን የዋጀ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች የተዳሰሱበት መንገድ፣ የዘመኑን በተለይም በከነፍኩልሽና አበድኩልሽ የሚከናወኑ የፍቅርና የትዳር ግንኙነቶች ከእንደዚህ አይነት እኩይ ባህሪያት የሚመነጨና፣ በዘመኑ ለትዳር ፍች ዋና መሰረት በደንብ ሳይተዋወቁ መጋባት፣ የሰዎን ልጅ ሰዉነት ሳይሆን ንዋያት እንደሚገዙትና በንዋያት የተገዛ የዘመኑ ፍቅር መነሻዉና መድረሻ የለያዬ እንደሆነ ደራሲዉ በአብይ ገጸ ባህሪያት አማካኝነት ያንጸባረቀበት መንገድ ነዉ፡፡

### 4.1.1.3 ከቤተሰብ ቁጥጥር መዉጣትና በዘመኑ በተማሪዎች የሚንጸባረቁ እኩይ ስነ ምግባር

‹‹…ቤተሰቦቼ ተቋም ገባች ብለዉ የበፊት ባህሪዬን በሙሉ ሰርዘዉ ሌላ ሰዉ እንደሆንኩ በማሰብ አክብረዉኛል፡፡አምነዉብኛል፡፡በዚህ አጋጣሚ ብዙ ሰዉ ባገኝም ለሰሎሞን ግን ደዉየለት አላዉቅም ብዙ ካወጣዉና ካወረድኩ በኋላ ደወልኩለት››፡፡(ሱለይ አደም፣ገጽ፣64)፡፡ ጎሌና የሚለዉን ሃሳብ ከነ ጓዙ ጠቅሎ ወክሎ የሚቀርብ ሲሆን የሰዉ ልጅ ግብረ ገባዊ

ተግባራትን እንዲፈጽም የዘህ ተቃራኒ ካደረገ ደግሞ እንዲጸጸትና እንዲስተካከል የሚመራዉ የግብረ ገብ ማዕከል ነዉ፡፡ለእያንዳንዱ ድርገት ትክክልና ስህተት ተገቢና የማይገባ ብሎ መመሪያ የምናበጅበት ቅጥ የሚያበጀዉ ህሌና ነዉ፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለዉም ከአካባቢያዊ ግንዛቤና ከዉስጣዊ ስሜት በሚጠራቀም እዉቀት አማካኝነት ነዉ፡፡የሚለዩበት የስነምግበር እሴቶች የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ሀቀኝነት የተበደሩትን ነገር መመለስ እንደሚገባ ያስገድዳል፡፡ ምክንያቱም የስነ-ምግባር እሴቶች በውስጣቸው ህሊናዊ ትእዛዝ ያላቸው ስለሆኑ ነው፡፡እንደዚህ አይነቱ ክስተትም ለስነ-ምግባር መርህ አለመታዘዝ (ethical dissonance) ይባላል፡፡ ይህም ለአዕምሯዊ እውቀት (ህሊና አለመታዘዝ) ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡ ለአእምሮ አለመታዘዝ ማለት ህሊና አድርግ የሚለንን ችላ ብለን አእምሮአችንን አታለን ከስነምግባር ውጭ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት ራሰችንን የምንሸውድበት ስልት ነው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሲያታልሉ፣ ሀቀኝነት የጎደለውን ባህሪያቸውን እና ተግባራቸውን ሀቅ እንደሆነ አድርገው መተርጎም ይጀምራሉ፡፡ (Shahar and Francesica, 2012፡3) ህሊና ግን ወቀሳዉን ይቀጥላል፡፡ በዚህ አጭር ታሪክም ደራሲዉ ያቀረባት ገጸ ባህሪ ቤተሰብ ተቋም ገብታ ባህሪዋን እንዳስተካከለች አምነዉ ቢያከብሯትም እንኳን እራሶን የምትታዘብበትና አእምሮዋን የሚወቅሳትን ነገር ወደ ኋላ በመመለስ መለካም የነበረዉን ሰዉ ማስታወስ ትጀምራለች፡፡በሀሳብም አዉጣ አዉርዳ አመዛዝና ትወስናለች፡፡ ይህም የሚሆነዉ የስነ ምግባር እሴቶች ከዉስጣዊ ስሜት እንደሚገባ ኅሊና ያስገድዳል፡፡ ለአእምሮ አለመታዘዝ ማለት ህሊና አድርግ የሚለንን ችላ ብለን አእምሮአችንን አታለን ከስነምግባር ውጭ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት ራሰችንን የምንሸውድበት ስልት ቢሆንም መጨረሻ ላይ ከኅሊና ተገዥነት እንደማንወጣ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ ታሪክ ዉስጥ የአብይ ገጸ ባህሪያት የሰሎሞንና ያይን አበባ እኩይና ሰነይ ስነ ምግባርን እንዲሁም በዘመናችን የሚታዩ ማንም አያየኝም በማለትና ለህሊና ባለመገዛት ከቤተሰብ ሃላፊነት ቁጥጥረና ጥበቃ ዉጭ ነኝ የሚሉ ጋሀዱን አለም ተማሪዎች ንጽብራቅ እንዲሁም ቤተሰብ ልጆቻቸዉ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከገቡ በኋላ በራሳቸዉ ሃላፍነት ይመራሉ፡፡ በማለት ከቋጥጥር ዉጭ የሚሆኑበትና የመጡበትን ዓላማ ወደ ጎን በመተዉ የዋልጌ አይነት ስነ ምግባራቸዉን የሚያንጸባርቁበትን መንገድ በአብይ ገጸ ባህሪያት የተገለጸ ሲሆን ድርሰቱን ለነበቡት ሁሉ ወላጆች ለልጆቻቸዉ የሚያደርጉትን ቁጥጥርና ምክር እስከ መጨረሻም ቢሆን እንደሚያስፈልጋቸዉ የተገለጸበት መንገድ ነዉ፡፡

### 4.1.1.4 የሃይማኖት ፍልስፋና ከስነ ምግባራዊ ሂስ አንጻር

እንደ (Quarcoopome, 1987፡154) ገለጻ በተለምዱዊ ሀይማኖት (traditional religion) አተያይ ስነ-ምግባር የሀይማኖት ፍሬ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ Aghaም ሀይማኖትና ስነ-ምግባር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው በመግለጽ የQuarcoopome ሀሳብ ይደግፋል፡፡ (Agha, 2003:43)

የስነ-ምግባር ፍልስፍናን ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚገልጹ በርካታ ምሁራን ናቸው፡፡ ሃይማኖት ከሌለ ስነ-ምግባር የሚባል ነገር እንደማይኖርም ያስረዳሉ፡፡ ስነ-ምግባር

እስካሁን የሃይማኖት የአንጎል ክፍል ወይም ከአስፈላጊ የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ ነጥሎ ማየት እንደማይቻልም ያስረዳሉ፡፡ በዚህም ሃይማኖተኛ የሆነ ሰው በተመሳሳይ ስነ-ምግባራዊ (መልካም ባህሪ ያለው) ነው በማለት እውነታነቱን ያጸድቃሉ፡፡ የስነ-ምግባር ህይወት ምን አልባት ከሃይማኖት ውጭ ሊታሰብ አይችልም ወደሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርሱ የፍልስፍና ሰዎችም አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአለም ላይ ቤተ-እምነቶች የሚበዙ ከሆነ አለም የተዋበች ቦታ ትሆናለች የሚል እምነት ያላቸው ናቸው፡፡

በግሪክ ፈላስፎች እይታ ቡዲሂዝም፣ ክርስትናና ሌሎች ሀይማኖቶች ከስነ-ምግባር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሊነጣጠሉ የማይችሉ እና አንድ ማእከል ናቸው፡፡

ሃይማኖት በእምነት ላይ የተመሰረተ ገናና እሳቤ ነዉ፡፡የቅዱሳን መጽሐፍትን ህጎች ማክበር ለሃይማኖት ቀዳሚና ዋነኛ ግብር ነዉ፡፡በዚህ መሰረት ትኩረት ከሚሰጣቸዉና የሰዉ ልጅ በአካባቢዉና በማህበረሰቡ ከሚፈራቸዉ ከሚያከብርቸዉ መካከል ስነ-ምግባር አንዱ ነዉ፡፡መለያ ህግና ስርዓት በመደንገግ መልካምና ክፉ ወይም ሰናይና እኩይ በማት ይገለገልባቸዋል፡፡ለስነ ምግባር ህግና ደንብ መኖር የሃይማኖት መኖር አንዱና ዋነኛዉ መሆኑ የበርካታ ፈላስፎች የፍልስፍና ሀሁ ነዉ፡፡

ለሃይማኖት መኖር የሚነሱ የፍልስፋና ሃሳቦች በርካታ ቢሆኑም የአካባቢዉንና የማህበረሰቡን አመለካከት፣ የሃይማኖት ተከታዮች የሚተዳደሩበት የስነ ምግባር ደንቦች፣ኑሯቸዉ የሚመሩበት የህይወት ፍልስፍና ዓለም የሚታይበትን መነጸር መሰረት በማድረግ የተለያዩ የሃይማኖት ፍልስፍናዎች በአልፎ ያላለፈ ሌሎች አጫጭር ልቦለዱች ላይ ተዳሰዋል፡፡

"አዎ እሷ በህይወቴ መኖሯ የእድለኝነቴ መገለጫ ነዉ፡፡የፈጣሪን መኖር የማየዉ በሷ ዓይኖች በኩል ነዉ፡፡ከአጽናፍ አጽናፍ ብርሃን አፍላቂ ነን ብለዉ የሚመጻደቁት ፅሐይና ጨረቃ ስራ ቢያቆሙ የሕላዌዬ ደባብ ለቅጽበት ፈቀቅ የማይለዉ በህይቴ ዉስጥ እሷ ስላለች ነዉ››(ሱለይ አደም፣ገጽ፣67)፡፡

…በክርስትና እምነት አስተምሮ እናት አባትህን አክብር ከሚለዉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ጋር በማገናዘብ ደራሲዉ እናት አባትን ማክበር አንድ የህይወት መርህ መሆኑን ከልቦለዱ አጽመ ታሪክ ጋር በማገናዘብ በዘመኑ ያለዉ ትዉልድ እናት አባቱን እንዲሁም በእድሜ የሚበልጡትን እንዲያከብር መልካም ስነ ምግባር እንዲላበሱ ለተደራሲያን በዓብይ ገጸ ባህሪያቱ በሰሎሞን እናቱን የሚያከብርበትና የሚወድበትን መንገድ ከእነ አገላልጹ በምናባዊ ገጸ ባህሪያት የዘመኑን ትዉልድ መከባበር የገለጸበትን መንገድ ያንጸባርቃል፡፡ በዚህም ታሪክ ዉስጥ ሀይማኖትን መሥነ-ምግባር ዉስጥ ያሳየናል፡፡

### **4.1.1.5** ከባህልና ከማህበረሰቡ አፈንግጠዉ የሚታዩ እኩይ ስነ ምግባሮች

‹‹ ለቡና መጥተዉ የነበሩ እናቶች ሁሉ አሉ ሰለሞንን ላቅፈዉ እየፈለኩ እነሱ ማህል የተገኘ በመሆኑ ነዉ መሰለኝ እሱንም ፈራሁት፡፡…በቃ ከዚያ ጊዜ በኋላ ሰለሞንን በእኔ ፍላጎት ዳግም አላገኘዉትም ስልኩን ጥቁር ዝርዝር ዉስጥ ካስገባዋቸዉ የወንድ ስልኮች መሀል

አስገባዉት የአይናፋሩ ሰለሞን ኑሮ ይናከሳል፡፡በክላሳችን ምክንያት የተለየሁት ወንድ መሆኑን አለመሆኑን ግን ለራሴ የምመልሰዉ ጥያቄ ሆኖ እራሴን አሳመመኝ››፡፡(ሱለይ አደም፣ገጽ፣75-76)፡፡

ሰዉን በራሱ ማንነት ሳይሆን በቤተሰቦቹና በጎረቤቶቹ ሚዛን መዝኖ ማየት ምልካም ያለመሆኑንና በተለይም የዘመናችን መለኪያ የሆነዉ ሰዉን በሰዉነቱ ከመቀበል ባለዉ ንብረትነ ማንነት የሚያገኘዉ ተቀባይነት እያደገ መምጣቱንና እኩይ ምግባር መሆኑን ደራሲዉ ለአንባቢያን ያስገነዘበበት መንገድ ነዉ፡፡4.6 በአልፎ ያላለፉና ሌሎች

## 4.1.1.6 በአልፎ ያላለፈ ልቦለዶች ዉሰጥ ማህበራዊና ስነ ምግባራዊ ጉዳዬች

ዘመናዊነት ሁለት ተቃርኖዎች አሉት፡፡በአንድ በኩል የሰዉ ልጅ ነጻነትና አብሮነት ጋር ከሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገት ጋር እንዲሁም ከኢኮኖሚ ብልጽግና ጋር ይየያዛል፡፡በሌላ ገጽ ግን ዘመናዊነት ዉስጥ የዘር ጭፍጨፋና ኢ-ሰባዊ የሆኑ ጭካኔዎች አሰቃቂ የዓለም ጦርነቶችና የህይወት ትርጉም የለሽነት ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡(Elkins 1959)::ጠቅሶ (ወንድዬ ካሳ፣50)፡፡የምትሃታዊ እዉነታዊነት ባህሪያት በኤጭ ልቦለድ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ይገልጻል፡፡

ማህበራዊ ሂስ እ.ኤ.አ በ1920ዎች እና በ1930ዎቹ በጀርመን ፍራንክኮንፈርት የፍልስፋና ትምህርት ቤት የተነሳ አዲስ የፍልስፋና ንቅናቄ ሲሆን ይህም ንቅናቄ በዘመናዊነት ዉስጥ ያጋጠሙንን ማህበራዊ ችግሮች መንስኤዎችን ነቅሶ የሚያወጣና ከችግሩ ወስጥ መዉጫ መንገዱንም የሚጠቁሙ ፍልስፋና በመሆን ያገለግላል፡፡ (ወንድዬ ካሳ፣50)፡፡ላይ በጥናታዊ ጹሑፉ ይገልጻል፡፡

የማህበራዊ ሂስ ዋነኛ ዓላማዉ በዘመናዊነት ስሌትም ሆነ በሌላ ጉዳይ ሰዎች ችግር ዉስጥ ገብተዉ መልሰዉ ከገቡበት ችግር የሚወጡበትን መንገድ ማመልከትና ማሳየት ነዉ፡፡ቀጣዩ ሃሳብም ይህንኑ ጉዳይ እንደንረዳ ያደርገናል፡፡

በዚህ አልፎ ያላለፈና ሌሎች አጭር ልቦለዶች ዉስጥም ስነ ምግባራዊና ማህበረሰቡ የደነገጋቸዉን ማህበራዊ ጉዳዮች በመዘንጋት ገጸ ባህሪያት ያላስፈላጊ ድርጊቶችን ሲያደርጉ እንመለከታለን፡፡ከዚህም አልፎ ያለ ቤተሰብ ፍቃድ አልባሌ ቦታ በመዋልና ከቤተሰብ ቁጥጥር ዉጭ ነን በማለት ገጸ ባህሪያቱ እኩይ ተግባራትን ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ ገጸ ባህሪያትም መልካም ስነ ምግባርን በመጎናጸፍ የህይማኖት አስተምሮቶችንና ህጎችን በመጠበቅ ቤተሰባቸዉን በማክበር በመንከባከብ በማህበረሰቡ ዘንድም ተቀባይነት ኑሯቸዉ ሲንቀሳቀሱ ሌሎች ደግሞ በተቃራኔዉ ይታያሉ፡፡

#### 4.1.1.7 ከዘመኑ ጋር ያልተበረዘ የመልካም ስነ ምግባር ማሳያ

…ሰለሞን ግን ትንሽ ሳይለይ አይቀርም፡፡ቢያንስ በሚያምሩ ልብሶች ቡቲስ ጫማዎች ክላሲክ ሽሚዞች ሽፋን ሊሸዉደኝ አልሞከረም፡፡ለነገሩ እኔ ብቻ እየተሰማኝ ያለዉ ነገር እንዴት እሱን እንደማይሰማዉ መናገር እችላለሁ፡፡ዓይኖቹ ሲያፍሩና ሲሸማቀቁ ተመለከትኳቸዉ፡፡የመጀመሪያዬ ነሽ ሰዉ በዚህ መልኩ ቀርቤ አላዉቅም!"አይዞህ ትለምደዋለህ አልኩት፡፡ጸጥ አለ ሌላ የምናወራዉ ነገር ከሌለን ብሄድ ደስ ይለኛል! አልኩት፡፡ (ሱለይ አደም፣ገጽ፣70-77)፡፡

መልካምና እኩይ ድርጊትና ምግባር ተብለዉ እንደተገለጹት ሁሉ የሰዉ ልጅ ባህሪዉና ጠባዩ ለግብረ ገባዊነት ማሳያ ናቸዉ፡፡ከዉስጣዊ ማንነቱ ዋነኞቹ የሆኑት ባህሪና ጠባይ በጊዜና ሁኔታዎች ለዉጥ ሊለወጡ የሚችሉ ናቸዉ፡፡የሰዉ ልጅ ባህሪዉን የሚያገኘዉ ከአካባቢዉ እንደመሆኑ መጠን ግብረ ገባዊ ጉዳዮችን ስንመረምርም ያለዉን ግብረ ገብ ብቻ ተቀብሎ የሚኖር ሳይሆን ወደ ተሻለና የላቀ ወደሚባል የግብረ ገብ ደረጃ የሚደርስበት ጽንስ ሃሳብ ላይ መድረስ አለበት፡፡ ሰለሞን በሀቀኝነት ያለዉን ምግባር ይዞ የቀጠለበት መንገድም፣ሂራን ከሌሎች ሳይሻል አይቀርም በማለት የገለጸችበትን መንገድ ስናስተዉል እኩይ ድርጊትና መልካም ድርጊቶችን እንድናጤንና የቱ የተሻለ እንደሆነም ሀሳብ እንድንሰጥና ህሊናችንን እንድንመረምር ይጋብዛል፡፡

## 4.1.1.8 ምርቃት በባህል የመልካም ስነ ምግባር መገንቢያነት

በሁላችን ሁኔታ የተደመመ የመሰለዉ ሰለሞን ዓይኖቹ ደስታን አርግዘዉ አዩሁ፡፡ሳልመጣ በፊት ገምቸዉ የነበረዉ ነገር ተሳካ፡፡እሳቸዉ ግን ዓይነ ስዉር ይሆናሉ ብዬ በፍጹም አልገመትኩም ሰለሞን "እማ ቡናና ድፎ ዳቦ ይዛ ነዉ የመጣችዉ መርቂያት!" አላቸዉ፡፡ይሆኑትን አጡ፡፡ እንደሰሙት የደስታ መልክ ብዙ መሆኑን ያየሁት በሳቸዉ ነዉ፡፡መመረቅ ጀመሩ፡፡ረ-ዝም ምርቃቸዉ እንዳለቀ ተነስቸ ድጋሚ ተሳምኩ፡፡ …ባለ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የቡና ስኔዎች በነጭ ረከቦት አጣጥቤ አቀረብኩ፡፡(ሱለይ አደም፣ገጽ፣72-73)፡፡

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በርካታ ሀይማኖታዊ መርሆች አሉ ለምሳሌ፡-አስርቱ ትዕዛዛት ተብለዉ ከሚታወቁት መካከል እናት አባትህን አክብር፣አታመንዝር ፣አትስረቅ አትዋሽ፣ አትግደል፣ከአምላክህ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ የሚሉት ይገኙበትል፡፡የእምነቱ ተከታዮች እነዚህን ትዕዛዛቶች ለመፈጸም ይጥራል፡፡በዚህ አልፎ ያላለፈና ሌሎች አጫር ልቦለድ በሚለዉ የሰለይ አደም አጭር ልቦለድ ወስጥም የልቦለዱ ዋና ገጸ ባህሪያት በልቦለዱ ታሪክ ዉስጥ በተደጋጋሚ የእምነቱ ተከታዮች አጠናክረዉ የሚጠብቆቸዉንና የሚያከብሮቸዉን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ሲተላለፉና ሲተገብሩ ይታያሉ፡፡ሆኖም ግን ደራሲዉ ከስነ ምግባር አንጻር ማስተላለፍ የፈለገዉን አንባቢዎች ለእናት ያላቸዉ ፍቅር፣ከዚህም በዘለለ በ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የቡና ስኒዎች ቡና ማቅረባቸዉ ለእናትም ይሁን ለእናት ሀገር ያለዉነወ ፍቅር በማህበረሰቡ ዘንድ የገለጸበት መንገድ  አመላካች ነዉ፡፡ በዚህም ፍቅር እንዲጨምርና ሀይማኖታቸዉ በሚያዝዛቸዉ መልኩ ስነ ምግባራቸዉን

ማነጾ እንደሚገባቸወና ምርቃት ከመልካም ስነ ምግባር እንደሚመነጭ ለአንባቢያን ያስገነዘበበት መንገድ ነዉ፡፡

### 4.1.1.9 ያለ አግባብ ገንዘብ ማስገኛዎች

…‹‹የጀበናዉን ቂጥ እየመቱ አንጠፍጥፌዉ የሚጠጡ እንደሆነ አያያዛቸዉ ነገረኝ አንዷ ጎረቤታቸዉ እኔን እያዩ ጭላጭ የቀረ ሲኒያቸዉ ላይ የሚያዩት ነገር አላቸዉ፡፡ሌሎች ይጠቋቆማሉ፡፡ባላየ አያቸዋለሁ፡፡

ሴትዮዋ ሟርት ሙጥሟጥ ምናምን ነገር የሚያደርጉና መድሐኒት የሚቆርጡ፣ስራስር የሚበጣጥሱ ነገር ናቸዉ፡፡ፈራኋቸዉ››፡፡(ሱለይ አደም፣ገጽ፣75)፡፡

ገጸ ባህሪዋ በርካታ ስነ ምግባር የጎደለዉ ድርጊት ማህበረሰቡን ወክለዉ ይፈጽማሉ የሰለሞን ጎረቤቶች ሲፈጽሙ ታዝባለች ሆኖም ግን ይህን ዓይነት ስነ ምግባር በዘርና በጠንቋይ ማምለክ ለዉርደትና ለዉድቀት የሚዳርግ እንጅ የትም ለያደርስ እንደማይችል በሁለቱ ዓብይ ገጸ ባህሪያት አማካኝነት ያሳየናል የአብይ ገጸ ባህሪያቷ ከሰለሞን የመራቅና ሁለተኛ ዓይኑን ላለማየት የወሰነችብት ምክንትም የሰለሞን ጎረቤቶች በቡና ስኔ እንጥፍጣፊ ላይ ያደረጉትን የጥንቆላ ምንገድ በመጥላትና አጥብቃ በመቃወም ነዉ፡፡

ደራሲዉ ገጸ ባህሪያቱዋን በዝህ መልክ ያቀረባትም ሆን ብሎ ይህ ዓይነት ስነ ምግባር የትም ሊያደርስ እንደማይችል ለአንባቢያን ለማሳወቅ ካለዉ ፍላጎት የተነሳ ነዉ፡፡የአምላክን ተዕዛዝ እረስቶ ለጠንቋይ ተገዝቶ እንኳን ፍቅረኛሞችን ለማስተሳሰር ይቀርና ስንዝር እንኳን መራመድ የማይቻል መሆኑን ታሪኩ ያስገነዝበናል፡፡ልቦለዱም ይህ ዓይነት ስነ ምግባር ማለት አምልክን የመካድ ትዕዛዝን ያለ መፈጸም  በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳይከሰት ለማስገንዘብ ያለዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነዉ፡፡

ፖጅማን እንደሚገልጸው ቨርቹ ኤቲክስ ትኩረት የሚያደርገው ሆኖ መገኘት ላይ ነው፡፡ በተለምዷዊው ግዴታ ተኮር ስነ-ምግባር ውስጥ ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ የሚል የድርጊት ጥያቄ ሲጠየቅ፣ በቨርቹ/መልካም ስነ-ምግባር/ ውስጥ ግን ምን አይነት ሰው ነው መሆን የሚገባኝ የሚል የመሆን ጥያቄ የሚነሳበትና መልስ የሚያገኝበት ነው፡፡

ቨርቹ ኤቲክስ በራሳቸው ብርሃን የስነ-ምግባር ገጽታን እንደ እንቁ የሚያብረቀርቁ ሰዎችን፣ እንደነ ሙሴ፣ ኮንፊሺየስ፣ ሶቅራጥስ፣ አርስቶትል፣ ቡድሃ፣ እየሱስ፣ አብርሃም ሊንከን የመሳሰሉትን በምሳሌነት ይጠቅሳል፡፡ እነዚህም ስነ-ምግባርን ራሳቸውን ምሳሌ አድርገው ያስተማሩ እንደሆኑ በማዘከር ስነ-ምግባር የሚይዙት (ሆነው የሚገኙት) እንጅ የሚማሩት ብቻ እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡ አድርግ አታድርግ በሚል መመሪያን ማውጣትና ማስተማር ብቻውን እንደማይገባም "…these are role models, who teach us all what it is to be moral by example, not by precept." (Pojman, pp, 166) በማለት የሚገልጹት ሆኖ ማሳየት እንጅ መመሪያን አውጥቶ የሚደረግ የማይደረግ በሚል ማስተማር ብቻ በቂ አለመሆኑን ነው፡፡ እንደጠናም "ቨርቱ ኤቲክስ ጥረት የሚያደርገው እጅግ የላቀ ባህሪ ያለው

ሰው መፍጠርን ወይም መቅረጽን ነው፡፡ ዋና አላማውም ለሰው ልጅ የሚልቅ ባህርይን ማጎናጸፍ ነው፡፡" ጠና፣ (2009፣102) በዚህ ታሪክ ዉስጥም ይህንን ነዉ የሚያስገነዝበዉ፡፡

በአጠቃላም አልፎ,ያላለፈ አጭር ልቦለድ ከስነ-ምግባር ሂስ አንጻር ሲታይ አንባቢዎችን ጥሩ ስነ ምግባር ሊያስተምር የሚችል ነዉ፡፡ከማህበረሰቡ ባህላዊ የሥነ ምግባር መርህ አንጻር ሲታይ ዋናዉ ገጸ ባህሪ ሰለሞን ለእናቱ የሚያደርገዉ በጎ ስራና የሚከፍለዉ መሳወትነት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባነት ያለዉነዉ፡፡ ሊበረታታ የሚገባዉ ስነ ምግባር ነዉ፡፡ከሀይማኖት አንጻር ደግሞ የሄራን በጎ ስነ ምግበርና ሁሉም ነገር ያለ አምላክ ፍቃድ ሊሆን እንደማይችል ያሳያል፡፡ስለሆነም በአምላክ ማመን እንደሚገባና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶችን ያስተምራል፡፡

## 4.2 በዘመናይ ማርዬ የቀረበዉ አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

የአወል እናትና አባት አወልን እንደወለዱ አባቱ ከዚህ ዓለም በሞት ይለየዋል፡፡እናቱም አወሌን ለአባቱ እናት ጥላዉ ወደ ከበርቴ ቤተሰቦቾ ትሄዳለች፡፡አወሌ ከናትም ከአባትም በመለየት አያቱን እንደናትና አባት በማየት ከሷ ጋር በቅብጠት ያድጋል፡፡በመጨረም አያቱ እየደከሙ ሲመጡ ወስዳ ለከበርቴ ቤተሰቦቹ እና ለእናቱ ታስረክበዋለች አሷም አንጀቷ አልችል ብሎ እሱም ከአሳዳጊ አያቱ ሲለይ እየጨነቀዉ ከእናቱና ከእናቱ ቤተሰቦች ጋር ይቀላቀላለል፡፡ወዲያዉ እንግዳ ሆኖ በመጣ ቀንም እዘይት ያለዉ ምግብ ይበላና ሆዱን ይትመማል በዚህም አጋጣሚ እናቱ ትሸማቀቃለች፡፡ ወዲያዉም ብዙም ሳትቆይ ወደ አረብ ሀገር ትሄዳለች፡፡ አወሌም አዲስ ቤተሰብ አዲስ አካባቢ ተላምዶ ለመኖር ገደዳል፡፡ከበርቴ አያቶቹም በስራ ብዛትና እንግልት ያለ እረፍት እያገለገለ እንዲኖር ያደርጉታል፡፡ትምህርትም ያስጀምሩታል ቢሆንም ግን ከስራ ብዛት ከቁጣና ከእንግልት የዘለለ አልነበረም ትምህርቱ በዚህ አጋጣሚ ነበር ጎረቤት የነበረችዉን የትምህርተ ቤት ጎደኛዉን የተዋወቃት ዘመናይና አወሌ ቤታቸዉ ከመቀራረ የተነሳ ለሁለት የወሰዱትን መጽሐፍ እየተወዋሱ ያነቡት ነበር፡፡ሆኖም ዘመናይ የአወልን በቤተሰቦቹ የሚደርስበትን የስራ ጫና በመታዘብ አንዳንዴ ከሷ ጋር እንዲያጠና የፈቀደችለትና ለሱም እንደ መደበቂያ ሁና አብራዉ ሲያጠኑ ነበረዉ ቀረቤታ እየቆየ በአወሌ በኩል ወደ ፍቅር የተለወጠዉ፡፡በዝህም ከዘመናይ ጋር ተኮራርፈዉ ትምህርትም ተዘግቶ እስከሚከፈት ድረስ ሳይገናኙ ተጠፋፍተዉ ይቀራሉ፡፡

### 4.2.1 ዘመናይ ማርዬ ከስነ ምግባር ሂስ አንጻር

ስነ ምግባራዊ ሂስ በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የሥነ ምግባር መርሆችን መሰረት በማድረግ ዘመናይ ማርዬ አጭር ለቦለድ ላይ የአወሌ በህጻንነቱ መወቅና መማር እንዲሁም መልካም ስነ ምግባር እንዲኖረዉ ከቤተሰቦቹ መጀመርና በቤተሰብ ታንጾ ማደግ ሲገባዉ ያላስፈላጊ የስነ ምግባር በዘመዶቹ አስተዳደግ ሲደረግለት ይስተዋላል፡፡ከቤተሰቦቹ ፍቅር ተነጥሎ ሲኖርም በዘመዶቹ የተለያየ ስቃይና እንግልት ሲደርስበት ይስተዋላል፡፡

…ከዚህ በኋላ ነበር ከእናቴ ቤተሰቦች በሚደርስብኝ “እንጀራዉን ለምን ጨርሰህ አልበላኸም ? ትርፍ ነዉ ብለህ ነዉ ?ጠገብክ ማለት ነዉ ?ከብቶችን በጊዜ ለምን አታስወጣቸዉም ?ሱቅ ጠብቅ ማለት ገብተህ ሸጥ ማለት ነዉ ? በቢራ ጠርሙስ ለሚገዛ ሰዉ ዘይት ለምን ትመርቃለህ ? በኪስህ የተገኘዉን ሽልግ ከየት አመጣኸዉ ? የተጋገረዉን ድፎ ከአንተ ዉጭ ማንም አይቆርሰዉም ስለዚህ እንደቆረስከዉ ተናገር!”አይነትና መሰል ጭቅጭቅ ነበር፡፡ ልቤን ሰዉ የሆነ ሰዉ እንዲራብ ያደረገዉ፡፡ ደግሞ ሶላት ብለዉ ዉዱ አድርገዉ መስገጃ ላይ ይቆማሉ፡፡ቁራዓን ቀልድ መስሏቸዉ ያነበንባሉ፡፡የመሰጅዱ አባ-ሾሾችን ሲመጡ ያረግዳሉ፡፡ዱዓ ብለዉ ጫት ይዘዉ ይቀመጣሉ፡፡ሶደቃ ብለዉ የከተማዉን ከበርቴ ሰብስበዉ ያበላሉ፡፡

እኔን ከሰዉ ቢቆጥሩኝ ሃጃቸዉ ይወጣ አልነበረም ? ዘመድ ሲያገኙ ደግሞ የዘይነባ ልጅ ነዉ!” ይባልልኛል፡፡እንግዳኮ እንዲስመኝ ነዉ፡፡ቀድመዉ እነሱ ስመዉ ነበር ሰዉ እንዲስመኝ መናገር የነበረባቸዉ፡፡አስመሳይነት የሰዉ ልጆች ድብቅ ባህሪ እንዳለ ከነሱ ነዉ የተማተርኩት፡፡ (ሱለይ አደም፣ከገጽ 35-36)፡፡

ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ለልጅ ስላላቸው ስነ-ምግባራዊ ግዴታን በተመለከተ ጠና የሚከተለውን ያስቀምጣሉ፡፡

ሁሌም ለልጅ ፍቅር ማሳየት፣ የልጆችን ፍላጎት ማወቅና ማክበር፣ የሌላውን ወገን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ማፍቀርና ማክበር፣ ልጆችን ከማናቸውም ጎጅ ነገሮች መከላከል፣ የሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ለልጆች መማሪዎች ናቸው፡፡ በማለት ሁሌም መልካም ቦታዎች እንዲገኙ መርዳት፣ ልጆች በበጎ ምግባር እንዲታነጹ መምከር ወይም ማገዝ፣ ልጆች ትህትናን፣ ቅንነትን፣ ግልጽነትን፣ታማኝነትን እንዲማሩ መርዳት፣ ባንጻሩ መልካም ያልሆኑ ነገሮችን እንዲጠየፉ ማድረግ፣ ልጆች የሀገርና የወገን ፍቅርና አክብሮት እንዲያድርባቸው ማድረግ የሚሉት ኢትዮጵያዊ ቤተሰባዊ የስነ-ምግባር ግዴታዎች እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፡፡ ጠና (2009፣268)

ከላይ የተጠቀሱትን መልካም ነገሮችን የማድረግ ተነሳሽነቱ የሚመነጭበትን መንገድም ከምንና በምን አይነት ሰው እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡ ግብረ-ገባዊ /ስነ-ምግባራዊ/ እውቀት ጥልቀት ካለው አስተሳሰብና ከአርቆ አስተዋይነት የሚመነጭ ነው፡፡ በቂና በሳል ግብረ-ገባዊ ዕውቀት የቀሰመ ሰው በስሜት፣ በስጋዊና ቁሳዊ ፍላጎት የሚነዳ ወይም የሚገፋ አይደለም፡፡ በሚግል ወይም በሚቀዘቅዝ ስሜት አይመራም፡፡ ይልቁንም የማመዛዘን ችሎታ ያለው በፈቃደኝነት ለበጎ ተግባሮች የመነሳሳት ፍላጎት ያዳበረና ራሱን በራሱ የማዘዝ አቅሙ ነጥሮ የወጣ ነው፡፡

በዋና ገጸ ባህሪዉ በአወሌና በዘመዶቹ መካከል ያለዉን በፈጣሪ የማመንና የፈጣሪን ተዕዛዝ ለይስሙላ ወደ ኋላ ብለዉ ከላይ ሲታዩ መልካም ቀርበዉ ሲታዩ እኩይ መሆናቸዉን ዋና አስመሳይነትን እንጅ እንደ ጠና ገለጻ መልካም ስነ ምግባርን አያንጸባርቅም፡፡

፤ደራሲዉ በዋና ገጸ ባህሪያቱ አማካኝነት የአስመሳይነት እኩይ ባህሪን ሲያንጸባርቅ ይታያል፡፡ በዚህም የሰዉ ልጅ በፈጠሪ ታምኖ ሁሉንም በእኩል ዓይን ማየት እንደሚያስፈልግና በተለይም ህጻናት ከናት ከአባታቸዉ ተለይተዉ በዘመድና በተለያዩ ወገን ቤት ሲያድጉ ግብረ ገብነት በጎደለዉ መልኩ ታንጸዉ ሊያድጉ እንደሚችሉና በህጻንነት በለጋ ዕድሜያቸዉ መልካም ባህሪያትን ከቤተሰብ ወርሰዉ ቢያድጉና ግብረ ገብነት ትምህረት ከቤት ቢጀመሩ አሁን ላለንበት ዘመን ዕየታዩ ላሉት የስነ ምግባር መጓደል ክፍተቶችን መቀነስ እና ማስቀረት እንደሚቻል በታሪኩ አማካኛነት ከተደራሲያን የተገኘዉ የድርሰት ስራ የሚያሳይ ነዉ፡፡በተለይ ስነ-ጹሑፉ በአጭር ልቦለድ ዉሥጥ የስነ መግባር ጉዳዮችን አካቶ ማቅረቡ ለተደራሲያን ከፍተኛ ፋይዳ እንደለዉ ከዋና ገጸ ባህሪዉ መረዳት ያስችላል፡፡ ለስነ ምግባር መጓደልም ስነ -ጹሑፉ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ከዚህ ታሪክ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በታሪኩ የቀረበዉም የህጻኑ ከቤተሰብ እይታና እንክብካቤ ዉጭ ማደግ፣ መልካም የስነ ምግባር እሴቶችን ከማህበረሰቡ አለማዳበርና ከሌሎች እኩይ ምግባር መቅሰም ለነገ የስነ ምግባር መጓደል አንዱ ምክንያት መሆኑን ታሪኩ ያስገነዝባል፡፡

## 4.2.2 የሰባዊነት መንጠፍ በዘመናይ ማርዬ አጭር ልቦለድ ዉስጥ

ዮናስ (1992፣108) የሰባዊነት መንጠፍ በህሊና መጠቀም አለመቻልንና (ከማህበረሰቡ ስነ ምግባር መዉጣትን) የግል ነጻ ፍቃድን፣አሳልፎ መስጠትን ይመለከታል፣በሌላ በኩል ሰዎች ሰዉነታቸዉ ተረጋግጦ ሰባዓዊ መብታቸዉ ተዋርዶና ተንቆ ከለእንስሳት እና ከዕቃት ተራ ተመድበዉ የሚታዩበትን እነሱም ይህንን የሚያገናዝቡበትን ሁኔታ ያመለክታል ሲል ጠቅሶል፡፡

በዚህ ልቦለድ ታሪክ ዉስጥም በዋና ገጸ ባህሪያትና በከበሪቱ ቤተሰቦቹ መካከል የሚደረገዉ ዋናዉ ገጸ ባህሪ አወሌ በዘመዶቹ ሰዉነቱ ተረጋግጡ ሰባዊ መብቱ ተዋርዶና ተንቆ ከእቃ ተራ ተመድቦ እያለ ዘመዶቹ ግን ዘንጠዉና በምቾት ተደላቀዉ ይኖራሉ፡፡ከዚህም በዘለለ ዋናዉ ገጸ ባህሪ አወሌ ከቤተሰቦቹ ያስመሳይነት ስነ ምግባር እንዲኖረዉ በህጻንነት እድሜዉ የሚመለከታቸዉና የሚታዘባቸዉ እኩይ ስነ ምግባሮችንና የሰባዓዊነት መነጠፍ አንዱ መከሰቻ አስመሳይነተ መሆኑን በታሪኩ ያሳያሉ፡፡

## 4.3 ልጅን አደራ አጭር ልቦለደ ጭምቅ ታሪክ

እናትና አባቷን የማታዉቅ እመነን የምትባል ወጣት ኑሮዋን ያለ አጋዥ ለብቻዋን እየመራች የናትና የአባቷን ጥያቄ በልቧ ጥያቄ እየፈጠረባት ስትኖር ከለታት በአንድ ቀን ወደ ስራ እየሄደች እያለች ጎረምሳ ወጣቶች መንገድ ላይ አቁመዉ በማንቋሸሽ ካልገረፍንሽ አናሳልፍሽም በማለት የለበሰችዉን ልብስ ጨምድደዉ በመያዝ ይታገሏታል፡፡እመነንም ልብ በሚነካ መልኩ ከምታስበዉ የህይወት ጥያቄ ጋር ሁና እባክህ ልቀቀኝ ልሂድበት በማለት ትማጸናለች፡፡በዚህ አጋጣሚ ከየት መጣ የማይባል ረዥም ሞጋጋ ሰዉዬ ፈርጣማዉን ወጣት ልቀቃት በማለት ይሳፈጠዋል፡፡ወጣቱም ደንደና ስለነበር እመነንም ‹‹የኔ ጦስ ለዚህ ሰዉዬ ተረፈዉ በማለት ስትፈራ ስትቸር ሞጋጋዉ ሰዉዬ በንዴት ልቀቃት ሲለዉ ወጣቱ

ሞጋጋዉን ሰዉዬ ሊመታ ሲሞክር ወጣቱ የሰነዘረዉ ቡጢ የራሱን ከንፈር በመምታት ደም በደም ይሆናል፡፡ደግሞ ሲሞክር እጁን ይሰበራል፡፡ሞጋጋዉ ሰዉዬም ሁለተኛ ብትሞክር ነፍስህ ይወጣል በማለት ያንገራግረዉና ልጅትን ካስለቀቀ በኋላ ሁለተኛ እንዳትነካት ሴት ልጅ ለዚያዉም የጀግና ልጅ ይለዋል፡፡የጀግና ልጅ የሚለዉን ስትሰማ እመነን በአእምሮዋ ከሰማይ የወረደላት መልዕክ መስሎ ታያት በብቸኝነቷ ላይ አይዞሽ የሚል ሰዉ በማግኘቷ በሌላ ጊዜም ተመሳሳይ የወጣቶች ጋጋታ ያለበት ቦታ ወጣቶች ብቻዋን ሲያገኞት በማቄም ምንሽን እንምታሽ እያሉ ሲያንገራግሮት ሞጋጋዉ ሰዉዬም ከየት መጣ ሳይባል ይደርስና ምን እየሰራችሁ ነዉ ልቀቋት ሲላቸዉ ይሳለቁበታል፡፡በዚህ ንዲቱም ተሰብስበዉ የነበሩትን ስድስቱን ወጣቶች በታትኖ ይጥላቸዉና እመነን ሂጅ ይላትል፡፡እመነንም ሰዉዬዉ እየተከታተለ ሲያድናት ምንም ይሁን ምንም ሰዉ ከጎኔ አለኝ ፈጣሪ ይመስገን ትላለች፡፡በመጨረሻ ላይም እመነን የምትሰራበትን ቤት ጠይቆ አለመኖሯን አረጋግጦ እንደወጣ መንገድ ላይ በጥይት ተመቶ ይሞታል፡፡

በኪሱ ዉስጥም የመታዉቀዉና ጥያቄ ሲፈጥርባት የቆየዉ አባቷ ለእመነን የላከላት አድራሻና ማንነት ይገኛል፡፡ለእመነንም በፖሊሶች ተጠርታ ይሰጣታል፡፡ሞጋጋዉ ሰዉዬ ለእመነን አባቷ ሆኖ ይገኛል፡፡ደብደቤዉም ከማታዉቀዉ አባቷ ዘንድ የተላከ መሆኑን ስታረጋግጥ የደም እንባ ታነባለች፡፡

የካሪም ስነ-ጽሑፍ እንደተጻፈበት የእምነት ወይም ባህል አንጻር በስነ-ምግባር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ለመረዳት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም አሳዛኝ ታሪኮች የሚዋቀሩት ህግን በተላለፉ ወይም ከስነ-ምግባር ደንብ በወጡ ገጸ ባህሪያት ድርጊት ላይ ተመርኩዘው በመሆናቸው ነው፡፡

“The changing face of moral visiton in the amharic novel” በሚል ርዕስ የቀረበው የዶክተር Tena Shale ጥናት የሚያረጋግጠውም ይህን የስነ-ምግባርንና የስነ-ጽሑፍን የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡

As can be perused from existing accounts of the origin and development of Amharic literature, morality continues to be the central concern of the Ethiopian writer. This is attested by many scholars who researched into the early stages of the literature, chief among whom are S.Wright (1963), A. Gerard (1968, 1971), T.L.Kane (1975), and R.K.Molvaer (1980). Tena, (2007,4)

ጠና በእውቅ ሊቃውንት በS.Wright (1963), A. Gerard (1968, 1971), T.L.Kane (1975), and R.K.Molvaer (1980). የተጠኑትን ጥናት ዋቢ አድርጎ እንደገለጸው የአማርኛ ስነ-ጽሑፍ ከመሰረታዊ እሳቤ ጀምሮ እያደገ በመጣበት ሂደት ሁሉ ስነ-ምግባር የኢትዮጵያዊያን ደራሲዎች ዋና የትኩረት ማእከል ሆኖ እንደዘለቀ ያስረዳል፡፡ እንደ ጠና ገለጻም የኢትዮጵያን ደራሲወች መልካሙን በማመስገን ክፉውን ደግሞ በመቃወም የተሰሳተችን ነፍስ በመታደግ በኩል ባለ ውለታ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን የተለመደ

አካሄድ በማጽደቅ በኩል ከፍተኛ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ (በTena 2007 ገጽ 4 ውስጥ የተጠቀሰ)፡፡

Molvaer በበኩሉ ከ1923 -1974 ያለውን የስነ-ጽሑፍ ጉዞ በማጥናት የአንድ የስነ-ጽሑፍ ስራ የስነ-ምግባርን ጉዳይ ቀዳሚው ያደረገ ከሆነ ብዙ የአማርኛ ስነ-ጽሑፎች ከበሬታ እንደነበራቸው አመላክቷል፡፡ Having studied the literature of the period, 1923 - 1974, Molvaer also points out that “a preoccupation with moral issues… is prominent in much of Amharic literature.” (ገጽ፣4). Tena በተጨማሪም የሞልቤርን ሀሳብ ወስዶ በሚከተለው መልኩ አስቀምጦታል፡፡

“It is worth noting that the pioneers, namely Afeworq Gebreyesus and Heruy Woldeselasse, who introduced the art of writing the novel into the literature, dedicated their works to the purposes of upholding and teaching morality”. Tena, (2007, 4)

ጠና እንደሚገልጸው በኢትዮጵያ ውስጥ በስነ-ጽሑፍ ፊር ቀዳጅ የሆኑት አፈወርቅ ገብረየሱስ እና ኅሩይ ወልደ ስላሴ የልቦለድ አጸጻፍ ጥበብን ከስነ-ጽሑፍ ጋር ያገናኙ እንደሆኑ የስነ ጽሑፍ ስራቸውም ለአንድ ነገር ዓላማ መዋል እንዳለበት፣ ይኸም ስነ-ምግባርን መደገፍና ማስተማር ላይ ትኩረት ያደርጉ እንደነበር ይገልጻል፡፡

በዚህ አሳዛኝ ታሪክ ዉስጥም ደራሲዉ ህግን በተላለፉ ወይም ከስነ-ምግባር ደንብ በወጡ ገጸ ባህሪያት ድርጊት ላይ ተመርኩዘው ስነ-ምግባርን መደገፍና ማስተማር ላይ ትኩረት ያደርጉ እንደሆነ ነዉ፡፡ በታሪኩ ዉስጥ የቀረበችዉ እመነን ህገ ወጥ ስነ ምግባርና ስብዕና በጎደላቸዉ ሰዎች የተለያዩ ስቃይና እንግልት ሲደርስባት፣ በሌላ በኩል ከየት መጣ የማይባል ረጅሙ ሰዉ እየመጣ ሲያድነት፣መጨረሻ ላምይ እመነንን መጥፎ ነገር እንዳይደርስባት ሲከታተል ህግን በተላለፉ ወይም ከስነ ምግባር በወጡ ሰዎች ሲገደል ደራሲዉ ስነ ምግባርን በመደገፍና በማስተማር በታሪኩ ያስዳስሳል፡፡በዚህም ስነ ምግባር ለአን ተግባርና አላማ መዋልና ማስተማር እንዳለበት አሰይቷል፡፡

## 4.4 ጀሮዬን ጣፈጠኝ አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

ሁለት እንደ ቤተሰብ የሚተያዩ ሙስሊምና ክርስትያን አያ ሙላትና ሸኽ ከድር በጉርብትና ይኖሩ ነበረ፡፡የተለቀ ፍቅርም ነበራቸዉ፡፡ልጆቻቸዉን እንደ ልጃቸዉ በማየት ያሳድጉ ነበር፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን ሸኽ ከደር ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ፡፡ልጆችና ቤተሰቦቹ ከቀበሩት በኋላ የሸኽ ልጆች በባዶነት ይዋጣሉ፡፡

አያ ሙላት በጎደኛዉና በጎረቤቱ ሸኽ ከድር ሞት ከዉስጡ እርር ብሎ ከማዘኑም በላይ የሸኹ ልጆች እንዳይርባቸዉ፣ እንዳይጠማቸዉ፣ እንዳይታረዙና ትምህርታቸዉን እንዳያቋርጡ፣ሸኽ ከድር አስጀምረዋቸዉ የነበረዉን የቁራን መቅራት ትምህርት እንዲከታተሉ በማሰብ የአባታቸወን ኃላፊነት ምትክ በመሆን እንዳባት እየመከሩና ሲያጠፉ

እየገሰጹ በቤታቸዉ የሚበሉትን እያካፈሉ አባታቸዉ እያለ ያስጀመራቸዉን የቁራን ትምህርት አስቀጠላቸዉ፡፡የሰፈሩ ሰዉም በሳቸዉ መልካም ድርጊት በመገረም አንቱታን አሰጣቸዉ፡፡መንገድ ላይም አያ ሙላትን ሲያገኙ ቁመዉ ማሳለፍ ጀመሩ፡፡በአካባቢዉም ትልቅ ጸጋና ክብር ተጎናጽፈዉ መኖር ቻሉ፡፡

ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ለልጅ ስላላቸው ስነ-ምግባራዊ ግዴታን በተመለከተ ጠና የሚከተለውን ያስቀምጣሉ፡፡

ሁሌም ለልጅ ፍቅር ማሳየት፣ የልጆችን ፍላጎት ማወቅና ማክበር፣ የሌላውን ወገን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ማፍቀርና ማክበር፣ ልጆችን ከማናቸውም ጎጅ ነገሮች መከላከል፣ የሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ለልጆች መማሪዎች ናቸው፡፡ በማለት ሁሌም መልካም ቦታዎች እንዲገኙ መርዳት፣ ልጆች በበጎ ምግባር እንዲታነጹ መምከር ወይም ማገዝ፣ ልጆች ትህትናን፣ ቅንነትን፣ ግልጽነትን፣ታማኝነትን እንዲማሩ መርዳት፣ ባንጻሩ መልካም ያልሆኑ ነገሮችን እንዲጠየፉ ማድረግ፣ ልጆች የሀገርና የወገን ፍቅርና አክብሮት እንዲያድርባቸው ማድረግ የሚሉት ኢትዮጵያዊ ቤተሰባዊ የስነ-ምግባር ግዴታዎች እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፡፡ ጠና (2009፣268)

ከላይ የተጠቀሱትን መልካም ነገሮችን የማድረግ ተነሳሽነቱ የሚመነጭበትን መንገድም ከምንና በምን አይነት ሰው እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡ ደራሲዉ ዋና ገጸ ባህሪዉ አያ ሙላትን በመወሰድ ገልጾታል፡፡ ‹ስለ አያ ሙላት ሳወራ የምናብ ፈጠራ እንደሚመስል አዉቃለሁ፡፡እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ከመነጋገር በመቆጠባችን ልባችን ሻክሮ ይሆናል፡፡ሰዉ ሲኖር በዓለም እነደ አያ ሙላት ቢሆን መላዕክት ስራ ባጡ ነበር፡፡…አያ ሙላት የሚደንቁኝ በዚህ ብቻ አይደለም፡፡ሰዉየዉ ከመገረምም፣ከመደነቅም በላይ ከፍ ይላሉ፡፡ስራዎችቸዉን ያስተዋሉ ሰዉ ሰዉ የመሆንን ክብር ገልቶ ያያል (ሰለይ፣177-80)፡፡

በዚህ ታሪክ ዉስጥም ዋና ገጸ ባህሪዉ መልከምነትን ከአስተዋይነት ጋር በማቀናጀት ይገልጻል፡፡ ጠና (2009፣212) ግብረ-ገባዊ /ስነ-ምግባራዊ/ እውቀት ጥልቀት ካለው አስተሳሰብና ከአርቆ አስተዋይነት የሚመነጭ ነው፡፡ በቂና በሳል ግብረ-ገባዊ ዕውቀት የቀሰመ ሰው በስሜት፣ በስጋዊና ቁሳዊ ፍላጎት የሚነዳ ወይም የሚገፋ አይደለም፡፡ በሚግል ወይም በሚቀዘቅዝ ስሜት አይመራም፡፡ ይልቁንም የማመዛዘን ችሎታ ያለው በፈቃደኝነት ለበጎ ተግባሮች የመነሳሳት ፍላጎት ያዳበረና ራሱን በራሱ የማዘዝ አቅሙ ነጥሮ የወጣ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊ የስነ-ምግባር መገለጫን ከሙሉው በጣም በትንሹ ወስደን ስንመለከተው የሀገራችን ህዝብ በስራ፣ በአኗኗር፣ በእምነት፣ በአመለካከትና በመሳሰሉት ዙሪያ በፈጠራቸው የወንድማማችነት ወይም እህትማማችነት፣ የጓደኝነት ወይም የወዳጅነት፣ የጉርብትና ወይም የዝምድና ግንኙነቶች ውስጥ የመፈቃቀድ፣ የመረዳዳትና የመተባበር ባህል አለው፡፡ የሞተን በስርኣት ይቀብራል፡፡ የተረዳን(መርዶ) ሰው በአግባቡ ያስተዛዝናል፣ የታመመንና የታሰረን ይጠይቃል፣ አደጋ የደረሰበትን ይረዳል፣ ያጽናናል፣ … ትንሹ ትልቁን በአግባቡ ያከብራል፡፡ ትልቁም ትንሹን ያፈቅራል፣ አንዱ ሌላውን ያምናል፣ በተራውም በእርሱ ይታመናል፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች ሲከሰቱ አብሮ ይቆማል፡፡ የሚሉትን የመልካም

ስነ-ምግባር መገለጫዎችን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡ በዚህ ታሪክ ላይም ይህንን ጉዳይ ያስገነዝባል፡፡

## 4.5 የአንድ ነፍስ ጨኸት አጭር ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

አንድ ወጣት የእነቱ ህመም በየዜዉ ሲጠናባቸዉ ከስራ ጫና ለማሳረፍ ሰራተኛ ያፈላልጋል፡፡በራሱ አፈላልጎ ማግኘት ስላልቻለና አብዛኛዎቹ ወደ አረብ ሃገር እንደሄዱ ሲያዉቁ በደላላ እንዲፈለግለት በማድርግ ዘቢባ የምትባል ወጣት ያገኛል፡፡ደላላዉ ወደ ቤት ይዞ በመምጣት የደለለበትን ብር ይቀበላል፡፡የወጣቱ እናት እጅግ አሩሩ በመሆናቸዉ ከዚህ በፊት የነበሩት ሰራተኞችም ከታዛዥነት ወደ አዛዥነት ሲቀየሩባቸዉ ልጆችም ሁኔታቸዉን በማጤን ተመካክረዉ ያሰናብቷቸዋል፡፡ዘቢባን እንዳዩት እናትዮዋ በእናት በእናት ጥያቄ ይጠይቋታል፡፡ወጣቱም እናቱ ለዘቢባ እንዳዘነችና ዉስጠ እንደራራላት ያስተዉላል፡፡ከዚህ በፊት በስንት ብር ትሰሪ ነበር ስትላት ህለት መቶ አለች ዘቢባ ወዲያዉኑ ወጣቱ እናት ቀበል በማድረግ ምነ አፈር በበላዉ በማለት ሶስት መቶ ሃምሳ እኔ እከፍልሻለሁ፡፡በማለት በእሽታ ተስማምተዉ ዘቢባም ወደ ስራዋ ትገባለች፡፡ስራ በጀመረች በሁለተኛዉ ቀን ዘቢባ ከባድ የደም መፍሰስ የነስር ህመም ያማታል ደምም እንደጎርፍ ይዘምባታል፡፡ልጆችም እናትዬዋም በአዩት ነገር ተደናግጠዉ ከጠየቋት በኋላ ሁሌም እንደሚያስቸግራት ሲያዉቁ እንሸኛት ለማለትም ይከብዳቸዋል፡፡መጨረሻ ላይም እሄዳለዉ ሰተል መታከሚያ ብር በመስጠት ይሸኞታል፡፡

ማነኛውም ሰው ሲወለድ የራሱን ክብርና መብት ተጎናጽፎ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ምክንያታዊነቱ እና በህሊና መታደሉ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የተለየ ክብር እንዲሰጠው አድርጎታል፡፡ በምክንያታዊ እና በህሊና የተገነባ መሆኑ ደግሞ ስነ-ምግባራዊ/ገብረ-ገባዊ/ እየተባለ እንዲጠራ አስችሎታል፡፡ "every person endwed with reasons and conscience is a name of moral status." (lenner, 2004:70) የሰው ልጅ ክብር የተለየ እና የእሴቶች ከፍተኛ መለኪያ/ልኬት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን፣ ምክንያታዊ ያልሆኑ ነገሮች የሚታደሉት አይደለም፡፡ ‹‹እረ ይቺ ልጅ ፈጣን ናት!›› ‹‹እረ ይቺስ ንቁ ናት!›› ብለን ያአፋችንን ሳንጫርስ ልናሰናብታት ተነሳን፡፡በዚህም ነበር ለሁለት የተከፈልነዉ፡፡ ባለባት የጤና እክል ምክንያት እሷዎ አዉቃ እራሶን ያሳመመች ይመስል እንዲህ ‹ትሂድ !› ሲባል ለእኔ አልቀለለኝም፡፡ አንድ የጋራችን የሆነ ችግር እሷ ላይ ተከምሮ እያየነዉ እንደቀላል አብሬ ‹ትሂድ!› ማለት ዘገነነኝ፡፡ (ሱልይ፣157) በዘህ ታሪክ ዉስጥም ሰባዊ ክብርን የሰዉ ልጅ የሚረዳበትነ መንገድ ከስነ ምግባራና ከኃሊና ጋር የተቆረኘ እንደሆነ በመገንዘብ በሰባዊ ፍጡር የመረረ ጭካኔን ለማድረግ የሞራል ሕግጋት እንደማይፈቅድ በታሪኩ ያስገነዝባል፡፡ በተጨማሪም Kaufmann እንደሚለው the theoretical discussion about human dignity usually starts with abstract values such as the sanctity of life or with human capacities such as autonomy, rationality or moral agency (Kaufmann, 2011:1)

እንደ ካውፍማን ገለጻ ሰባዊ ክብር የላቀ የስነ-ምግባር መገኛ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜም የሰው ክብር ከህይወት ቅድስና፣ ራሱን በራሱ ከማስተዳደር፣ ምክንያታዊ እና የስነ-ምግባር እንደራሴ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚገለጽ ነው፡፡

ሰባዊ ክብር ውርደትን፣ በተበላሸ ስነ-ምግባር መለካትን፣ ስቃይን፣ ድህነትን፣ ጦርነትን እና ባርነትን የሚያሳስብ ሀቲት እንደሆነ እና ክብር ባለበት ሁልጊዜም የሰባዊ ክብር መጣሻ መንገዶች ከጎን አይጠፉም የሚለው ሌላው የካውፍማን እሳቤ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰባዊ ክብር ስነ-ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችንና ልምዶችን ለመግለጽ ተስማሚ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ እነዚህ ስነ-ምግባር የጎደላቸው ልምዶችና ድርጊቶች አሁን በዘመናችን እየተተገበሩ መሆናቸውንም በልቦለዱ ታሪክ ዉስጥ ያትታል፡፡

‹‹ በጤና ልንጠቀም ያመጣነት ሰራተኛ በጤናዋ ልንጠቀም ያሰብነዉን ያክል በችግሯም ልንቸገር አለመፍቀዳችን ራስ ወዳዶች መሆናችንን ነገረኝ፡፡በመጣች በስምንተኛ ቀን ፊቷ የመጣች ጊዜ የነበረዉ መሆኑ ቀርቶ የበለጠ ገረጣ አሁን እጅግ አሳዘነችኝ፡፡(ሱለይ፣158)፡፡

የሰው ልጅ ክብሩን በተለያየ መንገድ እንደሚቀንስም፣ Bayertz 1996, Kretzmer and Klein 2002, Stoecker 2003) በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡ የሰው ልጅ ምንም እንኳ ከሌሎች በተለየ ክብር የታደለ ቢሆንም፣ ይኸው ክብሩን ጠብቆ እና አስጠብቆ እስከመጨረሻው ሲዘልቅ አይስተዋልም፡፡ በዚህ ዘመን የሰው ልጅ ክብር መሰረታዊ የህግ፣ የስነ-ምግባር እና የፖለቲካ ሀቲት ወይም ጉዳይ እየሆነ መምጣትም አንዱ የሰባዊ ክብር ጥሰት መብዛት እና ውስብስብ ባህሪ ያለው መሆኑ ነው፡፡ የሰባዊ ክብር ጥሰት በተለያዩ ቅርጾች ይገለጻል፡፡ ውርደት፣ መበላሸት፣ መበስበስ የሚሉ ቃላት የሰባዊነትን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ ገጽታዎች ናቸው፡፡ ክብር በግለሰቦች ብቻ የሚታደል አይደለም፡፡ ክብር ከግለሰብም ከፍ ብሎ በቤተሰብ፣ በቡድን፣ በድርጅት በጣም ስናሳድገውም እንደ ሀገር የምንይዘው ጸጋ ነው፡፡ እያንድ አንዱ ግለሰብም በቡድኑ ውስጥ ስላለው ክብር ተጋሪ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ በዚህ አጭር ታሪክ ዉስጥም ገጸ ባህሪዋ የሰባዊ ክብሯን በማይነካ መልኩ በሰራተኛነት ተቀጥራ ለመስረተ ብትሞክርም በጤና ችግሯ መስራት ስላልቻለች ሰባዓዊ ክብሯን አጥታ ከቤት ቤት ስትንከራተት አንዳንዱ ሰባዊነት የሚሰማዉ በማሳከምና ደሞዝ በመስጠት ሌላዉም በተቃራኒዉ በማድርግ ቤት ለቤት ስትንከራተት ያሰየናል፡፡

Margalit በበኩሉ፣ “Humiliation is any sort of behaviour or condition that constitutes a sound reason for a person to consider his or her self-respect injured” (Margalit 1996: 9).

እንደማርጋሊት አገላለጽ ውርደት አንድ ሰው አክብሮት እንደጎደለው ለመቆጠር የሚያስችለውን ትክክለኛ ምክንያት የያዘ ማንኛውም አይነት ባህሪ ወይም ድርጊት ነው፡፡ ይሁን እንጅ አንድ ሰው ውርደቱ በትክክል ሳይሰማው ተዋርዶ ሊገኝ ይችላል፡፡ “Someone can feel humiliated without in fact being humiliated. And one can respond to a humiliation with different feelings, or stoic indifference.” በማለት እንደሚገልጸው፣ ውርደት በተለምዷዊ አረዳድ አንድ ሰው እንደ ሰው ሰከተጎናጸፈው የክብር ልእልና ዝቅ

ለማድረግ የሚደረግ ተገቢ ያልሆነ  አተያይ ወይም አረዳድ ነው፡፡  በዝህም ታሪክ ዉስጥ ዘቢባ ባለባት የማያባራ የነስር ህመም ምክንያት ክብሯን በማጣት በሰራተኛነት እንኳ ሰርታ እራሷን እንዳታስተዳድር አድርጓታል፡፡በአሰሪዎቹ ዘንድም ሰዉ ከተጎነጸፈዉ የክብር ልዕልና ዝቅ ለማድረግ ተገቢ ያልሆነ አተያይ ወይም አረዳድ ያስገነዝበናል፡፡

‹‹ ዛሬ ግን ይሄዉ በዘቢባ ጉዳይ ተሰብስበን ተቀብጠናል፡፡እኛ ቤት ከገባች ገና አምስት ቀኗነዉ፡፡ ‹‹ትሰናበት›› እና ‹‹አትሰናበት›› በሚል ለሁለት ቡድን ተካፍለን ተቀምጠን እነከራከራል፡፡እኔ ‹‹አትሰናበትም›› እያልኩኝ ስከራከር እናቴ ‹‹ዘርይዉጣልህ›› ትለኛለች፡፡ትሰናበት የሚሉትን አትረግማቸዉም-ትናደድባቸዋለች፡፡…እሷዉ አዉቃ ራሷን ያሳመመች ይመስል እንዲህ ትሂድ ሲባል ለእኔ አልቀለለኝም፡፡ (ሱልይ፣157)፡፡በማለት በታሪኩ ያሰዳስሰናል፡፡

# ምዕረፍ አምስት

## 5 ማጠቃልያና አስተያይት

### 5.1 ማጠቃልያ

ይህ ጥናት "የስነ ምግባራዊ ሂየሳና ትንተና በሱለይ አደም አልፎ ያላለፈና ሌሎች" አጫጭር ልቦለዶች ላይ ሂሳዊ ትንተና በማድረግ፣ስነ ጽሑፍ ስለ ሕይወትና ተፈጥሮ ያለንን ዕወቀት ከማስፋትም በላይ አካባቢያችንንና ማህበረሰባችንን እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ስነ ጹሑፍ በዘመን መንፈስ ዉስጥ የራሱን ጭብጥ እየያዘ እራሱንም በተለያዬ የአጻጻፍ ስልቶች እያሳደገ የማህበረሰቡን ተጨባጭ ህይወትና ኑሮ መልሶ ለማህበረሰቡ ያቀርባል፡፡በጊዜ ሂደትም የስነ ጹሑፍ ሂስ ጭብጥን መሰረት በማድረግ ማጠንጠኛ ከሆኑት መካከል ስነ ምግባራዊ ሂስ አንዱ ሁኖ የሚጠቀስ ነዉ፡፡

የጥናት ዋና ዓላማዉም ተደርጎ የተከናወነዉ ከሱለይ አደም አጫጭር ልቦለዶች መካከል አልፎ ያላለፈ፣ ዘመናይ ማርዬ፣ ልጆን አደራ፣ጆሮየን ጣፈጠኝና የአንድ ነፍስ ጩኸት በሚል ርእስ የቀረቡት ታሪኮች ላይ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን ነቅሶ በማዉጣት ትንተና ማካሄድ ሲሆን ሌሎች ንዑሳን ዓላማዎችን በማካተት ከስነ ምግባር ሂስ አንጻር በመፈከር፣የገጸ ባህሪያቱን ስነ ምግባር የቀረበበትን ስልት በመተንተን፣ቀርቧል፡፡

ሰጥናቱ የስነ ጹሑፍ ጥናት እንደመሆኑ መጠን ትወራዊ መህቀፍን በመጠቀም በተመረጡ አጭር ልቦለድ ላይ "ጹሑፋዊ ትንትኔ ተካሂዷል፡፡ መረጃዎች በቦለዶች ዉሥጥ ያሉ የገጸባህሪያት ስነ ምግባሩ ከአካባቢዉ ጋር በሚኖረዉ መስተጋብር፣ በቤተሰብና መህበራዊ ጉዳዮች በሚፈጥሩት ቁርኝነት እያያዘ ፣ በማህበረሰቡ በሚኖረዉ ህግና ደንብ፣ በሚኖረዉ መስተጋብር፣ ስነ ምግባርና በመላበስና ባለመላበስ ገጸ ባህሪያት እንደተዋቀሩ ያሳያል፡፡

የትንተናዉ ዉጤትም አጠቃላይ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን የዳሰሰ ሲሆን አብዛኛዉን ገጸ ባህሪያት የስነ ምግባር መዛባት እንዳለባቸዉና ለዚህም ያበቃቸዉ የማህበረሰቡን የሰነ ምግባር ደንቦች በመጣስ፣የፈጣሪን ትዕዛዝ በማክበር መልካም ሲባሉ፣ ሳያከብሩና ሱቀሩ እኩይ ሊባሉ በመቻላቸዉ፣ የስነ ምግባር መዛባት የሌለባቸዉ የማህበረሰቡን የስነ ምግባር ደንቦች በማክበር ምስጋናንና ክብርን የቸሩ፣ ሲሆን ተደራሲያን ልቦለዱን በሚያነቡበት ወቅትም በገጸ ባህሪያት ላይ የሚስተዋለዉ የስነ ምግባር መዛባት ከዘመኑ ትዉልድ፣ ከማህበራዊና ስነ ምግባራዊ ስብዕና መዛባት፣ ጋር የሚያያዝ ነዉ፡፡ የስነ ምግባር መዛባት የሚፈጥራቸዉን ችግሮችን ለመቀነስ መከላከያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረጉ ስነ ጹሑፉ በሰዎች ላይ ተጽኖ ፈጣሪ በመሆኑና የራሱን አስተዋጽኦ በማበርከት የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ ያስገነዝባል፡፡ ደራሲያን አጭር ልቦለዶችን በሚደርሱበት ጊዜ ስነ ምግባራዊ ጉዳዬችን ለአንባቢያን ማድረሳቸዉ ስነ ጹሑፉ ለስነ ምጋባራዊ ጉዳዮች የራሱን ጉሉ አስተዋጽዖ ማበርከት እንደሚችል ከዚህ ጥናት መገንዘብ ችያለሁ፡፡

## 5.2 አስተያይት

በአልፎ ያላለፈና ሌሎች አጭርር ልቦለድ ዉስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ስነ ምግባራዊ ጉዳዬች ወደ አንባቢያን ቢደርሱ ተደራሲያን በሰዉ ልጆች ላይ በስነ ምግባራዊ ጉዳዬች ምክንያት ሊደርስ የሚችልን ችግር ከወዲሁ እንዲገነዘቡና በጊዜዉ ለሚንጸባረቁ የስነ ምግባር ችግሮች ተፈላጊዉን መፍትሔ እንዲሹ ያግዛቸዋል፡፡በመሆኑም ደራሲዉ ወደ ፊት እንደነዚህ አይነት በየነ ዲሲፕሊናዊነት ያላቸዉን ጹሑፎች ለአንባቢያን ቢያቀርቡ እዉቀታቸወን ለማካፈል ያስችላቸዋል፡፡

ተደራሲያን ልቦለዱን በሚያነቡበት ወቅት በገጸ ባህሪያት ላይ የሚስተዋሉ የስነ ምግባር መዛባት ከማህባራዊ ህይወት ህግና ደንብ አፈንገጠዉ መዉጣት የሚፈጥራቸዉን ዉጥረቶች ለመቀነስ ማህበራዊ፣ ስነ ምግባራዊና፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዬችን መደበቂያና ከጭንቀት መላቀቂያ በማድረግ መከላከያ ዘዴያቸዉን ከግምት ዉስጥ በማስገባት ተደራሲያን ንባባቸዉን ቢያደርጉ ድርሰቱን ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡እንዲሁም ስነ ምግባራዊ ጉዳዬች በጭብጥ የተገነቡና በቴክኔክ ረገድም ትልሙንና ግጭቱን ለመገንባት ጥቅም ላይ እንደዋለ ከግምት ዉስጥ እያስገቡ ንባባቸዉን ቢያካሂዱ ይዘቱን ለመረዳት ግልጽነት ይፈጥርላቸዋል፡፡

ወደ ፊት ጥናታቸዉን በስነ ምግባር ዙሪያ የሚያደርጉ ተመራማሪዎች የስነ ጹሑፍ ስራዉ ከስነ ምግባር ጋር ያለዉን ዝምድና እንዲሁም የስነ ጹሑፍ ስራዉ በተደራሲያን ስነ ምግባር ላይ ሊያሳድር የሚችለዉን ተጽዕኖ ቢመለከቱና ባለንበት ዘመን የምናያቸዉን የስነ ምግባር መጎደሎች በስነ ጹሑፍ ስራዎች፣ በአዳዲስ ደራሲዎች፣ በአጭር ልቦለድ መድብል መቅረባቸዉና፣ ስነ ምግባራዊ ጉዳዬችን ማንጸባረቃቸዉ ትዉልድን በስነ ምግባር አንጻ ከግብረገብ ባህሪ ጋር አዋህዶ ለማሳደግ መልካም ማሳያ ነዉ፡፡ በዚህም መነሻ መሰረት ሌሎች ተመራማሪዎች ከዚህ ጥናት የተለዬ ግኝት ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚሉት በአስተያይት የቀረቡ ሃሳቦች ናቸዉ፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


ሰላማዊት በየነ፡፡ (2010)፡፡ የተፈጥሮና የባህል ግጭትና እርቅ በአዳም ረታ ህማማትና በገና ውስጥ፡፡ አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤2010 ዓ.ም፡፡

ሱለይ አደም፡፡አልፎ ያላለፈና ሌሎች፡፡ሊትማን መጽሐፍት ማከፋፈያ፡፡2011 ዓ.ም፡፡

ስነ-ኽይወት ገዛኸኝ፡፡ (2007)፡፡ ባይተዋርነት በሰባተኛው መልአክ፣ትኩሳትና ሌቱም አይነጋልኝ፡፡አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤2007 ዓ.ም፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2011)፡፡ ጠርዝ ላይ፡፡ አዲስ አበባ፤ (የህትመት ቦታው ያልተጠቀሰ)፣

ባአምላኩ አስማረ፡፡ስነ ምግባራዊ ሂስ በካራን የተገኘ መሲህ ልቦለድ ጹሑፍ፡(2007)ዓ.ም፡፡

ያልታተመ፡፡

አንተነህ አወቀና ሂሩት አድማሱ፡፡ (2005)ዓ.ም፡፡ ተግባራዊ የስነ ጹሑፍ ሂስ ሞጅል፤፡ባህር

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልተተመ፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (1948) ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡

አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡ ስነ-ምግባራዊ ዝቅጠት በ ኢ.ያሪኮ 777፣ ኢ.ያሪኮ 888 እና ኤጭ…ልቦለዶች ውስጥ

እንደለ ገበየሁ፡፡ስነ-ምግባራዊ ዝቅጠት በ ኢ.ያሪኮ 777፣ ኢ.ያሪኮ 888 እና ኤጭ…ልቦለዶች ውስጥ፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡2012 ዓ.ም፡፡

ቴወድሮስ ገብሬ፡፡(2001)፡፡በየነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጹሑፍ ንባብ፡፡አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ

ዩኒበቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ወንዶሰን ሽመልስ፡፡የሰባዊነት መንጠፍ ፊርጆችና ረቦች በየህሊና ባርነት

ልቦለድ ዉስጥ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡2010ዓ.ም፡፡

ወንድዬ ካሳ፡፡የምሃታዊ እዉነታዊነት ባህሪያት በ "ኤጭ…!"ልባለድ ማሳያነት ፣2313ዓ.ም ያልታተመ፡፡

ኬዳነ መልድ ክፍሌ፡፡(1948)፡፡መጽሐፈ ሰዋሰዉ፡ወገስ፡ወበዝገበ፡ቃላት ሐዲስ፣አዲስ አበባ

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

አንተነህ አወቀና ሂሩት አድማሱ፡፡ (2005)ዓ.ም፡፡ ተግባራዊ የስነ ጽሑፍ ሂስ ሞጅል፡፡ባህር ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልተተመ፡፡

የብሉይና አዲስ ኪዳን መጽሃፍት፡፡አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፡፡ (2011)፡፡ ሥነ-ምግባር፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋህዶ

ቤተክርስቲን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን የታተመ፣

ጠና ደዎ፡፡ (2009)፡፡ ሰው፣ግብረ-ገብና ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች አዲስ አበባ፤

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዮሐንስ አድማሱ፡፡ (1980)፡፡ የልብ ወለድሥነ ጽሑፍ ጉዞ፡፡ መነን መጽሔት፣

ያላዉ እንዳወቀ፡፡(2009)፡፡የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባብር፡፡ባህር ዳር ዩኒበቨርሲቲ፡፡Tefera Seyoum priting pre

ዘረሁን አስፋዉ፡፡የስነ ጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡አዲስ አበባ፣ንግደድ ማተሚያ ድርጅት 1992 ዓ.ም፡፡

Abrhams.M.H.(1999).AGlossaryoflitrariyterms(7th,ed.)Heinle;comelluniversity.Blackburn .s. Beilng, agood,A short introduction to ethics oxfored,university press.2001. Asim, Karim. "Literature and Morality. International" J. Soc. Sci. & Education, Vol. 2, 2012. 186-193. 95

Adewumi,Samuel Idowu. (2013). The Moral, Social and Political decadence in the Nigerian Society: A Case Study of Femi Osofisan's Midnight Hotel. Researchon Humanities and Social Science ISSN 2222-1719 (Paper) ISSN 2222-2863 (Online) Vol.3, No.15, 2013 from www.iiste.org

Anggraini, Dhewinur. (2012). decadence in F.scott Fitzgerald's the beautiful and

Damned(1922): a socio cultural approach. School of teacher Training and education Muhammadiyah University of Surakarta.

Bruce L. Berge. (2011). Qualitative research methods for social science.

California State University, Long Beach: 4th edition.

Elkins (1959) The second and the performance.Trans,willin weaver,London ventage.

Habib.m.a.r.(2005).modern litrary criticism and theory.blackwell.publishing Ltd.

Hampson.E(1988). The construction of personality an introduction.second edition(2nd. Ed).london and newyork:Rutledje.

Horkhemimer.(1937) traditional and critical theory.Britanicas

Khan, Nargis. (2014). Role of Literature in Moral Development. University of

Allahabad. International Journal on Studies in English Language and Literature (IJSELL) Volume 2, Issue 3, March 2014, PP 6-9 ISSN multiplicity of religious denominatons have impacted positively on socioethical behavior). Global Journal of Arts, Humanities and Social Sciences Vol.6, No.9, pp.42-53, September 2018

Landgraf.D.(2014). decadence in Literature and Intellectual debate since 1945. 96

the United States–a division of St. Martin's Press LLC, 175 Fifth Avenue, New York, NY 10010.

Mazar, Naima. (2008).The dishonest of honest people: A theory of self-Consept

maintenance. American marketing association:jornal of marketing research Vol. XLV (December 2008), 633—644

Nikolova, I. (2018). 'Modern morality that gives life to vices: Glimpses of

the image of moral decay in Bulgaria', HTS Teologiese Studies/ Theological Studies 74(1), a4633. https://doi.org/ 10.4102/hts.v74i1.4633

Nyjoku, Dr. Nkechi C.(2016). teachers perception on the dimention of moral -

decadence among Secondary school students. Journal of Education and Practice in Ebonyi State, Nigeria. Journal of Education and Practice: Vol.7, No.26, from:www.jj.org

Prakash, Haveripeth. (2013). prostitution and its impact on socity-acromonological

perspect-Ve. International research jornal of social science.vol.2/3/3139.Nigerian journal of social studies,vol.XIXAPRIL.

Pojman, Louis, P.(2005.) How should we live? An introduction to Ethics.

Solomon R,C.moralityand the good life; introduction through classicalsourecess,new York,mcgra hill book company.1984.

Umeogu,Bonachristus. (2014). the internet communication and the moral egradation of the Nigerian youth. International Journal of Computer and information technology. (ISSN: 2279 — 0764. Volume 03 — Issue 02,

Smith, Douglas .(1998). (GM) On the Genealogy of Morals: A Polemic, translated. Oxford University Press, Oxford World's Classics.

SofadeKan, Adedayo. (2016). Moral decadence and its socio-economic implications on the Nijerian socities. Rennie, L. (2007). Values of science portrayed in out-of-school contexts. In D. Shale, Tena. (2007). The changing face of moral vision in the Amharic novel. Addis Ababa. Addis Ababa university.

Tyson,P,(2006).criticaltheory today aUser-Friendly Guide(2nd.ed.newyork;Ruutledge.

Tenna Dwo. (2007). Traditional Moral Values of the Oromo of Ethiopia:A

Philosophical Appraisal of Gada System Synopsis of a PhD Dissertation. India፡ Panjab University,